# የምልክቱ ድምጽ

በጌታ መገኘት ለጥቂት ጊዜ ቆመን እንቆያለን። ከዘፀአት፡ ምዕራፍ 4 ላይ፡ ከቃሉ እናንብብ።

**... ሙሴም መለሰ፡ እንዲህም አለ፡ ነገር ግን፡ አያምኑኝም፡ ቃሌንም አይሰሙም፡ እግዚአብሔር ከቶ አልተገለጠልህም፡ ይሉኛል አለ።**

**እግዚአብሔርም እንዲህ አለው፡ ይህች በእጅህ ያለችው ምንድር ናት?... እርሱም፡ በትር ናት አለ።**

**ወደ መሬት ጣላት፡ አለው። እርሱም በመሬት ጣላት፡ እባብም ሆነች፤ ሙሴም ከእርሷ ሸሸ።**

**እግዚአብሔርም፡ ሙሴን፡ የአባቶቻቸው አምላክ፡ የአብርሃም አምላክ፡ የይስሐቅም አምላክ፡ የያዕቆብም አምላክ፡**

**እግዚአብሔር እንደ ተገለጠልህ እንዲያምኑ እጅህን ዘርግተህ ጅራትዋን ያዝ አለው፡ እጁንም ዘርግቶ፡ ያዛት፡ በእጁም ውስጥ፡ በትር ሆነች።**

**እግዚአብሔርም ደግሞ፡ እጅህን ወደ ብብትህ አግባ አለው። እጁንም ወደ ብብቱ አገባት፡ ባወጣትም ጊዜ፡ እነሆ፡ እጁ እንደ በረዶ ለምጽ ሆነች።**

**እርሱም፡ እጅህን ወደ ብብትህ መልስ አለው። እጁንም ወደ ብብቱ መለሳት፣ ከብብቱም ባወጣት ጊዜ፡ እነሆ፡ ተመልሳ፡ ገላውን መሰለች።**

**ደግሞም አለው፡ እንዲህም ይሆናል፡ ባያምኑህ የፊተኛይቱንም ምልክት ነገር ባይሰሙ፡ የሁለተኛይቱን ምልክት ነገር ያምናሉ።**

**እንዲህም ይሆናል፡ እነዚህን ሁለት፡ ምልክቶች ባያምኑ፡ ቃልህንም ባይሰሙ፡ ከወንዙ ውኃን ውሰድ፡ በደረቁም መሬት ላይ አፍሰሰው፡ ከወንዙም የወሰድኸው ውኃ በደረቁ መሬት... ላይ ደም ይሆናል።**

2 ለጸሎት አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። አሁን በዚህ ምሽት፡ ለጌታ ልታሳውቁ የምትፈልጉት፡ ልመና አላቻሁ፡ እጆቻችሁን አንስታችሁ እንዲህ በሉ፡ “ጌታ ሆይ፡ አሁን አስበኝ። የሚያስፈልጉኝ ነገሮች አሉ።”

3 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ ዛሬ ማታ በድጋሚ ወደ አንተ እንቀርባለን፡ ወደ መጣንበት አፈር አንገታችንን ስንደፋ፡ አንተም፡ ብትዘገይ፡ ወደ አፈር እንደምንመለስ ተረድተናል። ነገር ግን በክርስቶስ ባለው በተባረከው በተስፋው ቃል ኪዳን፡ በእግዚአብሔር ያሉትን ሁሉ ክርስቶስ ከእርሱ ጋር ያመጣቸዋል። እኛም——ስለዚህ ክቡር ቃል ኪዳን እናመሰግንሃለን። አምላኬ

ሆይ እጆቻቸውን የሚዘረጉትን ሁሉ፡ የኔንም ጭምር፡ እንድታስታውሳቸው፡ እኔ አጸልያለሁ፡ ጌታ ሆይ።

4 በዚህ የእምነት መዝጊያ ሰዓት ላይ፡ በዚህ ምሽት ለሰዎች እንደዚህ ያለ እምነት እንድትሰጣቸው፡ ዛሬ ማታ፡ እፀልያለሁ፡ ጌታ ኢየሱስ ለእያንዳንዳችን እውን እንደሆነ፡ ከዛሬ ምሽት በኋላ በመካከላችን ደካማ ሰው አይኑር። በዚህ በመጨረሻው ክፉ ሰዓት፡ በምድር ላይ ታላቅ ጥላ ሲያጠላ ስናይ፡ ኃጢአተኛ ሁሉ፡ በጌታ በኢየሱስ መገኘት እንዳለ ተገንዝቦ፡ ከኃጢአቱ ንስሐ ይግባ፡ ልቡንም ለአንተ ሰጥቶ በመንፈስም ይሞላ።

5 እግዚአብሔር ሆይ፡ በዚህ ምሽት፡ ለመናገር እና ለመስማት፡ ለመለኮታዊ ምሪት፡ እንጸልያለን። መንፈስ ቅዱስ አሁን ሰብሰባውን ይውሰድና የህይወት እንጀራ ለሁላችን እንደየ አስፈላጊነታችን ቆርሶ ይስጠን፡ በስሙ እንለምናለንና። አሜን።

አረፍ አረፍ በሉ።

6 ዛሬ ማታ ህዝቡ እንዲያይ የምንሞክረውን ነገር ማከናወን እንደምንችል አምናለሁ፡ ይህም በ—በእግዚአብሔር ላይ እምነት የማድረግ እውነታ ነው።

7 አሁን፡ ነገ ከሰአት በኋላ ሁለት-ተኩል ላይ፡ የጸሎት ካርድ ያላቸው ሁሉ ይጸለይላቸዋል። ከዚያም ማንም ሰው ያለ ጸሎት ካርዶች፡ እንደማይቀር እርግጠኛ ለመሆን፡ በእያንዳንዱ ምሽት አንዳንድ የጸሎት ካርዶችን እንሰጣለን። እና ነገ እንደገና ይሰጣቸዋል፡ ሰለ... እንደማስበው ከሆነ፡ አንድ-ተኩል ገደማ ወይም እንደዚህ ያለ ነገር፡ ልክ ሰብሰባው ከመጀመሩ በፊት። እንዲጸለይላቸው የሚፈልጓቸው ሁሉም፡ ለምትወዷቸው ሰዎች፡ መጥተው የጸሎት ካርድ እንዲወስዱ አድርጓቸው። በርግጠኝነት—ወደ የሎት ካርድ እንኳን በደህና መጣችሁ ይባላሉ። እኛም...

8 እጄን በእነሱ ላይ በመጫን እና ለእነሱ በመጸለይ፡ ለሰዎች መጸለይ እፈልጋለሁ። አሁን እምነታችሁ በጌታ በኢየሱስ መገኘት ካልተነሣ እና እንደ ፈዋሻችሁ ሊቀበለው ካልቻለ፡ ብንጸልይላችሁ እና እጃችንን ብንጭንባችሁ፡ እንደሚረዳችሁ ብቻ ካመናችሁ፡ እንደው፡ የምትፈልጉትን ማንኛውንም ነገር ለማድረግ በእርግጠኝነት እዚህ መጥተናል።

9 የምችለውን ሁሉ እያየሁ ዘግይቼ፡ ረጅም፡ ጊዜ ያቆምኩት ምክንያት፡ በእነዚያ መሠረት ወደ እግዚአብሔር ልትደርሱ እና ልታገኙ ትችላላችሁ በሚል ነው። ብዙዎች የሉንም። ያለን... ሕንፃው ትልቅ አይደለም፡ በዚህም ምክንያት ብዙ ሰዎች የሉንም። እናም ነገ ከሰአት በኋላ ተጠቅመን እዚህ ስላለው ሁሉ መጸለይ እንችላለን፡ የከሰዓት በኋላ ሙሉውን ተጠቅመን፡ ለታመሙ እንጸልያለን።

10 እና ህይወትን ትንሽ የተሻለ እንዲሆን ለመርዳት የተቻለንን ነገር ለማድረግ እዚህ ተገኝተናል፡ በዚህ እየተጓዝንበት ባለው ጉዞ፡ ሸክማችሁን ቀላል ለማድረግ።

11 ከዚያም በማንኛውም ጊዜ፡ ወደ—ጌታ ኢየሱስ መምጣት የተሰማው፡ ማንም ሰው ቢኖር የአገልግሎቱ ክፍል እየተካሄደ የትም ላይ ቢደርስም፡ ወዲያውኑ ኑ። የመሠዊያው ጥሪ እስኪደረግ ድረስ አትጠብቁ። ግብዣው

እስኪሰጥ ድረስ አትጠብቁ። ያን ጊዜ መጥታችሁ፡ ክርስቶስን ተቀበሉ፡ ወዲያውኑ መጥታችሁ እምነዋለሁ በሉ። የመኖራችን ዋና አላማ፡ በእግዚአብሔር መንግስት የተወለዱ ነፍሳትን ማየት ነው።

12 አሁንም፡ ነገ እሁድ ስለሆነ፡ በየአብያተ ክርስትያናት ሁሉ፡ ሰንበት ትምህርት ይኖራል። እሁድ፡ አገልግሎታችንን፡ ከሰአት በኋላ የምናደርግበት ምክንያት ምንም አይነት አገልግሎት ላለማሰናከል ነው። እያንዳንዱ ክርስቲያን የሚሄድበት የ—የራሱ ቤተ ክርስቲያን ሊኖረው ይገባል ብለን እናምናለን። ክርስቲያን ሁሉ ከአማኞች ጋር አንድ ቦታ ህብረት ማድረግ አለበት። ህብረት የምታደርጉበት ስፍራ ሁሉ፡ ቤተክርስቲያን ነው።

13 አሁን፡ ኑሮዬ እዚህ ቢሆን፡ እዚህ ያሉ ፓስተሮች ተባብረው፡ የሚወክሏቸው፡ አብያተ ክርስትያናት፡ የአንዱ አባል እሆን ነበር። ለምን? ምክንያቱም ለሰዎች ሁሉ እንዲታዩ፡ እየተደረገ ያለውን ነገር ለመደገፍ፡ እዚህ መድረክ ላይ ተቀምጠዋል። በዚህ ዓይነት አገልግሎት፡ በመለኮታዊ ፈውስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት፡ እና በመሳሰሉት ያምናሉ። ስለዚህ ነገርም በዚህ ዙርያ እየመሰከሩ ይገኛሉ። ወደዚህ እንድመጣ የጋበዙኝም እነሱ ናቸው፡ ይህም ምናልባት ጌታ የሰጠኝ አገልግሎት ጉባኤያቸውን ይረዳ ዘንድ ነው።

14 አሁን የተቻለውን መንፈሳዊ ጥቅማጥቅሞች የሚፈልግ፡ እውነተኛ ፓስተር ማለት ይህ ነው፡ እግዚአብሔር ከሚሠራው ነገር ሁሉ፡ ቤተ ክርስቲያኑ ወደ እግዚአብሔር እንድትደርስ የተቻለውን ሁሉ ይጥራል። ለእንደዚህ አይነት ፓስተር በአድናቆት ኮፍያዬን አወልቃለሁ።

15 እነዚህ ሰዎችም ያን የሚያደርጉት፡ በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነው። እውነታውን መቀበል አለባችሁ። ይህን ማድረጋቸው በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ነውና። እና እኔ—ስለ እንደዚህ አይነት ታላቅ የእግዚአብሔር ሰዎች በእውነት አመሰግናለሁ፡ ስፍራቸውን እና አገልግሎታቸውን በራሳቸው አቋም፡እና—በራሳቸው እምነት ለማራመድ የፈቀዱ ናቸው። እግዚአብሔር አብዝቶ ይባርካቸው!

16 እና እነሱ ጥሩ እንደሚያደርጉላችሁ እርግጠኛ ነኝ። አሁን፡ እዚህ እንግዳ ከሆናችሁ፡ እነዚህ ወንድሞች ቤተክርስቲያናቸው የት እንዳሉ፡ የት እንዳሉ እወቁ። ነገ ልዩ አገልግሎቶች ይኖራቸዋል። ጎራ በሏቸው፡ ማስታወቂያ እንደተነገረ፡ በተለያዩ አብያተ ክርስቲያናት የሚሰብኩ አገልጋዮች እዚህ አሉ። ስለዚህ ነገ ከእነርሱ ጋር ሁኑ።

17 ነገ ከሰአት በኋላ ግን፡ ወደ መዝጊያው አገልግሎት ለመምጣት ከፈለጋችሁ፡ እናንተን ለመቀበል ደስታ ይሰማናል። ለሁሉም አብያተ ክርስቲያናት፡ ለሁሉም ሃይማኖት ተቋሞች፡ ለሁሉም ነው። ሁሉም ሰው እንቀበላለን፡ ሜቶዲስት፡ ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ጴንጤቆስጤ፡ ቸርች ኦቭ ክራይስት፡ ቸርች ኦቭ ጋድ፡ ካቶሊክ፡ ኦርቶዶክስ ጁው፡ አምላክ የሌላቸው ኤትይስት፡ ምንም ይሁን ምን። እኛ... ጋብዘናችኋል።

"'ኤትይስትም፡ ትላላችሁን? " አዎን፡ ዎዳጄ።

18 አምላክ የሌላው ኤትይስት ሰው በስብሰባው ላይ መጥቶ በጥሩ ምግባር ቢቀመጥ፡ እንደማንኛውም ሰው እንቀበለዋለን። ትክክል። እሱን እዚህ

የምንፈልገው፡ ምክንያት፡ ምናልባት ስህተቱን አይቶ፡ ወደ ጌታ እንዲመጣ የሚረዳው ነገር እንዲደረግ። እርግጠኞች... ነንና።

19 የክርስቲያን ቢዝነስ ሜንስ ያሳተሙት ባለ ራዕይ ትንሿ ጋዜጣ፡ እና ሌሎች ጥቂት ጋዜጦች ሰንቶች አንብባችኋል-... ፡ እነ፡ **ሉኪንግ ፓስት ዘ ከርተይን ኦቭ ታይም**? እንግዲህ ወዳጆች ሆይ፡ ያ እውነት ነው። ያንን እንዲያመልጣችሁ አትፍቀዱ። እኔ—ራሴ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የተለየ ሰው ሆኛለሁና። ያ እውነት እንደሆነ አውቃለሁ፡ ስለዚህ ማናችሁም እግዚአብሔር ለአማኞች ያዘጋጀውን ታላቅ ሰማይ እንዳያመልጣችሁ እ—እ—እምናለሁ። እንዲህ ከሆናችሁ፡ እዚህ ምድር ላይ ምን አሳካችሁ? ምክንያቱም፡ ከዚህ ዓለም በየትኛው ሰዓት እንደምትለዩ አታውቁምና። መለየታችሁ የማይቀር መሆኑን ግን፡ ይህን አንድ ነገር ታውቃላችሁ። ስለዚህ ያ እውነት ከሆነ፡ እኛ ለመሞከር በጣም ሞኞች አልሆንንም—ልክ ለማግኘት... ምንም አይነት እድል ለመውሰድ አንችልም። እያችሁ፡ ብቻ አስታውሱ፡ የእግዚአብሔርን ቃል እና በእሱ ውስጥ ያለውን የተሰፋ ቃል እመኑ።

20 እስቲ አስቡት፡ እያንዳንዱን በሽታ፡ እያንዳንዱ የልብ ህመም፡ እያንዳንዱን ሞት፡ እያንዳንዱን ችግር፡ እያንዳንዱን ሃዘን፡ ይህ ትንሽ ልጅ፡ እነዚህ ሁሉ ነገሮች፡ አካል ጉዳተኞች፡ ዓይነ ሰውራን፡ እያንዳንዱ ሆስፒታል የተገነባው በምን ምክንያት ነው? ምክንያቱም የቃሉን ትንሽ ክፍል ያላመነች ሰው ስለነበረች ነው። እሷም ሔዋን ነበረች። ሰይጣን ሸፈነባት። አልጠቀሰላትም፡ ግን ሸፈነባት፡ እንዲህ አላት፡ “በእውት... ጌታ እጅግ መልካም ነው።”

21 እግዚአብሔር መልካም አምላክ ስለመሆኑ፡ ዛሬ ብዙ ሰምታችኋል። መልካም አምላክ ነው፡ ነገር ግን የቅድሰና አምላክም ደግሞ ነው፡ ኃጢአትን ችላ የማይል አምላክ መሆኑን አስታውሱ። ቅጣቱ ተከፍሏል፡ እና በቅድመ ሁኔታዎቹ መሰረት መቀበል አለባችሁ። የቁጣ አምላክ፡ የቁጣ አምላክ መሆኑንም፡ አስታውሱ። በቸርነት እና በምህረት አምላክ ብቻ ሳይሆን፡ በቁጡ አምላክ ፊት ትቆማላችሁ። ዛሬ ማታ አዳኛችሁ ነው፡ በዚያ ቀን ፈራጃችሁ ነው።

22 ስለዚህ አንድም ነገር ሳትጨርስ እንዳትተወው እርግጠኛ ሁን፡ ወዳጄ። እሱ—አይሆንም... ላንተ አይበጅህም። በአጋጣሚ ብቻ አት—አትቅረብ። እርግጠኛ ሁን፡ ደግመህ እረጋግጥ፡ ምክንያቱም ሌላ እድል ስለማታገኝ ነው። እዚህ ምድር ላይ ስትሆን፡ ይህ ያንተ ብቸኛ እድል ነው። ባለጠጋውን ሰው እና አልዓዛርን አስታውሳቸው።

23 “በእሱ በእናንተ መካከል፡ ማንም ሰው ያልተሻገረው፡ ወይም የማይሻገርው ታላቅ ገደል አለ።” እያችሁ? እናንተ—ሰትሞቱ፡ ያኔ ይገባችኋል። በጸሎታቸው ከዚያ ሰፍራ እንደሚያወጧችህ የሚናገሩ ሰዎች እንዳሉ አውቃለሁ፡ ነገር ግን በፍጹም አትመኗቸው። ይህ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ይቃረናል። እያችሁ? “ዛፉ ዘንበል የሚልበት መንገድ፡ ያ የሚወድቅበት መንገድ ነው።” ኢየሱስም፡ ራሱ፡ እንዲህ አለ፡ “አንድ ሰው ከሞተ፡ ወደ ሲኦል በገባ ጊዜ፡ ገደል መኖሩን እና፡ ወደ መንግሥተ ሰማያት ፈጽሞ ሊመጣ እንደማይችል ተናግሯል።” ማንም ሰው አላለፈውም፡ እና በጭራሽ አያልፈውም። ኢየሱስ እንደዛ ነው ካለ፡ ያ ብቻ ነው። እንደሚመስለኝ፡ መልሱ ያ ነው።

24 ስለዚህ አስታውሱ፡ አሁን እድላችሁ ነው፡ እና ዛሬ ማታ የመጨረሻ እድላችሁ ሊሆን ይችላል።

25 ምን እየተካሄደ እንዳለ መረዳት ትችላላችሁ? ከቻላችሁ ተመልከቱት! ንግግሬ እንደዛ አታስቡትም ብዬ ተስፋ አደርጋለው፡ አንድን ሰው እንድትመለከቱ፡ ወይም አንድን ሰው እንድታምኑ ተጽዕኖ ለማድረግ እየሞከርኩ ያለው እንዳይመስላችሁ። ያንን እያደረኩ አይደለም፡ ወዳጄ። አሁን በመገኘቱ ውስጥ ያለነው ማን እንደሆነ እንድታምኑ እየሞከርኩ ነው። በዚያ ቀን የሚፈርድባችሁ፡ እምላክ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በእናንተ ፊት ራሱን እያሳየ ነው፡ በዚህ በመጨረሻው ዘመን እንደሚያደርገው የገባውን ቃል ያደርገዋል።

26 ይመስለኛል ወንድም ፕራይስ፡ ዛሬ ጠዋት ቁርስ ላይ፡ ወደ አንድ ጠርዝ ስለመምጣት፡ ከዚያም ጠርዙን ስለ መዞር ጥሩ ምሳሌ ሰጠ። በዚህ ደስተኞች ናችሁ? [ጉባኤው፡ "አሜን።" አለ—አርታዒ።] በእርግጠኝነት ናችሁ። በጣም፡ በጥሩ ሁኔታ አስቀምጦታልና።

27 አሁን፡ ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ፡ ጠርዝ ላይ እናስታውሰዋለን፡ ነገር ግን እነዚህን ጠርዞችን መዞር እንዳለብን አስታውሱ። አንድ ጊዜ፡ በዚህ ጉዳይ ላይ ሰበኩኩኝ፡ **መስቀለኛ መንገድ**፡ ብዬ ጠራሁት። ብዙ ጊዜ፡ መስቀለኛ መንገድን እናገኛለን፡ **በዚህ** መንገድ እና በተለያዩ መንገዶች እንሄዳለን።

28 አሁንም ዛሬ ማታ፡ ለሚቀጥሉት ጥቂት ደቂቃዎች፡ **የምልክቱ ድምጽ** በ—በሚል ርዕስ፡ መውሰድ እፈልጋለሁ። እና አሁን የእኛ ዛሬ ምሽት፡ አገልግሎታችን የሚከፈተው፡ በዘፀአት መጽሐፍ ውስጥ ይሆናል፡ **ዘፀአት** ማለት "መውጣት፡ ማውጣት" ማለት ነው። አሁን በተቻላችሁ መጠን በቅርበት ለማዳመጥ ሞክሩ።

29 የሆነ ጊዜ ልሰብካችሁ እፈልጋለሁ፡ በጣም ጥሩ ጉባኤ ናችሁ፡ ግን በቃ ድምጽ የለኝም። በዛ ላይ ትንሽ ጫና አለ፡ እና ምን እንደሚሆን አውቃለሁ። የሚቀጥለውን ስብሰባ ከመጀመሬ በፊት፡ ለሰምንት ወይም ለአስር ቀናት ያህል፡ አሁን ትንሽ ማረፍ አለብኝ። እያችሁ፡ እዚህ አንድ ስብሰባ ብቻ አይደለም። ከቀን ወደ ቀን፡ ከሳምንት እስከ ሳምንት፡ ከወር እስከ ወር፡ ከአመት እስከ አመት፡ ስብሰባ ነው፡ እያችሁ፡ እና መገመት ትችላችሁ።

30 እና ሁሉንም ጊዜዎች፡ ከዓመት እስከ ዓመት አስቡ፡ ፍጹም እና ትክክለኛ የሆነውን ብቻ እንጂ፡ አንድም ጊዜ ሌላ ተናግሮ አያውቅም፡ ሰባት ጊዜ፡ በሁሉም ቋንቋዎች፡ በመላው ዓለም። እያችሁ? ማንም ሰው፡ የትም፡ በትክክል ምን እንደነበረ፡ በትክክል በነጥቡ ላይ፡ ሁል ጊዜ ሊናገር አይችልም። አንድ ነገር ይሆናል ሲል፡ ልክ እንደዚያው ይሆናል። ለሳምንታት እና ለወራት፡ እና ለዓመታት፡ ከመሆኑ በፊት እንኳን፡ ቢናገርም፡ ሁል ጊዜ በትክክል በነጥቡ ላይ ነው። አንድ ጊዜም ወድቆ አያውቅም፡ በጭራሽም አይወድቅም፡ ምክንያቱ እግዚአብሔር ነው። አሁን፡ እኔ እንደ ሰው፡ ልወድቅ እችላለሁ። በፍፁም እንደ ምሳሌ እንዳታዩኝ፡ ምክንያቱም እኔ—ልክ እንደ እናንተ ነኝ፡ በጸጋው የዳነ ኃጢአተኛ ነኝ። ያ ግን እግዚአብሔር ነው፡ ከተፈጥሮ በላይ የሆነው፡ ራሱን የሚለይ፡ እያችሁ፡ ያንን ማድረግ አይጠበቅበትም፡ ነገር ግን እሱ እንደሚያደርገው ቃል ገብቷል።

31 ኢየሱስ ፈውሷል ምክንያቱም ቃሉን ሊፈጽም ስለሚችል። እነዚህን ነገሮች ያደረገው የእግዚአብሔር ቃል ስለሚፈጸም ነው።

32 ዛሬም ያንን የሚያደርገው ለዚህ ነው፡ እኔ ሌሊት እስከ ሌሊት፡ የነገርኳችሁ ቃሉ ይፈጸም፡ ዘንድ ነው።

33 አሁን አስተውሉ መገኘቱ ሲጠጋን፡ ያ፡ በእርግጥ፡ ስሜቶችን ይቀሰቅሳል። ዛሬ ጠዋት "ስሜት የሌለው ሁሉ የሞተ ነው፡" በማለት ተናግሬአለሁና። የትኛውም ኃይማኖት ምንም አይነት ስሜት ከሌለው፡ ብትቀብሩት ይሻላል፡ የሞተ ነው። ስሜት ይሰጣልና። እሱ ህይወት ይሰጠናል። ህይወት ሰናገኝ፡ ህይወት የሚሰጠን ምን እንደሆነ እናስታውስ። ህይወት የሚሰጠን ምንድነው? ኢየሱስ ክርስቶስ በመካከላችን፡ ሕያው መሆኑን ራሱን እያሳየ ያለው፡ የመንፈስ ቅዱስ መገኘት ነው። የሰው አካል አይደለም፡ ያ አካል ከሰማይ ሲመለስ፡ ያን ጊዜ፡ ጊዜ አይኖርም። ያን ጊዜ ያበቃለታል። እናም እነዚህ ነገሮች ሲፈጸሙ፡ በመጨረሻው ቀን፡ እንደምንኖር እናውቃለን።

አሁን፡ እግዚአብሔር ከዚህ በፊት ብዙ ዘፀአቶች አካሂደዋል። አለ...

34 በእግዚአብሔር ዘንድ፡ ነገር ሁሉ በሦስት ይጓዛል። እግዚአብሔር በሦስት ፍጹም ይሆናልና። የክርስቶስ የመጀመሪያ መምጣት፡ ሙሽራዋን **ሊቤዣት፡** የክርስቶስ ሁለተኛ ምጽአት፡ ሙሽራዋን **ለመውሰድ፡** ሦስተኛው የክርስቶስ መምጣት፡ ከሙሽሪት **ጋር**፡ ለአንድ ሺህ ዓመት ለመግዛት። ሁሉም ነገር በሦስት ነገር ውስጥ ይካሄዳል።

35 አሁን፡ ከዚህ በፊት፡ እንግዲህ ወደፊት፡ ሦስት ዘፀአቶች ይሆናሉ። አንደኛው፡ እግዚአብሔር ዘፀአት ሲያደርግ፡ ወደ መርከብ **ውስጥ** አስገባቸው፡ ከምድር በላይ ተሳፈሩ። ሁለተኛው ጊዜ፡ እግዚአብሔር ከ—ከግብፅ **ወደ ውጭ** አስወጣቸው። ሶስተኛው ጊዜ፡ እግዚአብሔር **ወደ ላይ** ይወስዳቸዋል። ወደ ውስጥ፡ ወደ ውጭ፡ ወደ ላይ! የሚቀጥለው ዘፀአት ወደ ላይ መወሰድ ነው። አሁን እየተጋፈጥን ያለነው፡ ወደ-ላይ የመወሰድ ጊዜ ነው።

36 በሕይወትም ተመሳሳይ ነገር ይሆናል። ወደ ሕይወት **ውስጥ** መጣን፡ ከሕይወት **ውጭ** እንወጣለን፡ **ወደ ላይ** ወደ ሕይወት እንነሳለን፡ ልክ ተመሳሳይ ነገር ነው። ስለዚህ እኛ...

37 የዛሬ ማታ አገልግሎታችን በዘፀአት ላይ ይጀመራል፡ እግዚአብሔርም ህዝቡን ለመውሰድ እየተዘጋጀ ነበር።

38 እስራኤል ሕዝብ ነው። እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር በግለሰብ ደረጃ አይገናኝም። ከእስራኤል ጋር ሲሰራ፡ ሁልጊዜም እንደ ህዝብ ነው። በመጨረሻዎቹ ቀናትም፡ ከ—ቤተክርስቲያን መወሰድ በኋላ፡ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደ ሕዝብ ያድናቸዋል። ይህን ለማድረግ ተዘጋጅቷል፡ አሁን በአገሪቱ ውስጥ ነው። እነርሱም ይድናሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ "ሕዝብ በአንድ ቀን ይወለዳል፡" ይላል። እግዚአብሔር አይሁዶችን እንደ አንድ ግለሰብ አያይም። እስራኤል፡ ህዝቡ ናቸውና፡ እንደ ሕዝብ፡ ይሰራባቸዋል።

39 በዚህም በዘፀአት ላይ፡ ሕዝቡን ከሕዝብ መካከል ሊያወጣ፡ ሕዝቡን ከፍርድ ሊያመጣ ነው።

40 ዓለምን ያሰጠመ ያው ውሃ፡ ኖኅን አዳነው። አያችሁ? ዛሬም ሕዝቡ የሚቃወመው፡ ያው መንፈስ ቅዱስ፡ ቤተክርስቲያንን ይቀበላትና ወደ ላይ ይወስዳታል፡ በማያምኑትም ላይ ፍርድ ያመጣል።

41 ኢየሱስን፡ "ብዔልዜቡል፡" ብለው በጠሩት ጊዜ፡ በሌላ አነጋገር "ጠንቋይ፡" ማለታቸው ነው፡ እነሱ... እንደዚህ አላቸው፡ "ለዚያ ይቅር እላችኋለሁ፡" (መሥዋዕቱ፡ ማለት የሰው ልጅ ገና አልቀረበምና።) "መንፈስ ቅዱስ ያንኑ ነገር ሊያደርግ በመጣ ጊዜ ግን፡ እሱን በአንዲት ቃል መቃወም በዚህ ዓለምም ሆነ በሚመጣው ዓለም ፈጽሞ አይሰረይለትም።"

42 ፍርድ የመጣ ዘንድ፡ እሱን ይቃወሙት ዘንድ ይገባዋል። አያችሁ፡ ችግሩ እራሳችን...

43 በአንድ ወቅት ስለ አንድ ከባህር ስለመጣ ሽማግሌ መርከበኛ፡ ያነበብኩት ታሪክ ትዝ አለኝ፡ እና አንድ—አንድ ወጣት እንግሊዛዊ ገጣሚ ወደ ባህር እየሄደ ነበር። እናም ገጣሚው ስለ ባሕሩ ብዙ ጽፎ ነበር፡ አይቶት ግን አያውቅም፡ ለማየት ጉዞ ላይ ነበር። ሽማግሌው አሳሽም፡ ከፒፓው የቀረውን በአፉ ይዞ፡ እንዲህ አለው፡ "መልካም ሰው ሆይ፡ ወዴት እየሄድክ ነው? "

44 እርሱም፡ "ወደ ባህር እየወረድኩ ነው።" እንዲህ አለው፡ "አይቼው አላውቅምና። ሌሎች ስለሱ የሚሉት ነገር፡ ጽፌያለሁ፡ ግን፡" እንዲህም አለ፡ "ኦህ፡ ወደ ባሕሩ መቃረቤን በማወቄ በጣም ተደስቻለሁ።" እንዲህ አለ፡ "ኦህ፡ ጨዋማ መአዛው ለማሽተት! ትልልቅ የባሕር አራዳዎች፡ ከላይ ሲንቦጫረቁ ለማየት፡ ሰማያዊው ሰማይም እራሱን ሲያንጸባርቅ ለማየት፡ እና የባህር ወፎች እየበረሩ ሲሄዱ መስማት፡ ኦህ፡ ለማየት በማሰቤ በጣም ተደስቻለሁ!"

45 ሽማግሌው አሳሽ፡ "እኔ ከሰልሳ አመት በፊት፡ በዚያ ተወለድኩ፡ እስከ አሁን ምንም የሚያምር አላየሁበትም።" አያችሁ፡ የተለመደ እስኪሆንበት ድረስ እጅግ አብዝቶ አይቶታል።

46 ዛሬ የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ችግርም ያ ነው። እግዚአብሔር የተለመደ እስኪሆንባቸው ድረስ፡ ስለ እግዚአብሔር እጅግ ታያቸው። ያ እንዲሆንባችሁ ፈጽማችሁ ትፍቀዱ!

47 እዚህ በቅርብ ጊዜ፡ በሎይቪል፡ ኬንታኪ፡ ከመጣሁበት ቦታ፡ ጄፈርሰንቪል፡ ኢንዲያና፡ ከወንዙ ማዶ፡ አንዲት ሴት በተን-ሰንት ሱቅ ውስጥ ትሄድ ነበር። እና በእጇም፡ ህጻን ልጅ አቅፋ ነበር፡ እና ወደ ባንኮኒ እየቀረበች እጅግ ትበሳጭ ነበር። የሆነ ነገር ታነሳለች፡ ለትንሹ ልጅ ታሳያለች፡ ቁጭ ብሎ ዝም ብሎ ያያል። ወደ ሌላ ባንኮኒ ትሄዳለች፡ የሆነ ነገር ወሰዳ ለትንሹ ልጅ ታሳያለች፡ ዝም ብሎ ያያል። ከትንሽ ቆይታ በኋላም፡ ትንሽ ደወል አንስታ ማንቃጨል ጀመረች፡ ትንሹ ልጅም ዝም ብሎ አየ። ከዚያ መጮህ ጀመረች፡ እና እጆቿን ወደ ላይ አወናጨፈች። እና በቴን-ሴንት ሱቅ ውስጥ ያሉ ሰዎች እሷን ይመለከቷታል፡ እናም ምን እንደተፈጠረ ለማወቅ ወደ እርሷ ሄዱ።

48 እንዲህ አለች፡ "እኔ... ትንሹ ልጄ፡" እንዲህ አለች፡ "ገና ሦስት ዓመቱ ነው።" እናም እንዲህ አለች፡ "እ... ከአንድ አመት በፊት፡ በድንገት፡ ዝም ብሎ ተቀምጦ በሆነ ነገር ላይ አፍጥጦ ማየት ጀመረ።" እንዲህ አለች፡ "ወደ ሐኪም ወ—ወሰድኩት፡" "ዶክተሩም የተወሰኑ መድሃኒቶች አዘዘለት፡" አለች። እንዲህም አለች፡ "እናም ዶክተሩ፡ ዛሬ፡ የተሻለው ይመስላል ብሎ

ነገረኝ። ነገር ግን፡" "እየተሻለው አይደለም፡" አለች። እንዲህ አለች፡ "ይህም በእሱ ዕድሜ ያለውን ትንሽ ልጅ፡ ትኩረትን መሳብ የሚችል ነገር ሁሉ፡ በፊቱ አቃጨልኩበት። በእሱ ዕድሜ ላይ ያለ ትንሽ ልጅን የሚስብ ነገር ሁሉን፡ በፊቱ አቃጨልኩበት፡ እና ዝም ብሎ ተቀምጦ አየር ላይ ያፈጣል።" "እየተሻለው አይደለም፡" አለች።

49 በጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን ያለ ነገርም ይህ ነው። እግዚአብሔር በመጽሐፍ ቅዱስ፡ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም፡ ስጦታዎች አቃጨለ፡ የሆነ ስህተት እንዳለው አይነት፡ አሁንም ተቀምጠው አየር ላይ አፍጥጠዋል። ወዳጆች ሆይ፡ ጊዜው ከማለፉ በፊት፡ የምንነቃበት ጊዜ ነው። አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ትኩረታችሁን ለመሳብ ካልሞከረ በስተቀር እነዚህን ስጦታዎችን አያንቀሳቅስም።

እግዚአብሔር ሕዝብን ከሕዝብ መካከል እያወጣ ነው።

50 ልክ አሁን እንደሚያደርገው፡ የሴቲቱን የቅሪት ዘር ትቶ፡ ሙሽራይቱን ከቤተ ክርስቲያን ሊያወጣ እንደሆነ ሁሉ ነው። የተመረጡት ከቤተክርስቲያን ይወጣሉ። ፍጥረታዊት ቤተክርስቲያን በታላቁ መከራ ውስጥ ታልፋለች። **ምርጦች** አንዳንድ ጊዜ "የተመረጡ፡ ምርጥ፡ ቅሪቶች" በመባል ይታወቃሉ።

51 ያኔ እንዴት እንዳደረገው እንይ፡ ምክንያቱም እሱ ነገሮችን የሚያደርግበትን መንገድ ፈጽሞ አይለውጥምና። እግዚአብሔር ነገሮችን የሚያከናውንበት አንድ መንገድ አለው፡ እና ያ እሱ የሚያደርግበት መንገድ ነው፡ እና ያ ሁልጊዜም፡ ትክክለኛው መንገድ ነው። እንዴት እንዳደረገው፡ እና ያደረገበትን ስርአት ተመልከቱ፡ እና ይህን በጨረፍታ ማየት እንችላለን።

52 አሁን፡ እኔ በእርግጠኝነት፡ ታይፖሎጂስት ነኝ። ትምህርት የለኝም። ወደ ኋላ መለስ ብዬ እሱ ያደረገውን ማየት አለብኝ። እና "ብሎይ ኪዳን ሊመጡ ላላቸው ነገሮች ጥላ እንደነበር፡" ተምረናል። እንግዲህ እዚህ አይቼ እጄን ከቶ ባላየው፡ እና ምስትም ጣቶች እንዳሉኝ፡ የእጄን ጥላ ቢታየኝ፡ እጄን ሳየው አምስት ጣቶች እንደሚኖሩኝ፡ ጥሩ ግንዛቤ ይኖረኛል። ስለዚህ በእነሱ ላይ የሆኑ ነገሮች እግዚአብሔር እንዴት እንደሚሰራ፡ አሁን የሚያደርገውን መንገድ የሚያሳይ ምሳሌ ነው።

53 በሚያደርግበት መንገድ፡ ደግሞ ከዚያ አይለወጥም። በእያንዳንዱ ጊዜ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ ነገሮችን የምያደርግበትን መንገዱን ፈጽሞ አይለውጥም። ሁል ጊዜ ተመሳሳይ ነው፡ ምክንያቱም የእሱ የመጀመሪያ መንገድ ፍጹም የሆነ መንገድ ነው። ምክንያቱ፡ እሱ ሌላ መንገድ ሊኖረው አይችልም፡ ምክንያቱም እርሱ ፍጹም ነው፡ እና፡ እሱ፡ መንገዶቹ ሁሉ ፍጹም ናቸው። እንዴት እንዳደረገው ተመልከቱ።

54 ሙሴ የተ—የተቀበለውን ስራ ለመውሰድ፡ አስቀድሞ የተወሰነ እና የተጠራ ሰው ነበረ። እግዚአብሔር...

55 አሁን፡ እኔ እንደማስበው፡ ሁላችሁም ይቅርታ ካደርጋችሁልኝ... እና ይህን በችኮላ አልናገርም። እኔ በዚህ መድረክ ላይ፡ የምናገረው፡ ከእግዚአብሔር በቀር ምንም አላውቅም—ማወቅም አልፈልግም። አሁን፡ የላተር ረይን ወንድሞቻችን የተቀላቀለባቸው እዚህ ጋር ይመስለኛል፡ አያችሁ፡ እርስ በርሳቸው እጃቸውን ይጭናሉ እና ነቢያት ያደርጓቸዋል ወዘተ። አሁን፡ ያ

መጽሓፍ ቅዱሳዊ አይደለም። “ሰጦታዎች እና ጥሪዎች ያለ ንስሐ ናቸው።” የተወለድከው ምንም ይሁን ምን። በመጀመሪያ፡ ማንነታችሁ፡ እንዲሁ ናችሁ።

56 በጥንት ዘመን የነበሩትን ፈሪሳውያን ተመልከቱ። ትንሽ ብርሃን ነበራቸው፡ ምክንያቱም የሚችሉት… ሕግ ነበራቸው፡ በሕጉም ይኖሩ ነበር፡ ውስጠኛው ልባቸው ግን መሆን በሚችለው ሁሉ ጥቁር ነበር።

57 አንዲት ምስኪን ሴት፡ አመንዝራ፡ ሴትም ነበረች… **ከዚህ** በፊት-የነበራት ሕይወት በተቻለ መጠን ጥቁር ነበር፡ በመጥፎ-ትታወቅ ነበር፡ ነገር ግን በልቧ ውስጥ ለሕይወት አስቀድማ ተወሰና ነበር።

58 ከዚያም ኢየሱስ፡ ቃል የሆነው፡ ወደ ሰፍራው ሲመጣ፡ እነዚያ ፈሪሳውያን እንደዝህ አሉት፡ “ይህ ሰው ብዔልዜቡል ነው።” ምን አደረገ? የነበራቸውን ትንሽ ብርሃን አጨለመባቸው።

59 ኢየሱስም “እናንተ ከአባታችሁ፡ ከዲያብሎስ ናችሁ፡ ሥራውንም ትሠራላችሁ፡” አላቸው።

60 ይህች ምስኪን፡ የቆሸሸች ሴት ስትመጣ ግን፡ የእግዚአብሔርንም ቃል አይታ፡ አወቀችው። አልኖረችውም፡ ግን አውቃዋለች። ወዲያውም እንዳናገራት፡ “ነብይ እንደሆንክ አያለሁ፡” አለች። እርሱም… እንዲህ አለች፡ “መሲሁ ይህን እንደሚያደርግ አውቃለሁ።”

እርሱም “እኔ እሱ ነኝ፡” አላት።

61 ምን አደረገላት? ጥቁሩን ሁሉ አጽድቶ ሁሉንም ነጭ አድርጎላታል። ለምን? በውስጧ ያረፈ ዘር ነበረ፡ በውስጥ የኖረ አስቀድሞ የተወሰነ ዘር ነበር… ዓለም ሳይፈጠር በፊት የእግዚአብሔር ሐሳብ ነበር።

62 አንዲት የዘላለም ሕይወት ብቻ አለች። የዘላለም ሕይወት ካገኛችሁ፡ ዓለም ከመፈጠሩ በፊት እናንተ ራሳችሁ በእግዚአብሔር ሀሳብ ውስጥ ነበራችሁ። እናንተ የእሱ ሀሳብ ክፍል ናችሁ፡ ምክንያቱም ዘላለም ጅማሬ ወይም ፍጻሜ የለውምና። ሁሌም፡ የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ አካል ናችሁ። ነጸብራቅ ነው። አሁን እየሆነ ነው። የሚያጥቡት አንድ ተጨማሪ ምስል አላቸው፡ ያ ሞት ነው፡ ከዚያ አሉታዊው አዎንታዊ ይሆናል፡ እሱ እንዳሰበው፡ በሙሽራይቱ እና ከክርስቶስ ጋር ናችሁ። እንደ ባልና ሚስት፡ ዛሬም፡ እግዚአብሔር፡ ክርስቶስ እና ቤተ ክርስቲያን አንድ ይሆናሉ። አሁን፡ የተመረጡት፡ ተጠርተዋል!

ሙሴ ሲወለድ፡ “የተወደደ ልጅ ነበር።”

63 መጽሐፍ ቅዱስ፡ ከነቢያት ለአንዱ፡ ለኤርምያስ እንዲህ፡ ይለዋል፡ እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ “በእናትህ ሆድ ሳልሠራህ፡ ለዚህ ህዝብ ነቢይ አድርጌሃለሁ።”

64 መጥምቁ ዮሐንስ፡ እሱም፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ታወቀ። ከመምጣቱ ሰባት መቶ አሥራ ሁለት ዓመታት በፊት፡ ኢሳያስ፡ እንዲህ ብሎ ተናገረ፡ “‘የጌታን መንገድ አዘጋጁ!’ ብሎ በምድረ በዳ የሚጮኽ ሰው ድምፅ ነው፡” ከመገለጡም አራት መቶ ዓመታት በፊት፡ ሚልክያስ እንዲህ ሰል፡ ዳግም እናገኘዋለን፡ “እነሆ በእግዚአብሔር ፊት መንገድ ያዘጋጅ ዘንድ፡ መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ።”

65 እያችሁ፡ እርሱ አስቀድሞ ተወስኗል። እነዚያም ሁሉ የእግዚአብሔር አገልግሎቶች፡ በእግዚአብሔር ከተጠሩ እንዲሁ ነበሩ።

66 በመማር የደረሱ ከሆኑ፡ ፈንጅ ረጋጮች ብቻ ናቸው፡ እያችሁ፡ ምንም አይጠቅሙም። ስለ ፍርፋሪ ከሆነ፡ እንግዲያውስ ስለ ፍርፋሪ ብኩርናችሁን ትሸጣላችሁ፡ ከድርጅት ወይም ከአንዳንድ ቡድን ጋር ለመሄድ ታመቻምቻላችሁ። ከእግዚአብሔር ከሆነ ግን፡ ምንም ይሁን ምን፡ በዚያ ቃል ትቆማላችሁ፡ ምክንያቱም የተወለዳችሁት በእርሱ ለመቆም ነው።

67 ሙሴ፡ ሌላ ማንም ሊተካው አይችልም። ሌላ ማንም ሰው ሥራውን መሥራት አይችልም። እርሱ ያንን ለማድረግ የተሾመ ነው።

68 ወንድሞች፡ እና፡ እህቶች፡ የዘላለም ህይወት ካገኛችሁ፡ አንድ ነገር እንድትሰሩ ተሹማችኋል። ምናልባት ጥሩ የቤት እመቤት፡ ምናልባት ሌላ ነገር ትሆኛለሽ፡ ግን ማንም ሊተካሽ አይችልም። እግዚአብሔር ስፍራ አዘጋጅቶላችኋል። የሌላውን ሰው ቦታ ለመውሰድ አትሞክሩ፡ ያ ሥጋዊ ማስመሰል ነው፡ እያችሁ፡ በእናንተ ላይ የሆነ ችግር እንዳለ ያሳያል። ማን እንደሆናችሁ ሁኑ፡ ልክ እንደዛው ሁኑ። ሌላ ምንም አትሁኑ።

69 አሁን፡ አሁን እግዚአብሔር ሙሴን ጥያቄዎችን እና ጥሪዎችን ለማረጋገጥ ምልክቶችን እንደሰጠው ተረድተናል።

70 እና ማንኛውም እውነተኛ ምልክት፡ እያንዳንዱ እውነተኛ ምልክት፡ ከእግዚአብሔር የተላከ ነው፡ ከ... ከኋላው ድምፅ አለው። አሁን እያምልጣችሁ። ይህ የመጨረሻው ትምህርቴ ነው፡ እያችሁ። እያንዳንዱ እውነተኛ ምልክት... አሁን ከእግዚአብሔር ያልሆኑ ምልክቶች አሉ፤ ሰይጣን ያለውን ማንኛውንም ነገር ማስመሰል ይችላል። ነገር ግን ከእግዚአብሔር የተላከ፡ እውነተኛ ምልክት፡ ከኋላው የእግዚአብሔር ድምፅ አለ።

71 እግዚአብሔርም ሙሴን እንደዚህ አለው፡ "የመጀመሪያውን ምልክት ድምጽ ካላመኑ፡ ይህንን ሌላ ምልክት በፊታቸው አድርግ። እና ከዚያ ያንን ካልሰሙ፡ ውሃ ወስደህ መሬት ላይ እፍሰሰው።" ያ በገዛ ደማቸው ውስጥ እንደሚንከባለሉ ምልክት ነበር።

72 እስተውሉ፡ ልክ እሱ እንዳለውም፡ "ከእግራችሁ ላይ አቧራውን አራግፉ። በዚያ ቀን፡ ካልተቀበላችሁ ከተማ ይልቅ፡ ለሰዶምና ለገሞራ ይቀልላችኋል።"

73 አሁን የቤተ ክርስቲያን ጨዋታ **እየተጫወትን** አይደለም፡ ይህ ቤተክርስቲያን **ነው**። ቤተክርስቲያን ክርስቶስ ነው። በክርስቶስ ነን። ምስጢራዊው የክርስቶስ አካል ነው፡ የተወለድነውም በውስጡ ነው። አትቀላቀሉትምና።

74 ከብራንሃም ቤተሰብ ጋር ለሃምሳ-አምስት ዓመታት ያህል ቆይቻለሁ፡ ቤተሰቡን እንድቀላቀል ጠይቀውኝ አያውቁም። የተወለድኩት ብራንሃምን ሆኜ ነው።

75 እና ያ ክርስቲያን የሆናችሁበት መንገድ ነው። ክርስቲያን ሆናችሁ ተወለዳችሁ፡ እንጂ አልተቀላቀላችሁም። የተወለዳችሁት በውስጡ ነው። ሁሉም ሰው መወለድን ይፈራል። ትንሽ ካርድ ለመፈረም፡ ወይም ትንሽ ውሃና ጨው ለመበጥበጥ፡ እጅ አጨባበጥ አንዳንድ ጥሩ ንጹህ መንገዶች

አሏቸው። ያ ልደት አይደለም። መወለድ አስፈሪ ነገር ነው። ልደት አ—አስቃቂ ነገር ነው። በሚያስጠላ ቦታ ውስጥ ቢሆን ግድ የለኝም፡ ወ—ወይም በረት ውስጥ፡ ወይም በሮዝ ባጌጠ በሆስፒታል ክፍል ውስጥ ይገደኛም፡ መወለድ ምስቅልቅል ነው፡ እና ምስቅልቅላችሁን ያወጣችኋል። እናንተ መተው የማትፈልጉት፡ **ይህንን**፡ **ያንን**፡ ወይም **ሌላ** አትፈልጉም፡ በፊታችሁ ላይ ያለውን ቀለም ግን እንባው ያጥበዋል እና ሌላ ሰው ያደርጋችኋል። ዳግመኛ ከተወለዳችሁ፡ ከውስጣችሁ ቅሻሻን ያወጣል፡ ነገር ግን አዲስ ፍጥረት ትሆናላችሁ። አያችሁ? ያንን አይፈልጉትም። ሌላ ቀላል መንገድ ይፈልጋሉ፡ ታውቃላችሁ፡ እና ምንም ቀላል መንገዶች የሉም። መዝሙሩ፡ እንዲህ እንዳለ፡ “መንገዴን በጌታ ጋር ከተናቁ ከጥቂቶች ጋር አደርጋለሁ።” ችግኝ ጣቢያ መሆን አይፈልግም።

እያንዳንዱ እውነተኛ የእግዚአብሔር ምልክት በእግዚአብሔር ድምፀ ይታጀባል።

76 አንድ ሰው በአገር ውስጥ፡ ወይም በማንኛውም ጊዜ ምልክት ቢሰጥ፡ እና ያ ከኋላው የሚናገረው ድምጽ የእግዚአብሔር ቃል ካልሆነ፡ ተመልከቱ፡ አትመኑት። አንዳንድ የድሮ ነገሮች፡ አንድ ሰው ተነስቶ፡ የእግዚአብሔር ምልክት ቢያሳይ፡ የሰውዬው ትምህርትም በእነዚህ ሁሉ ዓመታት ውስጥ የነበራችሁበት ሥነ መለኮት ትምህርት ከሆነ፡ እግዚአብሔር ያንን ምልክት አልላከውም። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ መለሰ ብላችሁ ተመልከቱ እና እንደዛ እንደ ሆነ ተመልከቱ። ቅዱሳት መጻሕፍትን መርምሩ። ሰውዬው ተመልሶ፡ “አሁን ሁላችንም **ይህንን** መቀላቀል አለብን። የቆየ የተደራጀ ነውና፡” ይላችኋል። ያንን አትመኑት። በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ፡ ወደዚያ እንገባለን፡ አያችሁ። አይደለም፡ ያንን አትመኑ።

77 እግዚአብሔር ምልክቱን ሁል ጊዜ ያጸድቃል። የእግዚአብሔር ምልክት ሁል ጊዜ የእግዚአብሔርን ድምጽ ይናገራል።

78 እናንተም የነበራችሁት ተመሳሳይ የጥንቱ ትምህርት ከሆነ፡ ለምን ምልክት ይሰጣል? ቀድሞውኑ በእሱ ውስጥ ናችሁ። ወደዚያ ጠርዝ ሊያደርሳችሁ እየሞከረ ነው። ወደ እቁም! ቀስ በል! ወዴት እንደምትሄድ ተመልከት ምልክቶች! ካላስተዋላችሁ እራሳችሁን በሆነ ጠርዝ ላይ ትጥላላችሁ። ሹል ኩርባ አለ፡ ይህም ኩርባውን ከመታጠፋችሁ በፊት፡ እናንተ እንዳትሰበሩ የሚጠብቅ ምልክት ነው። ትክክለኛ የመንገድ ሰሪዎች ምልክቶችን ያስቀምጣሉ። እኛም ወደ ክብር መንገድ ጉዞ ላይ እንገንእለኝ። ምልክቱም ስለ አረጁ ነገሮች የሚናገር ከሆነ፡ ከእግዚአብሔር ዘንድ አይደለምም።

79 እግዚአብሔር የሕዝቡን ትኩረት ለመሳብ ምልክቶችን ይሰጣል። ምልክቶች የእግዚአብሔርን ሰዎች ትኩረት ለመሳብ ነው፡ የእግዚአብሔር ምልክቶች ናቸው። የእግዚአብሔር ምልክቶች የእግዚአብሔርን ሰዎች ትኩረት ለመሳብ የሚሰጡ ናቸው።

80 እዚህ ጋርም ይህ የሚቃጠለው ቁጥቋጦ ነቢዩን ትኩረት ለመሳብ የመጣ ምልክት፡ ነበረ፡ ነቢዩ ከእግዚአብሔር ፊት ሸሽቶ ነበርና፡ እግዚአብሔርም የሚቃጠለውን ቁጥቋጦ ለምልክትነት ሰጠው። ይህንም እንግዳ ምልክት አየ፡ እንዲህ አለ፡ “ቁጥቋጦው በ—በእሳት ተያይዟል፡ ልሂድና ቍጥቋጦው ስለ

ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ምልክት ልይ አለ።" አሁን እግዚአብሔር የሚሸሸውን ነቢይ ትኩረት ለመሳብ ነው። ሌላ ማግኘት ይችል ነበር፡ ነገር ግን ሙሴን ለሥራው ስለ ተሾመ ስፍራውም ሌላ ሊተካው አይችልምና።

81 በጉዞው ውስጥ፡ አንዳንድ ባልደረቦች ይህን ለማድረግ ሞክረው ነበር፡ ታውቃላችሁ። ዳታን ተነሳና ከዛ ውስጥ ድርጅት መፍጠር ፈለገ። እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነገረው፡ "እውጣቸዋለሁና። እራስህን ለይ።" አያችሁ?

82 እግዚአብሔር ከግለሰብ ጋር ይሠራል። አያችሁ? አሁን ይህንን አስተውሉ፡ የነቢዩን ትኩረት ለመሳብ፡ ነቢዩን በትክክለኛው ቦታው ለማምጣት እየሞከረ ነበር፡ አያችሁ፡ የሚነድድ-የቁጥቋጦ ምልክትን ሰጠ።

83 እና፡ ተመልከቱ፡ ምልክቱን ተከትሎ የመጣው ድምጽ መጽሓፍ ቅዱሳዊ ድምጽ ነበር። "ከአስገባሪዎቻቸውም የተነሣ፡ የሕዝቤን ጩኸት ሰማሁ፤ ሥቃያቸውንም አውቄአለሁ፡ ቃሌንም አሰብሁ።" አሜን። ደስ ይላል። "ቃል ኪዳኔን አሰብሁ።" መጽሓፍ ቅዱሳዊ ድምፅ ነበር። "አሁንም እልክሃለሁ። አሁንም ነጻ ላወጣቸው ወርጃለሁ፡ አንተንም እልክሃለሁ።"

84 አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ያለ ሰው ምንም አያደርግም። እናንተ ታውቃላችሁ? ህዝቡን የሚያደናቅፋቸውም ያ ነው። አያችሁ?

85 ስለ ኢየሱስ ያደናቀፋቸው ያ ነው። እንዲህ አሉ፡ "ሰው ስትሆን፡ እራስህን አምላክ እያደረግክ ነህ።" እሱ አምላክ ነበር፡ ሊረዱት ግን አልቻሉም። "እንዴ፡ አንተ'ኮ፡ ሰው ብቻ ነህ።"

86 እርሱም እንዲህ አለ፡ "መልካም፡ እናንተ ራሳችሁ ነቢያትን፡ 'አማልክት፡' ትላላችሁ እና ሕጋችሁም ይደግፈዋል። የእግዚአብሔር ቃል የሚመጣላቸው፡ 'አማልክት' ብላችህ ብትጠሯቸው፡ እኔን የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ ስላልኩ እንዴት ትኮንኑኛላችሁ? "

87 አያችሁ፡ ምልክቶች፡ ትኩረትን ለመሳብ ናቸው። እና፡ አስታውሱ፡ ትኩረት ከሳበ በኋላ ተመሳሳይ የድሮ መስመር ከሆነ፡ ከእግዚአብሔር አይደለም።

88 አሁን ግን እግዚአብሔር ነቢዩን ለመሳብ እየሞከረ ነው፡ ምልክትም ሰጠው፡ ምልክቱም የተከተለው ድምፅ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ድምፅ ነበር። "ህዝቡን አይቻለሁ። ማልቀሳቸውን ሰምቻለሁ። ቃል ኪዳኔን አስቤአለሁ።"

89 አሁን እግዚአብሔር በተሰፋ ቃሉ ሊናገር ነው። ቃሉ ወደ ነቢዩ ይመጣልና፡ ነብዩን መላክ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንዲህ ይላል፡ እግዚአብሔር ራሱ፡ እንዲህ አለ፡ "አስቀድሞ ለባሪያዎቹ ለነቢያት ሳይገልጥ ምንም አያደርግም።" አያችሁ? እና ከዚያ፡ ምልክቱ ተሰጥቶ፡ ቅዱሳት መጻሕፍት ጋር ከተመሳሰለ፡ ያ የምልክቱ ድምጽ ነው።

90 የሙሴን፡ የምልክቱን ድምፅ አያችሁት? በመጀመሪያ፡ ምልክቱ የሚቃጠል ቁጥቋጦ ነበር፡ ድምፁም ከቅዱሳት መጻሕፍት ነበሩ።

91 ሙሴም ያንን ምልክት ይዞ ወደ ግብፅ ወረደ፡ እግዚአብሔርም የነገረውን ምልክት አደረገ፡ ምልክቱም ለራሱ ድምፅ ነበረው፡ ሰዎቹም አምነው ወጡ። ጉዞ እስኪያደርጉ ድረስ፡ ጥሩ አደረጉ፡ በድምፁ ላይ ማጉረምረም ሲጀምሩ ግን፡ ያኔ ቆሙ።

92 አስታውሱ፡ እስራኤልም ተጓዙ። የተጓዙትን ርቀት ልኩን ታውቃላችሁ? እነርሱ የተጓዙት... አርባ ማይል ብቻ ነበር፡ ለአርባ ዓመታት ያህል ይዞሩ ነበር። ለምን? ምልክቱን ባወጣው ድምጽ ላይ ማጉረምረም ስለጀመሩ ነው። ዳርቻው ዳር ሲጮሁ፡ እና በመንፈስ ሲጨፍሩ፡ ምን ያህል ትንሽ ያውቁ ነበር፡ ሙሴም በመንፈስ እየዘመረ፡ ለጥቂት ቀናት ብቻ ቆዩ። በኋላ ግን ማጉረምረም ጀመሩ፡ እና የተለየ ነገር ለማድረግ ፈለጉ፡ ለአርባ አመታት በምድረ በዳ ቆዩ፡ በዚያው ጠፉ፡ ይህም ስላላመኑበት ነው፡ ትክክል ነው። እግዚአብሔር እንዲህ አለ፡ “ሙሴ ሆይ፡ የተቃወሙት አንተን አይደለም፡ የተቃወሙኝ እኔን ነው።” ያ የእግዚአብሔር ድምፅ እንጂ፡ የሙሴ አልነበረም።

93 አሁን ተመልከቱ፡ ያህዌ በተሰፋ ቃሉ ስለሚናገር፡ ነቢያትን ግዴታ ይልካል። ያንን፡ ማየት ከፈለጋችሁ፡ ያ በዘፍጥረት 15፡16 ላይ ታገኙታላችሁ። እግዚአብሔር ለአብርሃም እንደነገረው እናስተውላለን፡ “ዘርህ በዚህች ባዕድ አገር ውስጥ ይኖራል፡ እኔም በበረታች ክንድ አወጣቸዋለሁ። የአሞራውያን በደል ገና አልተፈጸመም።” የሚሰጣቸው የተሰፋ ቃላቶቹ ሁሉ፡ እዚህ በሚነድ ቁጥቋጦ፡ ነቢዩን እየሳበ ነው።

94 አሁን የሚቃጠለው ቁጥቋጦ ቢናገር ኖሮ፡ “ሙሴ፡ እግዚአብሔር እግዚአብሔር ነው።”

“አዎን፡ አምናለሁ።”

95 “ኦህ፡ ሙሴ ሆይ፡ ጥሩ እየሰራህ ነው፡ ዝም ብለህ ቀጥልበት። ጥሩ ሴት አግብተሃል፡ ቆንጆ ነች። በእርግጥ ጥሩ ልጅ አለህ! ክብር ለእግዚአብሔር!” ያ ያው ያረጀ ትምህርት ነው። አያችሁ?

96 አንድ ነገር ለማድረግ ስለተዘጋጀ ግን፡ ሰውየውን መሳብ ነበረበት። ለዚያም ሰው የሚሰራባቸው ሁለት ምልክቶችን ሰጠው፡ እና እንዲህም አለው፡ “እያንዳንዱ ምልክት ድምፅ ነበረው።” ያም እንደዚያ መሆኑን ያረጋግጣል። አሁን ድምጾቹ፡ ማለት ፍጥረትን ሳይቀር መናገራቸውን አስቡ። ያህዌ አሁንም ለመናገር ተዘጋጅቷል።

97 አሁንም፡ የነቢዩ መምጣት ምልክት ነው። ይህን ታውቃላችሁ? የነቢይ መምጣት፡ ለዘመናት፡ ምልክት ነው።

98 አሁን፡ ስለ ሰነመለኮት ዶክተር ማለቴ አይደለም። ወይም ታማኝ ፓስተር፡ የሆነ ጥሩ ሰው ማለቴ አይደለም። እነሱ ይሁኑ። የእግዚኣብሔር ባሪያዎች ናቸው።

99 ነቢይ ግን ምልክት ነው። መጽሐፍ ቅዱስም እንዲሁ ይላልና። እና ምልክቱ ምንድን ነው? በዚህ ነቢይ ምልክቱ ድምፅ ይፈጸም ዘንድ፡ ቃሉ የሚፈጸምበት ምልክት ነው።

100 አስተውሉ፡ የነቢይ መምጣት የተቃረበ የፍርድ ምልክት ነው። ያንን ታውቃላችሁ? በምድር ላይ ነቢይ ካለ ፍርዱ ለመምጣት ዝግጁ ነው።

101 በመጀመሪያ፡ ለዚያ ቀን በእግዚአብሔርና በቃሉ፡ መረጋገጥ እንዳለበት፡ አስታውሱ፡ ከዚያም ምልክቱን ያደርጋል። እና ከዚያ ያንን ምልክት ምን እንደሚተነብይ፡ ተመልከቱ። እንደዝህ አለ፡ “ከተፈጸመ፡ እርሱን ሰሙት።” ኦሪት

ዘኍልቍ 12፡6፡ “ካልተፈጸመ፡ እርሱት።” እሱ የሚሰጠው መጽሓፍ ቅዱሳዊ ምልክት መሆን አለበት።

102 አንድ ጊዜ፡ ለምልክትም የሚሰጠውን፡ ትላንትናምል፡ ዛሬም፡ ለዘላለምም ያው ከሆነ፡ ደጋግሞ ይሰጠዋል። “የጌታ ቃል ወደ ነቢያት ይመጣል።” እነሱ ቃል ነበሩ። ኢየሱስም ሲመጣ፡ ቃል ነበር። ቃሉም የልብን አሳብ እና ፍላጎት፡ ያለማቋረጥ፡ ያለማቋረጥ ያውቃል። አሁን ተመልከቱ።

103 የዚህ ነቢይ መምጣት፡ ሁል ጊዜ፡ “ፍርድ በቅርብ ነው፡” የሚል ምልክት፡ ይሰጣል።

104 ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ እንጨርሳለን፡ ብዙ ጊዜ አልወሰድም። አሁን ለአሥር ደቂቃ ያህል፡ የተወሰነ እንፈትሽ። እና የቀረውን መልእክት፡ ይልቁንም፡ ለአሰር ደቂቃዎች።

105 ኖህ፡ በምድሪቱ ላይ—በምድሪቱ የነበረ ነብይ፡ የሚመጣው ፍርድ ምልክት ነበር። ሙሴ፡ በምድሪቱ ላይ ለሚመጣው ፍርድ፡ ምልክት የነበረ ነብይ ነው። ኤልያስ፡ በምድሪቱ ላይ ለሚመጣው ፍርድ፡ ምልክት የነበረ ነብይ ነው። ዮሐንስ፡ በምድሪቱ ላይ ለሚመጣው ፍርድ፡ ምልክት የነበረ ነብይ ነበር፡ እነርሱም ፈጽመው ተቆረጡ።

106 አስተውሉ፡ ምልክት! ምልክቱ ምን ያደርጋል? ምልክቱ ትኩረቱን ለመሳብ፡ እና የተመረጠውን ዝግጁ ለማድረግ፡ እና ፍርድ ከመምጣቱ በፊት ከመንገድ ለማውጣት ነው። ኖህ ያደረገው ይህንኑ ነው፡ የተመረጡትን አዘጋጅቷል። ሌሎቹም እንዲሁ፡ ምን ያደርጋል? ምልክቱ፡ እና የምልክቱን ድምጽ፡ ያላመነውን ያወግዛል እናም ለፍርድ ያዘጋጃል። የተመረጠውን ለማምለጥ ያዘጋጃል። ያ ምልክት ነው። ለሚመጣው ፍርድ፡ ለዚያ ምልክቶች ተሰጥተዋል። የተመረጡት፡ ያዩታል።

107 ንጹሕ ልብ፡ እና የረከሰ አካል እንደነበራት ምስኪኗ ሴት፡ እና ንጹሕ ሥጋና፡ የረከሰ ልብ የነበረው ፈሪሳዊ አይነቶች። አንዱን ይኮንናል፡ ሌላውን ያድናል።

108 ሙሴን ያዳኑት ያው ፍርዶችም፡ ማለት ሰብከቶቹ፡ ዓለምን የኰነኑ እነሱ ናቸው።

109 የተመረጡትን ያዘጋጃል። የተመረጡት ለምን ይዘጋጃሉ? በእግዚአብሔር-የተላከ ምልክት ሲያዩ፡ ወደ ኋላ ወደ ቅዱሳት መጻሕፍት ይመለከታሉ እና ያ እዚያ መሆን እንዳለበት ያያሉ። “አዎ፡ ይኸው።” ምንድነው ይሄ? ፍርድ በመጠባበቅ ላይ። ከዚያም የተመረጡ ሰዎች ድምፁን ያዳምጣሉ።

110 ያልተመረጡት ግን ችላ ብለው፡ እንዲህ ይላሉ፡ “የማይረባ ነው። ቀጥል! ተመሳሳይ የድሮ ነገራችን ይሻለናል።” አያችሁ? በሉተር ዘመን ያደርጉት የነበረው መንገድ ያ ነው። በዌስሊ ዘመን ያደርጉት የነበረው መንገድ ያ ነው። እንደዚያው ነው—ያኔም እንዳደረጉት፡ አሁንም ያደርጋሉ።

111 ነገር ግን ምልክት ነው፡ ምልክቱም የሚከተል ድምጽ አለው፡ ድምፁ ደግሞ መጽሓፍ ቅዱሳዊ ድምፅ እንደሆነ ይታወቃል። አሁን ያንን አትርሱ፡ አሁን ያንን ወደ ውስጥ መሄዳችሁን ቀጥሉበት፡ ዳግመኛ ላላያችሁ እችላለሁና።

112 ወደዚህ ቦታ ወርጄ ሁሉንም ወንድሞቼን የማገኝበት መንገድ ባገኝ ምኞቴ ነበር፡ ሪቫይቫል በሌለባቸው ጊዜ፡ ድንኳን ተክዬ፡ ከቀን ወደ ቀን በተቀመጥኩ፡ በእውነቱ እስኪገባቸው ድረስ—ድረስ ባስተማርኳቸው። እሱ አይፈቅድም እንጂ፡ አይመስለኝም። አያችሁ፡ ወደ መጨረሻው በጣም ቀርበናል። አሁን መጨረሻ ላይ ነን ብዬ አምናለሁ።

113 በዚያ በመጽሐፌ ውስጥ፡ ደጋግሜ ጽፌ ነበር። በ1933፡ አንድ ቀን ጠዋት፡ ፓስተር ወደ ነበርኩበት የባፕቲስት ሰንበት ትምህርት ቤት፡ ወደ ሰንበት ትምህርት ቤት ልሄድ ስል፡ መንፈስ ቅዱስ መጥቶ እስከ ፍጻሜው ዘመን አሳየኝ፡ እናም የሚፈጸሙትን ሰባት ነገሮችን አሳየኝ። ምልክት አደረግኳቸው። ባረጀች ቢጫ ወረቀት ላይ ነው።

114 ጀርመን ያንን የሲግፍሪድ ምሽግ እንዴት እንደምትገነባ ነገረኝ፡ እና አሜሪካኖች እንዴት ታላቅ ድብደባ እንደሚያደርጉበት፡ ምሽጉ የተሰራው—ከአስራ አንድ አመት በፊት ነበር።

115 ሙሶሎኒ እንዴት እንደሚነሳ፡ ወደ ኢትዮጵያ እንዴት እንደሚሄድ፡ እና ኢትዮጵያ እንዴት "ከሰሩ እንደምትወድቅ፡" ተናግሬአለሁ። በተቃራኒው፡ በአፍረት እንደሚሞት፡ የገዛ ወገኖቹም እንደሚተፉበት።

116 እንዲህም አልኩ፡ "ኮሚኒዝም፡ ፋሺሲዝም፡ እና ናዚሲዝም፡ የሚባሉ ሶስት ኢዝሞች ይነሣሉ። ሁሉም በኮሚኒዝም፡ በሩሲያ ውስጥ ይዋጣሉ።" ካት-... ካቶሊካዊነትን ያጠፋል። ካልሆነ ታያላችሁ!

117 እንዲህ አልኩ፡ "እንዲህ ዓይነት እድገት ይሆናል!" እንዲህ አልኩ፡ "እንቁላል የሚመስሉ አውቶሞቢሎች፡ መንገድ ላይ ሲሽከረከሩ አየሁ። የሆነ መቆጣጠሪያ ያላቸው፡ በአውራ ጎዳናዎች ላይ የሚሽከረከሩ መኪኖች አሉ፡ አሽከርካሪ አያስፈልጋቸውም። አሜሪካዊ ቤተሰብ ከመኪናው ጀርባ ቼከር ሲጫወት አይቻለሁ።" መኪናውን የሚነዱበት አውራ ጎዳናዎች ከሰሩ፡ አሁን መኪናውን ሰርተውታል። ትንሿ ቮልስዋገን ፍጹም እንቁላል ቅርጽ ናት፡ በትክክል፡ እና ሁሉም ሌሎች መኪናዎች እንደዛ ናቸው። በ 1933፡ መኪኖቹ ምን እንደሚመስሉ፡ መገመት፡ ትችላላችሁ?

118 ከዚያ በኋላም፡ ሴቶች፡ ምርጫ ላይ እንደሚሳተፉ እና ምን እንደሚያደርጉ፡ በትንቢት ተናግሬአለሁ። እና ይህች አገር፡ እንደ እስራኤል፡ ምሳሌ ሆና፡ ወደ ምድሪቱ መጥተው፡ የተቀመጡባትን አሳድደው፡ ምድሪቱንም ወረሱ። የነበሯቸው የመጀመሪያዎቹ ነገሥታት፡ እነ ዳዊትና ሰሎሞን፡ እግዚአብሔርን-የሚፈሩ ነገሥታት ነበሩ። ከጥቂት ጊዜ በኋላ፡ አክዓብ ዙፋን ላይ መጣ። መረጡት። ወንበሩ... ቤተ ክርስቲያን ዓለማዊ ሆነች። እና፡ እኛም ሊንከን እና ዋሽንግተን ነበሩን፡ ዛሬ ምን እንደሆነ ተመልከቱ። አሁን ወዴት እንደምንሄድ ተመልከቱ። የሚቀጥለው ነገር የት ነው? በመጨረሻው ሰዓት ላይ ነን።

119 እና በተፈጥሮ፡ በትክክል፡ ምልክት ነው። የተመረጠውን ያዘጋጃል፡ የማያምኑትን፡ ለፍርድ፡ ይኮንናል።

120 "ይህ ነቢይ እውነተኛ ነቢይ ከሆነ፡ እና የተናገረው ነገር የሚፈጸም ከሆነ፡" መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዘኍልቁ 12፡6፡ "ከሰው እንዳልሆነ ተረጋግጧልና፡ ማስጠንቀቂያውን ስሙት።" ነብዩ—ሰው ነውና። ነገር ግን ከተፈጥሮ

በላይ ከሆነው ምልክት የሚመጣው ድምጽ መጽሓፍ ቅዱሳዊ ድምጽ ነው፡ የተረጋገጠ ነው፡ እንደዝያ ከሆነ ማስጠንቀቂያ ነው።

121 መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው በነቢያት ነው፡ አስታውሱ። በሁለተኛ ጴጥሮስ፡ 1፡21። በዕብራውያን 1፡1፡ ላይም፡ እንዲሁ።

122 የእሳቱ ዓምድ፡ ለሙሴ፡ ሊናገረው ላለው ድምጽ፡ ምልክቱ ነበር። የእሳቱ ዓምድ ድምፁ ሊናገር እንደሆነ ያሳያል። ይህ የእሳቱ አምድም፡ ምልክቱ ነው። እናንተ ሰዎችም፡ ይህ የቅርብ ጊዜ የሂዩስተን ትዝታችሁ ነው።

123 ነብዩ፡ ሙሴ፡ የተሰፋው ቃል ሊፈጸም መቃረቡን፡ ለእስራኤል ገለጸ። ሙሴ ወርዶ የነቢይን ምልክት ባደረገ ጊዜ፡ በዚያን ጊዜ አንድ ላይ እንደሚሰበሰባቸው አወቁ።

124 የእግዚአብሔር ቃል በሥርዓት ምን ያህል ፍጹም ነው፡ በእያንዳንዱ ጊዜ ተመሳሳይ ነው። ባለፈው ምሽት እንደተናገርኩት፡ ኡሪም ቱሚም፡ እና ሁሉም ነገር፡ እንኳን እንዴት ሁልጊዜ ለእግዚአብሔር መልስ እንደሰጡ ብያለው።

125 እንደገና ለአፍታ ያህል፡ ነቢይ ዮናስን፡ እንውሰድ። የዮናስ 1ኛ ምዕራፍ እዚህ ተጽፎ ይገኛል ከትንቢቱ፡ 1ኛ ምዕራፍ። ዮናስ ከዓሣ አንበሪ ሆድ የወጣው፡ ምልክት ነበር። እያችሁ፡ ሰዎቹ አረማውያን ነበሩ። የባሕር አማልክትን ያመልኩ ነበር፡ እና የባህር-አምላካቸው ዓሣ አንበሪ ነበር።

126 አሁን ብዙ ሰዎች ዮናስን ለመኮነን ይሞክራሉ። እኔ ሁልጊዜ ዮናስን ነበር የምደግፈው። ዮናስ ከጌታ ፈቃድ አልወጣም። "የጻድቃን አካሄድ በእግዚአብሔር የታዘዘ ነው።" እንዲህ ማለት እንፈልጋለን፡ "ዮናስ ነው።" ምን ዋጋ እንዳለው፡ ለአንድ ጊዜ... በእሱ ላይ ብቻ እንውሰድ። ወደ ነነዌ መሄድ እንዳለበት አውቃለሁ፡ ነገር ግን እግዚአብሔር ያንን መርከብ ወደ ተርሴስ እንዲወስድ አደረገው። እናም በባህር ላይ ችግር እንዲሆን አደረገ።

127 ዮናስም እንዲህ አለ፡ "እጆቼንና እግሮቼን እሰሩ። በችግር ውስጥ ያለሁት እኔ ነኝ፡ ችግሩን ያመጣሁት እኔ ነኝ።" ወደ ውጭም ጣሉት። ዮናስን የዋጠው ትልቅ ዓሣ፡ በውኃ ውስጥ ይዋኝ ነበር። ለሳይንስ ለማመን ከባድ እንደሆነ አውቃለሁ።

128 እዚህ ቅርብ ጊዜ፡ በሉዊቪል፡ ኬንታኪ፡ ከአሥር ዓመታት በፊት ገደማ፡ አንድ—አንድ ዓሣ አንበሪ በ—በ ጠፍጣፋ መጫኛ ላይ አመጡ። እና በዚያም እንዴት መቆጣጠር እንዳለበት የሚያውቅ፡ አንድ ሾካካ ሰው ነበረ። መጽሐፍ ቅዱስ ውሸት እንደተናገረ ለማስመሰል እየሞከረ ነበር። እንዲህ አለ፡ "ታውቃላችሁ፡ ያንን የቀደመው የመጽሐፍ ቅዱስ ተረት፡ ዮናስን ዓሳ አንበሪ እንደ ዋጠው ሲናገር ሰምታችኋል።" እንዲህ አለ፡ "ተመልከቱ፡ ጉሮሮው እጅግ ጠባብ ከመሆኑ የተነሣ፡ ኳስ እንኳን ማሳለፍ አትችሉም። አቅመ-አዳም የደረሰ ሰው እንዴት ወደ ሆዱ ውስጥ ይገባል?" እንዲህ አለ፡ "እያችሁ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ባሉ ነገሮች የተሞላ፡ የድሮ ተረት ነው።"

129 ያ እኔ—አስተሳሰብ በጣም ሰለከበደኝ። እንዲህ ኣልኩት፡ "ዎዳጄ፡ የሆነ ነገር ማለት እፈልጋለሁ።"

አለኝም፡ "ምን ማለት ትፈልጋለህ?"

130 እንዲህ አልኩት፡ “እየህ፡ መጽሐፍ ቅዱስን በትክክል አላነበብክም።” እንዲህ አልኩት፡ “መጽሐፍ ቅዱስ ልዩ ዓሣ ነባሪ ነው ይላል። ‘እግዚአብሔር ትልቅ ዓሣ አዘጋጀ።’ ይህ በልዩነት የተፈጠረ፡ እሱ እንዳደረገ፡ እሱን ለመዋጥ! አንድ ተራ ዓሣ አልነበረም። እግዚአብሔር እንግዳ ሥራ ሊሠራ ነበር፡ ስለዚህ እንግዳ ዓሣ አገኘ።” እየህ? ከዚያ በኋላ ስለ እሱ ምንም አይናገርም። ስለዚህ፡ እግዚአብሔር የተለየ፡ ነገር ነበረው።

131 ልክ እንደ ምስኪኗ ልጅ፡ አንድ ጊዜ፡ ከጸሎት ቤት እንደመጣች፣ ፊቷ የተላጠ ሽንኩርት እስኪመስል ድረስ፡ ትንሿ ፀጉሯ ወደ ኋላ ለጥ አርጋ፡ በደንብ አበጥራዋለች። መጽሐፍ ቅዱስ ይዛ፡ ወደ ታች እየወረደች ነበር።

132 ይህ ጂም ዶርሲ የተባለ ሽማግሌ በኡቲካ ይኖር ነበር። እሱ ወታደር የነበረ ሽማግሌ፡ እምነት አልባ ነበር፡ እና—በእግዚአብሔርም አያምንም ነበር። እርሱም “የት እየሄድሽ ነው፡ አንቺ ወጣት ሴት፡” ብሎ ጠየቃት?

አሷም “ወደ ቤት እየሄድኩ ነው፡ ዎዳጄ፡” አለችው።

እንዲህ አላት፡ “በክንድሽ ውስጥ የያዝሽው ምንድነው? ”

“መጽሐፍ ቅዱስ ነው፡” አለችው።

እንዲህ አላት፡ “ያንን አታምኚም፡ አይደል? ” እና...

“አዎ፡ እምናለው፡ ዎዳጄ፡” አለችው።

133 እና “ዮናስን ስለዋጠው ዓሳ አንበሪው ታሪክ ታምኚያለሽን” ብሎ ጠየቃት?

“እንዴታ፡ እያንዳንዱን ቃል፡ በደንብ አምናለሁ፡” አለችው።

134 እንዲህ አላት፡ “እምነት ከምትሉት ነገር፡ ከእምነት ሌላ ምን ማረጋገጫ አለሽ? ”

“እንዴ፡” አለችው፡ “ገነት ስደርስ፡ ዮናስን እጠይቀዋለሁ።” አያችሁ?

“እዚያ እሱ ከሌለስ፡” ብሎ ጠየቃት?

135 እሷም “እንግዲያውስ አንተ ትጠይቀዋለህ፡” አለችው። በጣም ጥሩ ማቅናት ነው ብዬ አስባለሁ። ስለዚህ ያ ትክክል ነው ብዬ አስባለሁ።

136 መጽሐፍ ቅዱስ ዮናስ ዓሣ ነባሪውን እንደዋጠው ቢናገር፡ አምናለሁ። ሊያዘጋጅ ይችላል። እግዚአብሔር የተናገረውን፡ ሁሉ ማድረግ ይችላል፡ እና ሁልጊዜ ቃሉን ይጠብቃል። ስለዚህ፡ በዮናስ፡ እንኳለቅበት ነበር...

137 ግን አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? ዓሳ በሚዋኝበት ጊዜ፡ ምግቡን ያድናል። እና ከዚያ ሲበላ፡ ወደ ታች ይወርዳል እና ትንንሾቹን ዋናዎቹን ከታች ያደርጋል። ወርቃማ ዓሣን መግቡት እና የሚሆነውን ተመልከቱ። ትንሽ ሆዳቸውን ይሞላሉ፡ ከዚያም ወደ ታች ወርደው መዋኛዎችን በትክክል ከታች ያስቀምጧቸዋል፡ እና እዚያ ይተኛል እና ያርፋል።

138 መልካም፡ ይህ ትልቅ የተዘጋጀ ዓሣ መጥቶ ይህን ነቢይ ዋጠው። ወደ ባሕሩም ታች ወረደ፡ ምናልባት አርባ ፊት በጥልቁ ገባ። በባሕሩ ግርጌ ላይ፡ ለማረፍ ወደ ታች ወረደ።

139 አሁን ስለ ዮናስ ሁልጊዜ እናስባለን። እና ሁሉም ሰዎች እንዲህ ይላሉ፡ “አሁን ጸለይኩኝ፡ ግን እጄ አልተሻለኝም። ጸለይኩኝ፡ ነገር ግን ምንም የተሻለ ስሜት አይሰማኝም።” በዮናስ ላይ ፈጽሞ እንዳትጮሁ።

140 አሁን የሱን ምልክቶችን ተመልከት። አሁን፡ በመጀመሪያ፡ በማዕበል የተሞላ ባህር ላይ ነበር፡ እና እግዚአብሔር ከላከው መንገድ ወጣ። እጆቹና እግሮቹ ታሰረው ነበር። ማዕበል ወዳለበት፡ ወደሚናወጥ ባህር ተጣለ፡ እና ዓሣ አንበሪ ዋጠው እና ከባህሩ በታች ተኛ። እና በአሳ አንበሪ ሆድ ውስጥ፡ በትውከቱ ውስጥ፡ አንገቱ ላይ የባህር አረም ዙርያ ተኳቷል። እና **ይህን** መንገድ ቢመለከት፡ የዓሣ አንበሪ ሆድ ነው። እሱ **በዚያ** መንገድ ብመለከት፡ የዓሣ አንበሪ ሆድ ነበር። ያየበት ቦታ ሁሉ፡ የዓሣ አንበሪ ሆድ ነበር። ስለ ሕመሙ ምልክቶች ታወራላችሁ፡ እሱ ሊኖረው ይችላል። ግን ምን እንዳለ ታውቃላችሁ? እንዲህ አለ፡ “ውሸታም ከንቱዎች ናቸው። ዳግመኛ አላያቸውም፡ ነገር ግን አንድ ጊዜ ወደ ቅዱስ መቅደስህ እመለከታለሁ።”

141 ፍጥረታዊው፡ የምድር፡ ሰው ሰሎሞን፡ መቅደሰን ሲቀድስ ጸለየ፡ እንዲህ አለ፡ “ጌታ ሆይ፡ ህዝቦችህ በየትኛውም ቦታ ቢቸገሩ፡ እና ወደዚህ ቅዱስ ሰፍራ ቢመለከቱ፡ ከሰማይ ሰማቸው።”

142 ዮናሰም ሰሎሞን በጸለየው ነገር አመነ። እግዚአብሔርም ከዓሣ አንበሪ፡ ከሦስት ቀንና ሌሊት በኋላ አወጣው። የኦክሰጅን ቱቦ እዚያ አሰቀምጦ ሊሆን ይችላል። ያደረገውን አላውቅም፡ ነገር ግን ቃሉ እንደሚለው፡ ለሦስት ቀንና ለሊት በሕይወት አኖረው። ቃሉም ትክክል ነው።

143 መልካም፡ ዮናስ፡ በእነዚያ ሁኔታዎች ውስጥ፡ አንድ ሰው ወደሠራው መቅደሰ እንደገና ከተመለከተ፡ እኔና እናንተ ዛሬ ማታ፡ ኢየሱስ በግርማው ቀኝ ቆሞ ወደተቀመጠበት ቤተ መቅደሰ ልንመለከት፡ ምን ያህል ያሰፈልገናል፡ በትንንሽ ምልክቶቻችን፡ በኑዛዜአችን፡ በገዛ ደሙ፡ ማለደልን! ዮናሰን አትኮንኑት፡ ከዚያም በእናንተ ላይ ምን ችግር እንዳለባችሁ ተመልከቱ። ተሰፋውን ተመልከት፡ “እግዚአብሔር ያንን ብሏል!” የአብርሃም ልጆች ከሆናችሁ፡ “እግዚአብሔር ያንን ብሏል!” እሱ ራሱ ቃል ይገባል፡ ያደርገዋል።

144 አስተውሉ፡ ሰዎች ሁሉ ዓሣ ለማጥመድ፡ መረባቸውን እና ዕቃቸውን እየጎተቱ ነበር። ድንገትም፡ የባህር-አምላክ፡ ዓሳ አንበሪ፡ ወደ ውሃው ዳር በፍጥነት መጣ። ሁሉም በጉልበታቸው ወደቁ። እግዚአብሔር ነገሮችን እንዴት እንደሚሰራ ያውቃል። ወዲያውም ወደ ውሃ ዳር ደረሰና ምላሱን አወጣ፡ እና፡ ያንን ባደረገ ጊዜ፡ ከዓሣ ነባሪ አፍ ውስጥ እየተራመደ ነቢዩ ወጣ። ነቢዩ! እግዚአብሔር ነቢዩን በውሃው ዳር ላይ ተፋው። ንስሐ መግባታቸው አያስገርምም። አያችሁ?

145 ያ ምልክት ነበር። ዮናስ ከአሳ አንበሪ መውጣቱ፡ ምልክት ነበር። ምን አደረገ? ይህም ከእግዚአብሔር ዘንድ ምልክት ነበር። ድምፁ ምን አለ? “በአርባ ቀን ውስጥ፡ ንስሃ ግቡ ወይም ትጠፋላችሁ።” የእግዚአብሔር ምልክት፡ የእግዚአብሔር ድምፅ! ሁል ጊዜ፡ እግዚአብሔር ምልክት ሲልክ፡ እግዚአብሔር ድምፁን ከዚያ ምልክት ጀርባ ይልካል። አስተውሉ፡ “ንስሐ ግቡ፡ አለዚያ በአርባ ቀን ውስጥ ይህች ከተማ ሁሉ ትጠፋለች።”

146 ያለ ነቢይ በምድር ላይ፡ ከአራት መቶ ዓመታት በኋላ የነቢዩ ዮሐንስ ሲገለጥ፣ ምልክቱም ከአራት መቶ ዓመት በኋላ፡ ታየ። ያ ትንሽ የእረፍት ጊዜ!

147 አሁን መንፈሳዊ ከሆናችሁ የምናገረውን ትረዳላችሁ። እግዚአብሔር ማስተዋላችሁን ይክፈትላችሁ። ምን ያህል ጊዜ ቆይቷል?

148 አራት መቶ ዓመታት፡ እስራኤል ያለ ነቢይ፡ አብያተ ክርስቲያናት በጣም ተጣመሙ፡ በዚህ ሁኔታ መካከል ዮሐንስ መጣ። ዮሐንስ ነቢይ ነበር፡ ይህም መሲህ ከእርሱ በኋላ እንደሚናገር የሚያሳይ ምልክት ነው። ተመልከቱ። ምክንያቱም፡ ሚልክያስ 3፡ "መንገዱን ያዘጋጅ ዘንድ፡ እኛ ሰዎችን ያዘጋጅ ዘንድ፡ መልእክተኛዬን በፊቴ እልካለሁ።"

149 ዮሐንስን ተመልከቱ፡ በእርሱ ውስጥ ራስ ወዳድነት የለም። ምንም ክብር አልወሰደም። መሲህ ብለው ሊጠሩት ሞከሩ፡ እርሱ ግን "ጫማውን ልፈታ ብቁ አይደለሁም፡" አለ።

150 ነገር ግን ኢየሱስ በተገለጠ ጊዜ፡ ምልክት ነበረው፡ የእሳት ዓምድ፡ ከላይ ብርሃን ነበረው፡ እንደ ርግብም ድምፅ ወረደ እንድህ እያለ፡ "በእርሱ ደስ የሚለኝ፡ የምወደው ልጄ ይህ ነው።"

151 አስተውሉ፡ ዮሐንስም ወዲያው እንዲህ አለ፡ "እርሱ ሊልቅ። እኔ ላንስ ያስፈልጋል።" ቤተክርስቲያንን ለክርስቶስ አቀረባት። አሜን።

152 በመጨረሻው ቀን፡ ይህ እንደገና እንደሚደገም፡ ተነግሮናል! መሲሁን ለሰዎች የሚያስተዋውቅ፡ መልእክት ይመጣል። እና እንደዚህ አይነት መንገድ ይሆናል፡ ያኔ እንዳረጉት በድፍረት ይቃወማሉ። ቃል ገብቷል እሱ። የማቴዎስ፡ ማለት የሚልክያስ ተከታይ ምዕራፍ፡ ስለ ጉዳዩ ይነግረናል። ተመልከቱ።

153 ስለ እሱ ጠየቁት። የዮሐንስ ባህርያት ራሱን በኤልያስ መንፈስ ለይቷል። አሁን ሁለቱንም ነቢያት አስተውሏቸው።

154 አሁን፡ ኤልያስ በእስራኤል ጊዜ፡ በሁከት ውስጥ የተነሣ ሰው ነበር።

155 አክዓብ ንጉሥ ነበር። ሴቶቹም ሁሉ ኤልዛቤልን ተከትለው ተሳለቁበት፡ ምናልባትም ወተርሄድ አይነት የጸጉር አቆራረጥ የተቆረጡ፡ ምናልባት ዛሬ እንዳለው አይነት። ሁሉም ኤልዛቤልን ተከተሉ። ፓስተሮችም ችግር የሌለው መሰሏቸው ነበር። "ተውአቸው። ዝም አሏቸው።"

156 በዚያን ጊዜም፡ እግዚአብሔር ኤልያስ የሚባል ሰው፡ ከምድረ በዳ አስነሣው። ከየት እንደመጣ እንኳን አናውቅም። እሱን የሚታወቅበት ትምህርት ቤት አልነበረውም። እርሱ ግን ተነሣ፡ ያን ሁሉ ነገር ኮነነ። አጠቃላይ-አደረጃጀቱን ኮነነ።

157 እሱ ዛሬ፡ በዚህ ሆነታ ቢመጣ፡ የእኛን-አደረጃጀትም እንዲሁ ይኮንናል።

158 ኤልዛቤልን ሁሉ ኮነነ። እና በመጨረሻ፡ ነቢዩን ያዳከመችው፡ እሷ ነበረች። እንደ ዮሐንስ፡ ሸሸ፡ ኤልዛቤል ልትገድለው ስትሄድ ከጥድ ዛፍ በታች ተኛ። ጠላችው።

159 ዮሐንስ ከበረሃ በመጣ ጊዜም ይህ እናስተውላለን፡ የምድረ በዳው ወዳጅ፡ ከምድረበዳ እንደገና መጣ፡ በፍቺ እና በጋብቻ፡ እንደገና አግብተው ለሚኖሩ፡ በቀጥታ ለዘመናዊ ሴቶች ነገሩን ቆራረጠ። ከየትኛውም ትምህርት ቤት

አልመጣም። ከእግዚአብሔር የተላከ ሰው፡ ከእግዚአብሔር ነው የመጣው። እናም ዘመናዊ ሴቶችን፡ እነርሱን አጥብቆ ኮነናቸው፡ ወደ ኋላም አላለም። ነገር ግን ጊዜው እንደቀረበ፡ መሲሁ ሊናገር እንደሆነ በግልጽ ተናግሯል። ያንን ተመልከቱ።

160 አሁን የኤልያስን የመጀመሪያ መምጣት ጊዜ ከእነዚህ ዘመናዊ ነቢያት ጋር አነጻጽሩት፡ ኤልዛቤሎቻቸው ፀጉራቸውን እንዲቆርጡ፡ መፍቀድ፡ ቁምጣም እንዲለብሱ፡ ሲጋራ እንዲያጨሱ፡ የፈለጉትን ሁሉ እንዲያደርጉ ፈቀዱላቸው። ምንም ባይናገር ይሻለዋ፡ እሱን ትታው፡ ሌላ ታገባለችና። እነርሱን በሰው-ሰራሽ ሃይማኖቶችን መምራት፡ ያ ነውር ነው፡ የሰው አስተምህሮ። እናም፡ ይህንንም በማድረግ፡ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ከንቱ ያደርጋሉ፡ ምክንያቱም ቤተ ክርስቲያንን መቀላቀል እና አሁንም ክርስቲያን ነን ስለሚሉ፡ መብታቸውን ተጠቅመው ክርስቲያን ነን ይላሉ፡ እና ይቀጥላሉ። እነሱ የሚፈልጉት ያ ነው። ያኔ ያደረጉት ይህንኑ ነው።

161 ነገር ግን፡ እግዚአብሔር በሚልክያስ ምዕራፍ 4 ላይ፡ ቃሉን እንደገና እንደሚፈጽም፡ ቃል እንደገባ፡ አስታውሱ። ያ ትክክል ነው። ልክ እንደ ዘመነ ዮሐንስ፡ ልክ እንደሌሎች ጊዜያት፡ ዛሬ የት እንዳለን ተመልከቱ።

162 ይህን ትንሽ ሽማግሌ አሞጽ፡ ያሳደገውን ትንሽ ህብረት እዩ። ከየት እንደመጣ አናውቅም። እረኛ ነበር። እግዚአብሔር በበጎቹ ማሰማርያና ላም ማሰማርያ፡ እና፡ አውጥቶ አሠለጠነው። ወደ ሰማርያም በመጣ ጊዜ፡ ተነሥቶ በዚያች ኮረብታ ላይ በተነሣ ጊዜ፡ ወደዚያ ተመለከተ። ፀሐይም ራስ በረሃው ላይ አበራች፡ ጢሙም ሸበት፡ እና ዓይኖቹ አንድ ላይ ተጣብቀይ ያበራሉ። አምላካዊ ዓይኖቹ ተርገበገቡ፡ ቱሪስቶች ወደ ውስጥ ሲገቡ ባዩት ትእይንት ሳይሆን፡ ከተማይቱ ሁሉ ለኃጢአት ለመሰጠቷ ምክንያት ነው።

163 ይህ ትንሽ፡ ማንነቱ ያልታወቀ ሰው ማን ነው? አዎ፡ ነቢዩ ነው፡ አሞጽ። በዳግማዊ ኢዮርብዓም፡ በከዳተኛ ንጉሥ ዘመን፡ ሕዝቡ ማንኛውንም ነገር ያድርግ ብሎ ትንቢት ተናገረ። ካህናቱ ሁሉም እንዲሁ ነበሩ። ምርጥ አብያተ ክርስቲያናትን ሠሩ። ምርጥ አለባበስ ነበራቸው። ሴቶቻቸው ሴሰኞች ነበሩ። በፈለጉት መንገድ ለብሰዋል። ቱሪስቶች ቆንጆዎቹን ልጃገረዶች እና የእነሱን ጉዞ ለማየት፡ ወደ ሁሉም ቦታ ይጎርፉ ነበር።

164 ልክ የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው ተብሎ እንደሚታሰብ፡ ሌላ ዘመናዊ U.S.A. ሆኑ። ማንም ስለ ስለ እሱ አያነሣም። በህዝቡ ላይ እንደዚህ የተጣበቀ ይመስላል። ፊፍ-...

165 የዛሬ፡ አሥራ ስምንት ዓመታት! ልጄ ርብቃ ዛሬ አሥራ ስምንት፡ ዓመቷ ነው። አስራ ስምንት አመታት፡ እነዚህን ነገሮች በመኮነን፡ በዚህ ህዝብ ተመላልሻለሁ። እና ተመልሼ ሰመጣ፡ ከአመት እስከ አመት፡ ለመጀመሪያ ጊዜ ስጀምር ከነበረው ብዙ ፀጉቸውን-ያሳጠሩ ሴቶች ይኖራሉ።

166 አንድ ታላቅ፡ ታዋቂ የጴንጤቆስጤ ሰባኪ፡ ከአንድ አመት በፊት፡ ቢሮ ውስጥ ወሰደኝ፡ በደንብ-የሚታወቅ፡ አለም-አቀፍ ታዋቂ ሰው፡ እንዲህ አለኝ፡ "እኔ... ወንድም ብራንሃም፡ እጄን በላይህ ጭኜ እንድጸልይልህ ፍቀድልኝ።"

እንዲህ አልኩት፡ "አልታመምኩም።"

167 አለኝም፡ “ግን የሆነ ችግር አለ።” እንዲህ አለ፡ “ወንድም ብራንሃም፡ አገልግሎትህን ታበላሻለህ። ማንም አይተባበርህም። ሰባኪዎቹ ከአንተ ጋር እንደማይተባበሩ ምንም ጥያቄ የለውም፡ ሴቶችን የምትኮንንበት መንገድ ነው።” እንዲህ አለኝ፡ “ሰዎች ነብይ ብለው ይጠሩሃል።”

እንዲህ አልኩት፡ “ነኝ ብዬ በጭራሽ አልተናገርኩም።”

168 እንዲህ አለ፡ “አንተ እንደሆንክ ግን ያስባሉ።” አልኩት፡ “እኔም እንዲሁ አምናለሁ።” “ለታመሙ ሰዎች እንድትጸልይ ተጠርተሃል፡” አለኝ። እንዲህ አለኝ፡ “ለታመሙ ሰዎች ጸልይ፡ እና ሴቶችን ግን ተዉአቸው። ስሜታቸውን ጎዳህ።”

“እንዴት፡” ብዬ ጠየቅኩት?

169 አለኝ፡ “ጸጉራቸውን-ማሳጠራቸው እና ሌሎች ነገሮችን መልበሳቸው ሰለ እነሱ ማውራት።”

“ያ’ማ ስህተት ነው፡” አልኩት።

170 መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ “ፀጉሯን የምትቆራርጥ—አንዲት ሴት፡ ባሏ በፍቺ ሊተዋት ይችላል።” ፈጽሞ ትክክል ነው። “ራሷን ታዋርዳለች።” ያ መጽሐፍ ቅዱስ ያለው ነው። እንደወደዳችሁት ወይም እንደማትፈልጉ አላውቅም፡ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ፡ በአንደኛ ቆሮንቶስ ውስጥ የተናገረው ያንን ነው።

171 [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]… ገላ ውጭ እስኪወጣ ድረስ ቆዳን-አጥብቆ ያጣብባል። ከዚያም እነሱ—እነሱ እየዞሩ መጥተው፡ እንዲህ ይላሉ፡ “ለምን፡ ሚስተር ብራንሃም፡ ገበያ ላይ ያለው ብቸኛው ልብስ ይህ ነው።”

172 እቃ እና የልብስ ስፌት ማሽኖች አሁንም አለ። ሰበብ የለም። የአሚሽ እና የዱንካርድ ሴቶች አሁንም ይለብሷቸዋልና። በትክክል። [ጉባኤው ያጨበጭባል—አርታዒ።]

ከዚያስ ምን ሆነ? ወጡና ቀጠሉ።

173 አንዲት ሴት እንዲህ አለች፡ “መልካም፡ ሚስተር ብራንሃም፡ እኔ ቁምጣ አልለብሰም። እኔ የምለብሰው-… ” ምንድን ናቸው፡ ፔዳል ፑ-… [አንድ ወንድም “ፔዳል ፑሽርስ፡” አለ።—አርታዒ።] አዎን። “እነዛን እለብሳለሁ፡” አለች።

174 እኔም “ያ’ማ የከፋ ነው፡” አልኳት። እንዲህ አልኳት፡ “መጽሐፍ ቅዱስ እንዲህ ይላል፡ ‘ለሴት የወንድ ልብስ መልበስ አስጸያፊ ነገር ነው።’” እና ይህች አሜሪካ አሁን ምን አይነት መልከ-ጥፉ እይታ ነች! አያችሁ? ያ ትክክል ነው።

175 አንድ ነገር ልንገርሽ፡ እህቴ። ለባልሽ ወይም ለወንድ ጓደኛሽ እንደ አበባ፡ ንፁህ ልትሆኚ ትችያለሽ፡ ነገር ግን በፍርድ ቀን ምንዝርና ሰለ ስራሽ መልስ ትሰጪያለሽ። ኢየሱስም እንድህ አለ፡ “ወደ ሴት ያየ ሁሉ፡ የተመኛትም፡ ያን ጊዜ ከእርሰዋ ጋር አመንዝሯል።” ኃጢአተው አንቺን ካየ፡ በፍርድ ቀን መልስ ትሰጥበታለች። እራስሽን ለእርሱ አቅርበሻል። እንደፈለግሽ። ኡህ-ሁህ።

176 ፈሪሃ እግዚአብሔር ያላት ሴት እንደዚህ አይነት ልብስ መልበስ ለምን ትፈልጋለች? ከዚያም በልሳን ሰለ ተናገራችሁ እና ወለሉ ላይ ስለሮጣችሁ

መንፈስ ቅዱስ አለኝ ትላላችሁ። ያ’ማ፡ ሆቴንቶትሶችም፡ አረሜውያንም ያንን ሲያደርጉ አይቻለሁ። መንፈስ ቅዱስ ግን ንጽህና ነው፡ ቅዱስ፡ ያልረከሰ ነው። በእርግጠኝነት።

177 ይህ ሰው እንዲህ አለኝ፡ “አንተ ከሆንክ... ነብይ መሆንህን ያምናሉ። ታላቅ መንፈሳዊ ስጦታዎችን እንዴት እንደሚቀበሉ፡ እና ለእግዚአብሔር ነገሮችን እንዴት እንደሚያደርጉ ለምን አታስተምራቸውም? ነብይ ከሆንክ ለምን አታስተምራቸውም? ”

178 እንዲህ አልኩት፡ “ABC እንኳን መማር በማይችሉበት ጊዜ አልጀብራን እንዴት ማስተማር እችላለሁ? ” ABC ምን ማለት እንደሆነ ታውቃላችሁ? “ኦልዌይስ ብሊቭ ክራይስት።” ኡህ-ሁህ። ያንን እንዴት ልታደርጉት ነው? አያችሁ፡ **ከዚህ** በመጀመር ፈንታ፡ **ወደዚያ** መሄድ ትፈልጋላችሁ።

179 እግዚአብሔር ቤተክርስቲያኑን በኢየሱስ ክርስቶስ መሠረት ላይ ይገነባል፡ እና ያ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ከሱ ውጪ፡ ሁሉም ሌሎች አቋማች አአሸዋ እየተተሰመጡ ነው። እግዚአብሔር አይለወጥም። ተፈጥሮው አይለወጥም።

180 ሴቶችን ከወንዶች፡ ወንዶችንም ከሴቶች የተለየ አድርጓል። የተለየ ልብስ አለበሳቸው፡ እናም በዚህ መንገድ እንዲቆዩ ይፈልጋል። አያችሁ? ሴቶች ወንዶችን መምሰል ይፈልጋሉ፡ ወንዶች ደግሞ ሴቶችን መምሰል ይፈልጋሉ። ኦህ፡ ይገርማል! እንደዚህ ያለ ጠማማነት! ያ ነው... እና ሁሉም ነገር፡ በሰዎች ላይ የተያዘ ይመስላል፡ እና እናንተ መለወጥ አትችሉም። ታላቅ ጭራቅን ይመስላል፡ ታላቅ ጨለማ፡ እኔ የምናገረውን ከተረዳችሁ፡ በመንፈስ ነው። በጭራቅ ተይዘዋል፡ እና እነርሱም—እነሱ ከእሱ መራቅ አልቻሉም፡ በጣም ብዙ ሆሊውድ፡ ብዙ ቴሌቪዥን፡ በጣም ብዙ ሌሎች ከንቱ ነገሮች። ያለን ነገር ሁሉ የተበከለ ነው። ይህ አያስገርምም፡ “ስለ ተመረጡ ሲባል፡ ነገሩ ባያጥር ኖሮ፡ ሥጋ ለባሽ ሁሉ ባልዳነም ነበር።”

181 እናንተም “ከዚህ በፊት ይህን አላውቅም ነበር፡” ትላላችሁ። መልካም፡ ከአሁን በኋላ፡ አሁን አውቃችኋል። አያችሁ? ያ ነው... ያንን ባቆም ይሻላል። ወደ ኋላ እንመለስ። አስተውሉ።

182 ዮሐንስ ምልክት ነበር። እና ያንን አስታውሱ፡ እግዚአብሔር ለመጀመሪያ ጊዜ ባደረገው መንገድ፡ እንደገና የሚያደርገው በዚያ መንገድ ነው። ቃል ገብቷል። አሁን፡ እግዚአብሔር በማንኛውም ጊዜ፡ ለእንደዚህ አይነቱ ተግባር፡ የሰዎችን ቡድን አይጠቀምም።

183 አስታውስ፡ በአንድ ወቅት አንድ ቡድን ነበር፡ ያም፡ አክዓብ በሚባል ታላቅ ሰው፡ እሱም አገኘው እና... አራት መቶ የእስራኤል ነቢያትን አመጣለት። እንግዲህ፡ እነዚያ የአረማውያን ነቢያት አልነበሩም። አራት መቶ እስራኤላውያን ነቢያት ናቸው። ሁሉም ዲግሪያቸውን እና ሁሉም ነገር ነበራቸው፡ ትልቅ ትምህርት ቤት ነበራቸው።

184 የይሁዳ ንጉሥ የሆነ፡ ኢዮሣፍጥ የሚባል፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበረና ወደዚያ ወረደ። እነሆም አማኝ ከማያምን ጋር የተቀላቀለበት ጊዜ ያኔ ነው። ነገሮች ተበላሹ።

185 እርሱም እንዲህ አለ፡ “ሬማት-ዘገልዓድ... ” አሁን ምን ያህል እውነት ሊሆን እንደሚችል፡ ተመልከቱ። እንዲህ አለ፡ “ሬማት-ዘገልዓድ የእኛ ነው፡ እዚያ ላይ። እዚያ ላይ ባለው የአገሪቱ ክፍል፡ ይህ የእኛ ነው።” ኢያሱ፡ ምድሩን በመከፋፈል፡ ለእስራኤል ሰጠ። ፍልስጤማውያን፡ አረማውያን፡ መጥተው ወሰዱአቸው። እንዲህ አለ፡ “የእኛ ናት።”

186 አሁን በመሠረታዊነት፡ ሰዎች እንዴት ትክክል ሊሆኑ እንደሚችሉ፡ እና እንዴት እንደሚሳሳቱ ተመልከቱ። ነገሩ በእውነቱ የሚገባው ለእስራኤል ነው። ነገር ግን ወንድሜ ሆይ፡ የእግዚአብሔር ቃል ኪዳኖች በሙሉ፡ በቅድመ ሁኔታዎች ላይ ናቸው፡ አየህ፡ “በጌታ ፊት ቢመላለሱ።”

187 አሁን እዚህ ተመልከቱ። እንዲህ አለ፡ “ከእኔ ጋር ትመጣለህ፡ ያንን ምድርስ እንድንመልስ ትረዳኛለህን? መልካም፡ ያም፡ የፍልስጥኤማውያን ልጆች፡ በእስራኤል ሰንዴ፡ ሆዳቸውን እየሞሉ ነውና።” እንደ ቅዱስ ቃሉ መሰረት ትክክል ነው። እንዲህ አለ፡ “እንድንወጣባቸው እርዳኝ።”

188 እንዲህ አለ፡ “መልካም፡ የእኔ... ” የችኮላ ስህተት የሠራው እዚያ ላይ ነው፡ “ሰረገሎቼ ያንተ ናቸው፡ ሰዎቼም እንደ አንተ ናቸው። ከአንተ ጋር እሄዳለሁ።”

189 ከዚያም ኢዮሣፍጥ ማሰብ ጀመረ፡ ታውቃላችሁ። “አለ፡ ከመሄዳችን በፊት ስለዚህ ጉዳይ ጌታን ማማከር የለብንምን? ”

190 “ኦህ፡ በእርግጠኝነት፡” አክዓብም አለ፡ “በእርግጠኝነት። ኡህ-ሁህ። ይቅርታ። እኔ—እኔ ያንን ማሰብ ነበረብኝ።”

“የሆነ ቦታ ነቢይ የለምን? ”

191 “ኦህ፡ በእርግጠኝነት። አለኝ—እዚህ ታች አንድ—አንድ ሴምናሪ አለን፡ ከመቼውም ጊዜ ካየሃቸው የተሻለ ነው። ሁሉም በጣም ጥሩውን ልብስ ይለብሳሉ። ከፍተኛ-ጥራት ያላቸው ምሁራን ናቸው። እስከ ጥግ ድረስ፡ አስተምሬአቸዋለሁ፡ እናገኛቸዋለን።”

192 ስለዚህ ወደዚያም ወረዱ። እና ሁሉም ተሰበሰቡ። ግብዞች አልነበሩም። ራእይ እስኪያዩ ድረስ፡ ደጋግመው ጸለዩና ጸለዩ።

193 ከዚያም እንዲህ ሆኑ። ከእነርሱም አንዱ ከብረት ሁለት ትላልቅ ቀንዶች ሰራና። እንዲህ አለ፡ “በዚህ ፍልስጥኤማዊያንን፡ ወይም የ—አሦራውያንን ወግታችሁ፡ ከሀገር ታወጣላችሁ።” እንዲህ አለ፡ “**የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል**። ጌታ ከአንተ ጋር ነውና፡ ውጣ።” እያንዳንዳቸውም፡ ከዚያም፡ በአንድ ልብ ሆነው፡ በመንፈስ ተሞሉ። የእስራኤል ነቢያት በአንድነት “ውጣ፡ ጌታ ከአንተ ጋር ነው።” (እናንተስ “ይህ መጽሓፍ ቅዱሳዊ ነው” ትላላችሁን? ) “እግዚአብሔር ይህን ርስት ለሰዎቹ ሰጣቸው፡ ጠላትም ወሰደው። ለማስመለስ የመሄድ መብት አላችሁ።”

አሁን፡ ጴንጤቆስጤ ሆይ፡ ከዚህ ትምህርት እንድትማሩ እፈልጋለሁ።

194 ኢዮሣፍጥ፡ ግን፡ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ነበረ፡ “አሁንም ትንሽ ስህተት አለ፡” አለ። እንዲህ አለ፡ “ሌላ ሰው የላችሁምን? ”

195 “አራት መቶ በደንብ-የሰለጠኑ ነቢያት እዚህ ከቆሙ በኋላ፡ ሌላ ሰው? ” እዚህ ወለል ላይ ብዙዎች እንዳሉ ሁሉ። “በአንድ ልብ ቆመው፡ እንድህ ይላሉ፡

‘የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል።’ እንዲህ ይላሉ ‘ኢያሱ ምድሩን ለእኛ ሰጠን፡ ሄዳችሁ መልሱት። የእኛ ነው። ሂዱ ውሰዱ!’”

196 ኢዮሣፍጥ ግን ሌላ ጠየቀ። እንዲህ አለ፡ “ጌታን የምናማክረው ሌላ ሰው የለምን? ”

197 እንዲህ አለ፡ “ኦህ፡ ሌላ አንድ አለ፡ ግን፡” እንዲህ አለ፡ “እጠላዋለሁ።” ኡህ-ሁህ፡ ኡህ-ሁህ። “እርሱም የይምላ ልጅ፡ ሚክያስ ነው፡” አለው። “አልወደውም። እሱ ሁል ጊዜ ስለ እኔ መጥፎ ነገር ይናገራል፡” አለው።

እንዲህ አለ፡ “ንጉስ እንዲህ አይናገር። ሂድና እሱን አምጣው።”

198 ከዚያም የሆኑ መልእክተኞችን ወደዚያ ላኩ። ከእነርሱም አንዱ እንዲህ አለው፡ “አሁን፡ ሚክያስ፡ አንድ ነገር ልንገርህ። አሁን፡ እንዳያባርሩህ፡... - ከጥቅት ጊዜ በፊት፡ ከኅብረት እንደቆረጡህ ታውቃለህ፡ ምክንያቱም ሁልጊዜ ለሰዎች መጥፎ ነገር ስለምትናገር ነው። አሁን የህብረት ካርድህን መልሰህ ማግኘት ከፈለክ፡ እነሱ የሚያደርጉትን ተመሳሳይ ነገር ተናገር፡ እና፡ ኦህ፡ እንደገና በእቅፋቸው ስር ያስገቡሃል።”

199 እሱ ግን በእርግጥም ነብይ ነበር። እንዲህ አለ፡ “ጌታ አምላክ ሕያው እንደመሆኑ፡ እግዚአብሔር በአፌ ያስቀመጠውን ብቻ እናገራለሁ።” ኦህ! እግዚአብሔር ይህን ሰው ይባርከው። እንዲህ አለ፡ “እስከ ዛሬ ማታ ድረስ ቆዩና፡ ጌታ የሚለኝን እያለሁ።”

200 በማግስቱ ጠዋት፡ “ወጣና፡ እስራኤል እረኛ እንደሌላቸው በጎች ሲበተኑ አየሁ፡” አለ። ከዚያም ራእዩን አንሥቶ ኤልያስ ከተናገረው ጋር አነጻጸረው፡ በአክዓብም ላይ ከደረሰው ነገር ጋር አነጻጸረው። የተረገመውን እንዴት ይባርካል? ምንም ያህል ቢሆን...

201 እኛ እግዚአብሔርን የምንፈራ ሕዝብ ነን። የጴንጤቆስጤ ቤተ ክርስቲያን፡ ባፕቲስት፡ እና ሜቶዲስት፡ እና የመሳሰሉት፡ የክርስቲያን ቤተክርስቲያን ናቸው፡ እግዚአብሔር የረገመውን ግን እንዴት ትባርካላችሁ? “ምንም መሰሎ አይስማኝም፡” እንዲህ ትላላችሁ፡ “እኔ—እኔ **ይህንን** ተቀላቅያለሁ። **ይህንን** አደረግሁ።” ያ ከዚህ ምንም ግንኙነት የለውም። ምን እንዳደረጋችሁ ተመልከቱ። እንዴት እንደዘጉ፡ ጴንጤቆስጤዎችን ተመልከቱ። የነበርክበትን ተመልከት፡ እና አሁን ያለህበትን ተመልከት። ምንም ጥያቄ የለውም፡ አይኖች፡ ዓይኖች ታውረዋል።

202 ከዚያም፡ አክዓብ፡ ይህ... ቄስ አፉን በጥፊ መታው። እንዲህም አለ፡ “አስገቡት፡” አክዓብም እንዲህ አለ፡ “ወደ ውስጠኛው ወህኒ አስገቡት። በሰላም ስመለስ፡ ከዚህ ሰው ጋር እጨርሳለሁ።”

203 እንዲህ አለው፡ “ተመልሰህ ከጣህ፡ እግዚአብሔር አልተናገረኝም።” ኡህ-ሁህ? አያችሁ? ነቢይ ነበረ፡ ምልክትም ነበረ፡ ድምፁ ነበረ። አለመታዘዝም ፍርዱን አመጣ።

204 መንፈስ ቅዱስ ዛሬ ነብያችን ነው። ድምፁን መስማት አቃታችሁን? የመንፈስ ቅዱስ መልክ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ! እርሱ እነዚህን ነገሮች እንደሚናገር፡ በቅዱሳት መጻሕፍት ተለይቷል።

205 እግዚአብሔር ይህን አንድ ሰው አናገረው። ይህ፡ እግዚአብሔር ከቡድኖች ጋር ፈጽሞ አይነጋገርም፣ ከአንድ ሰው ጋር ነው። ኤልያስ ቡድን አልነበረም። ዮሐንስ ቡድን አልነበረም። እነሱ ቡድን ወይም የኃይማኖት ተቋም አልነበሩም፡ እንዳቸውም አልነበሩም። ነገር ግን ሁሉ ይህንኑ ተቃውመዋል። ያ ትክክል ነው። ዮሐንስ እንዲህ አለ፡ "አብርሃም አባታችን አለን ብላችሁ ታሰባላችሁ። እግዚአብሔር ከእነዚህ ድንጋዮች ለአብርሃም ልጆች አድርጎ ሊያስነሣቸው ይችላል።"

206 እና የፍጻሜው-ዘመን ምልክት የመጨረሻ-ዘመን ድምጽ ይኖረዋል። የፍጻሜው-ዘመንም ምልክት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በተነገረው መሠረት ይሆናል። የፍጻሜው-ዘመን ድምጽ፡ የፍጻሜው-ዘመን ምልክትን፡ ተከትሎ የሚመጣው በትክክል በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ ተለይቶ የሚታወቀው፡ ቃል የተገባለት መጽሐፍ ይሆናል።

207 አሁን በሉቃስ 17 ላይ የፍጻሜው-ዘመን ምልክቱ፡ በሰዶም እንደነበረው እንደሚሆን እናነባለን፡ ቃል ኪዳን። እና እኛ የሰጋ ሰዶም አለን፡ ምልክቱን በመንፈሳዊ እዚህ ለምን ማመን አንችልም? ቅዱሳት መጻሕፍትን ማየት ከቻላችሁ፡ ደግሞ፡ ሉቃስ 17 ምልክቱ ነው፡ ሚልክያስ 4 ደግሞ ድምጹ ነው። ምልክቱም እግዚአብሔር በሥጋ የተገለጠ፡ የልብን ምሥጢር የሚያውቅ ነው፡ የሚልክያስ 4 ድምፅም ህዝቡን ከሃይማኖት ተቋም፡ ወደ አባቶች እምነት የሚመልስ ነው። ያ ምልክት ነው።

208 ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? አሁን እየዘጋሁት ነው። ምልክቶች በአብዛኛው ተቀባይነት አላቸው፡ እርግጠኝነት፡ ድምፁ፡ ግን፡ ኦህ፡ አይሆንም። ምልክቱን ተከትሎ የሚመጣው ድምጽ፡ ከዚህ ጋር ምንም መቀበል አይፈልጉም። አዎን።

209 የኢየሱስ ምልክት፡ እንደ መሲህ፡ የታመሙትን መፈወስ፡ ያንን ተቀበሉ። አንድ ቀን ግን "እኔና አብ አንድ ነን፡" አላቸው።

210 ኦህ፡ ይገርማል፡ ያ ድምፅ ተቀባይነት አላገኘም። እንዲህ አሉ፡ "ከእግዚአብሄር ጋር እኩል፡ እራስህን አምላክ ታደርጋለህ።"

እርሱም "እኔ የእግዚአብሔር ልጅ ነኝ፡" አላቸው።

211 "ኦህ፡ ይገርማል፡ እግዚአብሔር እንዴት ልጅ ሊኖረው ቻለ? " አያችሁ? "እግዚአብሔር ልጅ አለው ከማለት ያርቃችሁ!"

212 ነገር ግን፡ አያችሁ፡ እነሱ——ምልክቱን አመኑ፡ የታመሙ ሰዎች ተፈውሰዋል፡ እና፡ ኦህ፡ ያ ድንቅ ነበር፡ ብቻ ያ ጥሩ ነበር። ነገር ግን ወደ ድምፅ ሲመጣ፡ ድምፁን ማመን አልፈለጉም። ምን አደረጉ? እሱን አሰወጡት።

213 እና ምን እንደሆነ ታውቃላችሁ? መጽሐፍ ቅዱስ፡ በዚህ በሎዶቅያ ቤተ ክርስቲያን ዘመን፡ በራዕይ ምዕራፍ 3 ላይ፡ ተመሳሳይ ነገር እንደሚደረግ ይነግረናል። እሱ ከቤተክርስቲያን ውጭ ነበር። ያ የተገለጠው ቃል ነው። እርሱ የተገለጠው ቃል ነበር። እርሱ አሁንም የተገለጠው ቃል ነው።

214 የሰዶምን፡ የሉቃስን ምልክት ብታምኑ፡ ያንን ማመን ከቻላችሁ፡ የሚልክያስ 4ን ድምጽ ለምን አትቀበሉትም? አያችሁ፡ ለምን እናንተ፡ እናንተ? ሊረጋገጥ ይችላል። ሊደረግ የሚቻልበት ብቸኛው መንገድ... ምልክቱ ሊረጋገጥ ይችላል፡ ነገር ግን ድምጹን መቀበል አለባችሁ።

215 ሙሴ በአካል እንዲወርድ፡ ተልእኮ ተሰጥቶታል፡ መንፈሳዊም ምልክትን እንዲያደርግ እና ህዝቡን ወደ አባቶች ቃል ኪዳን እንዲመልስ።

216 የሚልክያስ 4 ህዝቡን መመለስ ነው "ወደ አባቶች እምነት መመለስ።" ኦህ፡ ዕውር እና የተበታተናችሁ ሆይ፡ ወደ ራሳችሁ፡ ተመለሱ!

217 በመዝጊያው ላይ፡ ይህን እናገራለሁ፡ ይህን የመጨረሻው ሃሳቤን። ነቢዩም እንዲህ አለ፡ "ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።" ተመልከቱ፡ እንዲህ አለ፡ "ቀንም ሆነ ሌሊት ተብሎ ሊጠራ የማይችል ቀን ይመጣል።" አሁን አዳምጡ። እየዘጋሁ ነው። "ቀን ይመጣል... " ይህንን በጥልቀት እንዲሰምጥ እናደርገው፡ እና እግዚአብሔር በዚህ ማህበረሰብ ውስጥ፡ ዛሬ ማታ፡ በዚህ አዳራሽ ውስጥ በሁሉም ልብ ውስጥ ያኑረው። ነቢዩም እንዲህ አለ፡ "ቀንም ሆነ ሌሊት ተብሎ የማይጠራ ቀን ይመጣል፡ አስከፊ፡ ዝናባማ፡ ጭጋጋማ ቀን። ነገር ግን፡" እንዲህ አለ፡ "ሲመሽ፡ ብርሃን ይሆናል።"

218 አሁን፡ አስታውሱ፡ ፀሐይ ሁልጊዜ በምስራቅ ትወጣለች እና ወደ ምዕራብ ትሄዳለች። ስልጣኔ ፀሐይን ይከተላል። ታውቃላችሁ። እና፡ አስተውሉ፡ በምስራቅ የምትወጣው ያች ፀሀይ በምዕራቡ የምትጠልቅ ፀሐይ ናት። አሁን፡ ሥልጣኔ ከፀሐይ ጋር በትክክል ተጉዟል፡ እስከ አሁን ድረስ ምሥራቅና ምዕራብ ተገናኝተዋል። እኛም በምዕራብ ዳርቻ ላይ ነን፡ ምስራቅ እና ምዕራብ።

219 እና፡ አስታውሱ፡ ወንጌልም በተመሳሳይ መንገድ ተጓዘ። የኢየሱስ ክርስቶስ መምጣት፡ S-u-n ሳይሆን S-o-n፡ ከምስራቅ ተነሳ። S-o-n፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ወደ ምስራቃዊ ሰዎች፡ ከምስራቅ ተነሳ።

220 እና አሁን ሰዎች ቤተ ክርስቲያንን የተቀላቀሉበት፡ የእምነት ተቋሞችን የፈጠሩበት፡ ለማየት በቂ የሆነ ብርሃን የሆነበት ጊዜ ነው፡ "መልካም፡ ቤተ ክርስቲያን ይኖረናል፡ **ይህንን** እንገነባለን። ትምህርት ቤት እንገነባለን። ሆስፒታል እንገነባለን። እናስተምራለን። ሴሚናሪ ይኖረናል።" ይህን ለማድረግ በቂ ብርሃን ነበራቸው።

221 ነገር ግን፡ አስታውሱ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንድህ አለ፡ የጌታ ነቢይ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፡ እርሱም **የሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር እንዲህ ይላል፡** "በምስራቅ የበራችው ፀሐይ በምዕራቡ፡ በምሽት ጊዜ እንደገና ታበራለች። ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።"

222 ምን እያደረገ ነው? በሉቃስ ምዕራፍ 17 ላይ የተናገረውን በትክክል ይፈጽማል። "በመጨረሻው ዘመን፡ የሰው ልጅ በምስራቅ እንደነበረው ሲገለጥ፡ ያው ልጅ ያበራል፡ አንድ ኃይል፡ አንድ መንፈስ ቅዱስ፡ ያው አንድ ነገር ያደርጋል። ሲመሽ ብርሃን ይሆናል።"

223 ተመሳሳይ ፀሐይ በተጓዘበት፡ ተመሳሳይ መልኩ ል-ጅ-ም ተጉዟል፡ በምሥራቅ በኩል፡ ከጳውሎስ ጋር መጣ፡ በማርቲን ሉተር፡ ወደ ጀርመን ዘለለ፡ እንደገና ዘለለ፡ በሚቀጥለው አቅጣጫ ላይ፣ እና ከዚያ ወደ እንግሊዝ፡ ወደ ጆን ዌስሊ ሄደ፡ በአትላንቲክ ውቅያኖስ ላይ ዘሎ፡ ወደ ዩናይትድ ስቴትስ፡ ወደ ጴንጤቆስጤ፡ እና አሁን ጴንጤቆስጤ ራሷን ቀንሳለች፡ እኛም አሁን በባህር ዳርቻ ላይ ነን።

224 ሁሉም፡ የሃይማኖት ተቋም ሆኑ፡ ልክ እንደ መጀመሪያው ዘመን፡ እግዚአብሔር የረገመውን መደራጀትን አደረጉ። ጰንጤቆስጤ፡ እና ሁሉም፡ ያንን አደረጉ።

225 እርሱ ግን እንድህ አለ፡ "ሲመሽ ብርሃን ይሆናል። በምሽት ጊዜ ምልክት ይነሳል።" እንዳያመልጣችሁ፡ ጓደኞቼ። እንዳያመልጣችሁ፡ አሁን፡ ያው ልጅ ያንን ብርሃን ይሰጣል። ተመሳሳይ S-u-n ተመሳሳይ S-u-n የጸሓይ ብርሃን ትሰጣለች። ተመሳሳይ S-o-n ተመሳሳይ S-o-n የልጅ ብርሃን ይሰጣል።

226 አሁን፡ ይህ የእኔ አባባል አይደለም። እዚህ ያላችሁ ሁሉ፡ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚለው ያውቃል፡ እጆቻችሁን እነሡ። [ጉባኤው እንዲህ ይላል፡ "አሜን።"—አርታዒ።] ያ ፈጽሞ ትክክል ነው።

227 አሁን፡ ትችላላችሁ፡ የእናንተ ውሳኔ ነው። የእግዚአብሔር ልጅ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ህያው እንደሆነ፡ እመኑ። በህይወት አለ። እርሱ በትህትና፡ ትሁት ነው። ሁልጊዜም እንደዛው ይኖራል። የከፍታ መንገዱ ወደታች ነው። ራሳችሁን አዋርዱ፡ ከኩራት ሃሳቦቻችሁ ራቁ፡ እና ጌታ ኢየሱስን እመኑ። ምልክቱን ተመልከቱ፡ ከዚያም ድምፁን እመኑ። የተበታተናችሁ ሆይ፡ ወደ ራሳችሁ፡ ተመለሱ!

እንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

228 "ከሙሴም ጋር እንደ ነበረው፡ የፊተኛው ምልክት በእጃቸው ያለውን፡ ድምፅ ካላመኑ፡ ሁለተኛውን ምልክት አድርግ። ከዚያም፡ ይህን ምልክት ካላመኑ፡ ከዚያም በውቅያኖስ ውስጥ ወይም በባህር ውስጥ ያለውን ውሃ (ውሃ ህይወትን ይወክላል) ውሰድና፡ መሬት ላይ አፍስሱ፡ ደም ይሆናል።"

229 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ አሁንም በጣም ረፍዷል፡ ነሲመሽ ግን ብርሃን እንደሚኖር ቃል ገብተሃል። ሰዎች እያሰላሰሉ ቃሉን ሲያጠኑት፡ የወንጌላችን ድምጽ ወደ ልቡናቸው ዘልቆ ይግባ።

230 ይህንን ማህበረሰብ ባርካቸው፡ ጌታ ሆይ። እነዚህን ሰዎች ባርካቸው። እዚህ ተቀምጠው የተራቡ፡ ድሆች ሕፃናት ሲረገጡና ሲጨቆኑ፡ እና **ይህን** ሲሆኑ፡ ተመልከታቸው፡ ሰይጣን ያንን ያደረገው እዚያ በደረሰ ጊዜ እነርሱን ከነገሩ ለማሳወር መሆኑን ይታወቃልና። ዛሬ ማታ፡ እነርሱ፡ በአንድ ልብ ሆነው፡ ኢየሱስ ክርስቶስን አምነው፡ ከሙታን መነሣቱን፡ የገባውንም ቃል ኪዳን ይመኑ።

231 "ባላሰቡበት ጊዜ፡ የሰው ልጅ ይመጣል፡" ብለሃልና።

232 ቤተ ክርስቲያኒቱ፡ ብዙ ገንዘብ አግኝታ፡ በሚሊዮን በሚቆጠር ዶላር ህንፃ እየገነባች። አባት ሆይ፡ ጥግ ላይ ቆመው፡ አታሞ—መምታት፡ እንደሚሻላቸው አምናለሁ፡ ዓለምን ለመምሰል ከመሞከር፡ ዛሬ ምሽት በእነዚህ ታላላቅ አስከሬኖች ውስጥ ከመቀመጥ ይልቅ፡ በእጃቸው ኮፍያ ይዘው፡ እንደ ሳሊቬሽን አርሚ ጥግ ላይ ያረጀ ከበሮ ቢመቱ ይሻላልና፡ "የአምልኮ መልክ አላቸው፡ ኃይሉን ግን ክደዋል።"

233 ዛሬ ማታ፡ አንድ ጊዜ፡ እንደገና፡ አድረገው፡ ጌታ ሆይ፡ ሳምሶን "አንድ ጊዜ እንደገና፡ ጌታ ሆይ፡ አንድ ጊዜ እንደገና፡" እንዳለ። አንተ ክርስቶስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ እንደ ሆንህ ይታወቅ፣ ትላንትና፡ ዛሬ እና ለዘላለም

ያው እንደሆንክ። ምልክቱንም እንዲያዩ፡ ምናልባት ድምፁን ያምኑ ዘንድ፡ በመካከላችን ራስህን ላይ። በዚህ፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እጠይቃለሁ። አሜን።

234 የጸሎት መስመር ልንጠራ ነው፡ በፍጥነት። የሚጨርስበት ጊዜ አሁን እንደሆነ አይቻለሁ። ግን የጸሎት መስመር ይኑረን፡ ትንሽ የጸሎት መስመር ብቻ፡ ከዚያም ነገ እንጀምራለን።

235 ዛሬ የጸሎት ካርዶችን ሰጥቷል። ስለዚህ፡ ካርዶችን በየቀኑ እንሰጣለን፡ ስለዚህ እያንዳንዳቸው በተለየ ጊዜ ቢመጡ እድል ያገኛሉ። በፀሎት መስመር ላይ መሆን፡ ያ አይፈውሳችሁም። ማንም ያውቃል፡ በእያንዳንዱ ስብሰባ፡ እዚህ ከተፈወሰው የበለጠ ፈውስ እንዳለ፡ እያችሁ፡ ሁልጊዜ። መንፈስ ቅዱስም እንዲሁ በሁሉም ቦታ አለ። እሱ አማኞችን ብቻ ለማግኘት እየሞከረ ነው፡ ያ ነው በቃ፡ እሱ መድረስ ይችላል።

236 የጸሎት ካርዶችን ፒ፡ እንደ ጳውሎስ። ባለንበት፡ ቦታ እንሁን… መልካም፡ ከአንድ እንጥራ። አንድ፡ ሁለት፡ ሦስት፡ አራት፡ አምስት፡ ስድስት፡ ሰባት፡ ስምንት፡ ዘጠኝ፡ አሥር፡ ከቻላችሁ፡ እዚህ ላይ ቁሙ። የጸሎት ካርዳቸው ፒ፡ ልክ እንደ ጳውሎስ ነው፡ አንድ እስከ አስር ነው፡ መቆም ከቻላችሁ፡ እዚህ በኩል በዚህ በኩል ቁሙ። መቆም ካልቻላችሁ፡ እንዲረዳችሁ አንድ ሰው እናገኛለን። አስር፡ አንድ፡ ሁለት፡ ሶስት፡ አራት፡ አምስት፡ ስድስት፡ ሰባት፡ ስምንት… ደህና፡ ሁለት ተጨማሪ። ስምንት፡ ዘጠኝ፡ አስር፡ መልካም። ከአስር እስከ አስራ አምስት፡ ከአስር እስከ አስራ አምስት፡ ያ አምስት ተጨማሪ ነው። ከአስራ አምስት እስከ ሃያ፡ እየተነሳችሁ እንደሆነ ለማየት እንድችል ተነሱ፡ ፒ፡ ከአስራ አምስት እስከ ሃያ። ከሃያ እስከ ሃያ-ምስት። የትም ብትሆኑ፡ አሁን እንያችሁ። አሁን የተቀሩት ታዳሚዎች እውነተኛ አክባሪ ይሁኑ፡ ጥቂት ደቂቃዎች ብቻ። ያ የጸሎት ካርድ ፒ ነው፡ ከአንድ እስከ ሃያ-አምስት፡ አይደለም እንዴ? ሃያ-አምስት፡ ከአንድ እስከ ሃያ-አምስት።

237 አሁን ሁሉም ሰው በእውነተኛ ትሕትና ይሁን። ለእግዚአብሔር ይህን ያህል ክብር ስጡ፡ መልእክቱን ስጡ። አንድ ደቂቃ ለመንቃት እና ለማሰብ፡ የእግዚአብሔር ውለታ አለባችሁ።

238 አሁን ህዝቡን እያዘጋጁ ይመስለኛል። ያም ደግሞ… የጸሎት ካርድ ካላቸው፡ ሁሉም አልተሰለፉም፡ ፈልገው ያገኛሉ፡ በጥቂት ደቂቃዎች ውስጥ ይነግሩኛል፡ እና ከዚያ እነርሱ… ከዚያም ምናልባት መስማት የተሳነው ወይም የማይችለውን ሰው ካለ ያያሉ።

239 የት እንዳሉ አላውቅም፡ ወዳጆች ሆይ፡ የጸሎት ካርዶች። ልጁ እዚህ ይመጣና… (ማነው የሰጣቸው? አንተ ነህ፡ ወይስ ቢሊ? ቢሊ? ) ደህና እሱ ይመጣና፡ እና ካርዶችን፡ በእናንተ ሰዎች ፊት ይቀላቅላቸዋል፡ ከዚያም የጸሎት ካርድ ይሰጣል፡ ወዲያው ይመጣል፡ ሁላችሁም እንድትቀመጡ ይነግራችኋል፡ የጸሎት ካርድ ይሰጣችኋል። እያችሁ? የት የት እንዳሉ እኔ አላውቅም። ልጁን እዚህ ለማየት እየሞከርኩ ነበር፡ እያችሁ። እና፡ ሌሎች፡ እኔ—እኔ አላውቅም፡ እኔ—እኔ ያንን የማውቅበት መንገድ የለኝም። እኔ እንደማስበው እግዚአብሔር እንደዚያው እንድሆን በሚፈልገው መንገድ ያደርገዋል።

240 አሁን፡ አሁን ሌሎቻችሁ፡ ያ የጸሎት ካርድ የላችሁም። እጃችሁን አንስታችሁ፡ እንዲህ በሉ፡ “የጸሎት ካርድ የለኝም፡ ግን ታምሜአለሁ።” በህንፃው ውስጥ በማንኛውም ቦታ፡ እጃችሁን ከፍ አድርጉ። የት እንዳላችሁ ግድ የለኝም፡ ከፍ አድርጉ... መልካም፡ እዚህ ብዙ ሰዎች የሉም፡ አሁን። መልካም፡ በዚህ መሰረት፡ ነገ የፀሎት መስመርን ለመፀለይ ብዙ ጊዜ አይፈጅም። እዚህ ውስጥ ወደ ሃያ የሚጠጉ ናቸው፡ እዚህ የቆሙት ሳይኖሩ፡ እነዛ የታመሙ ናቸው።

241 ያ ጥሩ ነው። እንደዚያ ስትቀበሉት በማየቴ ደስ ብሎኛል። ምናልባት፡ ካሰብኩት በላይ እምነት ይኖራችኋል። አያችሁ? አያችሁ? ፈውሳችሁን ከተቀበላችሁ፡ ካርዳችሁን ጣሉ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ያ እውነተኛ እምነት ነው። ማንም በእናንተ ላይ እጁን አልጫነም፡ እጃችሁን በክርስቶስ ላይ ጫኑት።

242 አሁን እዚህ ምሽት፡ በጸሎት መሰመር ውስጥ ያልገባችሁ፡ ይህን ታሪክ ታምናላችሁ። የልብሱን ጫፍ እንደዳሰሰችው ሴት፡ ዘወር አለና እንደዳሰሰችው አወቀ፡ ሰንቶቻቹ ታሪኩን ታስታውሳላችሁ? እርግጥ ነው፡ ታስታውሳላችሁ።

243 አሁን ታምናላችሁን፡ እሱ፡ በመጽሐፍ ቅዱስ በዕብራውያን 4 ላይ፡ ያ፡ “እርሱ አሁን፡ ሊቀ ካህናት ነው፡ በድካማችን ሰሜት ሊነካ እንደሚችል ታምናላችሁ”? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] መልካም፡ እሱ ትናንት፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው ከሆነ፡ እንደዚያው አያደርግምን? [“አሜን።”] ከማታ እስከ ማታ፡ እዚህ፡ ይህን አልሰራምን? [“አሜን።”] ሰንቶቻችሁ በሌሎች ሰብሰባዎች ላይ ተገኝታችሁ ሲያደርግ አይታችኋል? ከፍ አድርጉ... [“አሜን።”] በእርግጠኝነት። አያችሁ? በዓለም ዙሪያ! እሱ ያውቃል፡ ሰለእናንተ ሁሉንም ያውቃል።

244 አሁን ምን ለማድረግ እየሞከርኩ እንደሆነ ተመልከቱ? ምን እንድታደርጉ እንደምፈልጋችሁ ሰንቶቻችሁ ትረዳላችሁ? አያችሁ? ማንም እጁን በእናንተ ላይ ሳይጭን፡ እፈልጋችኋለው፡ እንደ እውነተኛ የእግዚአብሔር ትዕዛዛት፡ እፈልጋችኋለው፡ እንዲህ በሉ፡ “ኢየሱስ ክርስቶስ፡ አንተን አምንሃለሁ። አሁን አንተን እንደ መድኃኒቴ እቀበላለሁ። አሁን አንተን እንደ አዳኜ እቀበላለሁ። በሙሉ ልቤ አምናለሁ፡ ሰራው ተከናውኗል።” ከዚያ ያንን ቃል ያዙ፡ ምስክርነታችሁን ያዙ እና ከእሱ ጋር ወደፊት ሂዱ። ከዛ የሚሆነውን ተመልከቱ። አያችሁ? የሚሆነውን ተመልከቱ። አያችሁ? አሁን እናንተ እንዲታደርጉት የምሞክረው ያንን ነው፡ ማመን ያለብን ትክክለኛው መንገድ ያ ነው።

245 ምን አልክ? [አንድ ሰው እንዲህ አለ፡ “አራት እና አሥራ ዘጠኝ።”—አርታዒ።] ቁጥር አራት፡ የጸሎት ካርድ ቁጥር አራት እና አሥራ ዘጠኝ፡ ይቀራል። የጸሎት ካርድ አራት። አንድ ሰው ተመልከቱ፡ አጠገባችሁ ካርዶችን ተመልከቱ። የጸሎት ካርድ ቁጥር አራት እና አሥራ ዘጠኝ ቁጥር። መልካም፡ ለአፍታ ያህል፡ ጠብቁ። አያችሁ፡ እኔ ካልጠራሁት፡ ከዚያ በዛ ላይ እንደገና እመለሳለሁ፡ አያችሁ። ምን አላችሁ? ምን አላችሁ? [“አራት።”] አራት አግኝታችኋል? ዘጠኝ ቁጥርሰ-... ማለት አስራ ዘጠኝ የለም። ምን አላችሁ? [“በተጨማሪም አራት።”] የጸሎት ካርድ ቁጥር አራት ገና አልገባም፡ ወይስ አስራ ዘጠኝ። የሆነ ሰው ካርዶችን ከያዘ፡ ወደ መሰመር ከገቡ። ወይም፡ ተመልከቱ፡ አያችሁ፡ ሊሆን

ይችላል… ያለው… ያ ትንሽ ልጅ ካርድ አግኝቷል? አረጋግጡት፡ አይደለም… ያ ቁጥር አይደለም። **እዚህ** ያለችው ሴት በዚህ ጎማ ወንበር ላይ ያለችው፡ ካርድ ይዛለች? የእሷን ቁጥር አረጋግጡ። ያ—የእሷ ቁጥር ነው? በአልጋ ላይ ያለችው ሴት፡ አዎ? አገኝተውታል። እነሱ፡ ሁሉም አሁን ውስጥ ነው። እሺ። መልካም። አሁን—አሁን፡ የጸሎት ካርድ ያላችሁ ሰዎች፡ ያዙዋቸው። በእግዚአብሔር ቸርነት፡ ልናገለግል ነው።

246 አሁን፡ ወዳጆች ሆይ፡ ይህ የመጨረሻው ምሽት ነው፡ ነገ እሁድ ከሰአት በኋላ ነው፡ እራሳችንን እናረጋጋ። አሁን ያላችሁ አለማመን ሁሉ—ሁል ጊዜ ምክንያታዊ ያልሆነ ሀሳብ፡ ወሰዳችሁ ወለሉ ላይ ጣሉት፡ እንደወትሮ፡ እግራችሁን ስር ላይ አድርጉት፡ እንዲህ በሉ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እኔ አሁን አምንሃለሁ።" ስንቶቻችሁ ይህን ታደርጋላችሁ? [ጉባኤው እንዲህ ይላል፡ "አሜን።"—አርታዒ።] አመሰግናለሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

247 አሁን ማንም አይተወው። በትክክል ተቀመጡ፡ እና እመኑ። በዚህ መንገድ ተመልከቱ፡ እና አሁን ተመልከቱ።

248 የእግዚአብሔር ማንነት ሁልጊዜም ያውቃል፡ የሆነውን አስቀድሞ ማየት ይችላል፡ እና የሆነውንም መናገር፡ እንዴት እንደሆነ፡ ወይም ምን እንደምሆን። ያንን እናውቃለን። ነቢያት የሚታወቁት በዚህ መንገድ ነበር። ኢየሱስ መሲሂ ተብሎ ይጠራ የነበረው በዚህ መንገድ ነበር። እና እርሱ ዛሬም ያው መሲህ ነው በዚያን ጊዜ የነበረው፡ እዚህ ምድር ላይ ያለ አካል ብቻ። መንፈሱን ወደ ሰውነታችሁን፡ እና ወደ ሰውነቴ ለመጠቀም መልሶ ልኳል። አሁን፡ ይህን ማድረግ ላትችሉ ትችላላችሁ። በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ በአንድ ትውልድ ውስጥ፡ አንድ እንዳለ እናውቃለን። ነገር ግን፡ እያችሁ፡ ግን አሁንም ማመን ትችላላችሁ፡ እና ሌሎች ልታደርጓችሁ የምትችሉትን ነገሮች አግኝታችኋል፣ ሁላችሁም።

249 ያ አይን ሰላልሆንኩ፡ ከእንግዲህ ጣት አይሆንም ብሎ፡ ጣት ቢወሰንስ? ይህ ክንድ እንዲህ የሚል ቢሆንስ፡ "ከእንግዲህ ወዲህ ወደ ላይ አልነሳም፡ ምክንያቱም እኔ ዓይን፡ ወይም ጆሮ፡ ካልሆንኩ ክንድ አልሆንም"? ለምን፡ ሰውነቴን ያሽመደመደው ነበር።

እግዚአብሔር ያደረጋችሁትን ሁኑ።

250 ኦራል ሮበርትሰን፡ ቢሊ ግርሃምንን፡ ቶሚ ኦስቦርንን ሰንት ጊዜ አደንቃለሁ!

251 ከእነዚህ ሰዎች መካከል አንዳንዶቹ ወደዚያ ይገቡና እንድህ ያላሉ፡ "ክብር ለእግዚአብሔር ይሁን! እመኑት!" የቡልዶግ እምነት። ከዛ ውጡ፡ በተቻለ መጠን አዲስ ሆናችሁ ከዚያ ውጡ።

252 ቢሊ ግራሃም መልእክት ይዞ ይቆማል፡ ህዝቡን ለጥቂት ደቂቃዎች ይናገራቸዋል፡ እንዲህ ይላል፡ "ውሳኔያችሁን አድርጉ፡ ወደ መሠዊያው ኑ።" ቁሙ እንጂ፡ ሌላ እንቅስቃሴ አታድርጉ።

እንዲህ ይላል፡ "ታዲያ ለምን እንዲህ ታደርጋለህ፡ ቢሊ? "

253 "መልእክቴ ወጥቷል። ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው የመጣው፡" ይላል። ያ ትክክል ነው።

254 እሱም መሆን ባለበት፡ በዚያ በሰዶም ቤተ ክርስቲያን አለ። ሰሙ እንደ አብርሃም በሃ-ም ይጨርሳል፡ ሰድሰት ፊደላት፡ አብርሃም ግን ሰባት ነበር። በባቢሎን ውስጥ፡ የዚያች ቤተ ክርስቲያን መልእክተኛ አያችሁት? በእርግጠኝነት። እንደ ቢሊ ግራሃም የንሰሃ መልእክትን፡ የያዘ አንድም ሰው በሀገሪቱ ውስጥ የለም። በዚያም ጸና። ርቃችሁ ትሄዳላችሁ፡ ሄዳችሁም የቲ-ቦን ስቴክ በልታችሁ፡ የዱቄት ወተት ጠጥታችሁ ወደ መኝታ። ይሁን መልካም ነው።

255 መቆም እና ሰይጣንን መዋጋት ሲገባችሁ! አንድ ጊዜ በሎንግ ቢች፡ ወንድም ጃክ እና እኔ... አባትህ እዚያ ቆመን ነበር።

256 እዚያም አቶ። ፉለር፡ ቻርልስ ፉለር፡ ጥሩ ወንድም፡ ቆመው እየሰበኩ ነበር። በዚያ ቀን ከሰአት በኋላ ወደ ሁለት ወይም ሦስት ሺህ ሰዎች ነበሩ። ስብሰባ ላይ ተቀምጠን አዳመጥን። ከሱ በኋላ፡ አዳራሹን ተከራይቼ ነበር። በዚያም ቆሞ ጥሩ ንግግር አደረገ። እንዲህም አለ፡ “ክርስቶስን መቀበል የሚፈልግ ማንም ሰው ካለ? ” ሁለት ወይም ሶስት ሰዎች ለልጆቻቸውን ለማሰባረክ መጡ። አንዲት ሴት መቀበል እንደምትፈልግ ተናገረች። ከዲያቆናት አንዱ፡ ተነሥቶ ትንሽ ጸሎት አቀረበ፡ ተመልሶ ሄዶ ተቀመጠ። ተጨባበጡ፡ ዞረው ወጡ። ጥሩ-አለባበስ የለበሱ፡ በእውቀት የላቁ ሰዎች ነበሩት፡ ከዚያ ወጥተው ሄዱ።

257 እነሆ የእኔ ገቡ፡ ወገብ የሚያጠነክሩ ጃኬቶች፡ ዊልቼር፡ ዓይነ ስውሮች፡ አንካሶች፡ የቆሰሉት፡ አካል ጉዳተኞች ናቸው። እምነታችሁ እንደዚህ አይነት ነገር ሲያጋጥመውስ!

258 አሁን እዚህ፡ ክርስቶስን ምን እንዲሆን ነው ያልኩት? የማያምኑ ሰዎች በዙሪያው ተቀምጠዋል፡ አንድ እንከን ለማግኘት ይፈልጋሉ፡ አያችሁ፡ አንድ ጉድለትን ለማግኘት እየሞከሩ ነው።

259 አስታውሱ፡ በቅርብ ጊዜ እዚህ በቶሮንቶ፡ እዚያ ቆመን ለታመሙ ሰዎች ስንሰብክ፡ ስንጸልይ ነበር። ያልተለመደ መንፈስ እየተሰማኝ ነበር፡ በግራዬ በኩል ተቀምጦ ነበር። እያየሁት ነበር። አንድ ሰው እዚያ ተቀምጦ ነበር፡ እኔን ለማደንዘዝ ብዙ ሰዎች ቀጥረውት ነበር። ወደ ጦር ሰፈሮች እየዞረ ወታደር በእጃቸው ተንበርክከው እንደ ውሾች እንዲጮሁ፡ ያደርጋቸዋል፡ ሂፕኖቲዝም። ያ እርኩስ መንፈስ ተሰማኝ። ከየት እንደመጣ አላውቅም ነበር። መመልከቴን ቀጠልኩ። ያንን ጥቁር ጥላ አይቻለሁ። ጥቂት ደቂቃዎችን ብቻ ነው የጠበቅኩት። እንድህ አልኩት፡ “አንተ የሰይጣን ልጅ፡ ዲያብሎስ ለምን እንደዚህ ያለ ነገር አእምሮህን አሳወረ? የእግዚአብሔርን መንፈስ ልትፈትን፡ እግዚአብሔርን ልትገዳደር መጥተሃልና፡ ከዚህ ተሸክመው ይወስዱሃል።” እዛው ወንበሩ ላይ ወድያው ሽባ ሆነ አሁንም ሽባ ነው። አያችሁ?

260 ቤተ ክርስቲያን አንቀልድበትም። ስንቶቻችሁ በስብሰባዎች ውስጥ ነበራችሁ እና ተመሳሳይ ነገሮች ሲከሰቱ አይታችኋል፡ የሚከናወኑ ነገሮችን ታውቃላችሁ? በትክክል። ያ ትክክል ነው። አስታውሱ፡ ት—ትሑታን ሁኑ።

አሁን እዚህ አለ፡ እንደማሰበው፡ የመጀመሪያው ሰው። ልክ ነው?

261 አሁን፡ አያችሁ፡ እኔ ሰብኪያለው፡ በዚህ ቀን ምን መሆን እንዳለበት በትክክል ነግሬአችኋለሁ። አሁን ያ ከሆነ፡ ይህ ምልክት ነው። ምልክቱ ያ ነው፣ ከዚያ ምልክቱን ተከትሎ የሚመጣውን ድምጽ እመኑ። አያችሁ?

262 እንግዲህ እነሆ ይህች ሴት አለች። በትክክል፡ ለእናንተ አዲስ ለመጣችሁ፡ ይህ ቅዱስ ዮሐንስ 4 ነው፡ ጌታችን ኢየሱስም ከጉድጓድ አጠገብ እንዲት ሴት የተገናኘበት። በሕይወታቸው፡ ከዚህ በፊት ተገናኝተው አያውቁም ነበር፡ እና ለሴቲቱ ችግሯ ምን እንደሆነ ነገራት። እሷም መሲሑ መሆኑን አውቃለች። ታሪኩን ታውቃላችሁ? እዚህም እንደገና፡ አንድ ወንድና ሴት ገጠሙ። እንግዲህ ሴቲቱ እሷ አይደለችም፡ እኔም ያ ሰው አይደለሁም፡ ግን አሁንም ያው አምላክ ነው። አያችሁ? አሁን፡ ኢየሱስ እንዲህ አለ፡ “እኔ የማደርገውን ሥራ እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ፡” ቅዱስ ዮሐንስ 14፡12።

263 አሁን፡ ይህች ሴ፡ አንተን ሳታውቅ፡ ለምን እንደቆምክ አታውቅም። የቤት ውስጥ ችግር ሊሆን ይችላል። ለሌላ ሰው ሊሆን ይችላል። ምናልባት ታምመሽ ይሆናል። ምናልባት ሊሆን ይችላል… ምናልባት እዚያ ቆመሽ ይሆናል፡ የሆነ ነገር ይዘሽ። ከሆነ፡ ብቻ ምን እንደሚሆን ተመልከቱ። አያችሁ? ምናልባት የሆነ ነገር እያሰመሰልሽ ይሆናል። ምንም ይሁን ምን፡ እኔ አላውቅም… እውነተኛ አማኝ ልትሆኚ ትችያለሽ። እኔ አላውቅም፡ እግዚአብሔር ግን ያውቃል። እውነቱን እንደነገረሽ እና እንዳልተናገረሽ ግን ታውቂያለሽ፡ አይደል? እውነት ከሆነ፡ ታውቂያለሽ።

264 አሁን፡ አያችሁ፡ እምነትሽ ያ ነው። እንዴት ወደዚህ መምጣት ፈለግሽ? አሁን ማንም ሰው ስህተት ነው ብሎ የሚያምን ካለ፡ ወደዚህ መጥቶ በሽተኛውን ይውሰድ፡ ወደዚህ መጥተህ የቀሩትን ውሰዱ። ያንን ካላደረጋችሁ፡ ከዚያም አትኮንኑኝ። አያችሁ?

265 አሁን እዚህ ተመልከቺ፡ እህቴ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ። አሁን ስለአንቺ፡ ምንም አላውቅም። ለኔ እዚህ የቆምሽ ሴት ብቻ ነሽ።

266 እንግዲህ በመጽሐፍ ያረጋገጥሁት፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሆነ፡ በመጨረሻው ቀን ተመልሶ በመንፈሱ ሙላት ራሱን እንደሚገልጥ ቃል ገባ…

267 ልክ እንደ ቤተክርስቲያን መምጣት፡ ከሰው እንደመጣ፡ ከታች ጀምሮ፡ እስከ ጭኑ ድረስ ይወጣል፡ እስከ ራስ፡ ራስም የሰውነት ራስ ነው። አካልም ወደ ላይ ወጥቷል፡ ከመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ጀምሮ፡ ወደ ላይ ወጥቷል፡ በእነዚህ፡ ተሃድሶዎቹ፡ እስከ አሁን ድረስ፡ መጥቷል… የመጣው በማጽደቅ፡ በመቀደስ፡ በመንፈስ ቅዱስ ጥምቀት ነው። አሁን ራስ ነው፡ ክርስቶስ፡ ወደ አካል የሚመጣው፡ የክርስቶስ አካል። የሚያውቀው እርሱ ነው። እጄ እንዴት እንደሚሰራ አያውቅም፡ የሚያውቀው በጭንቅላቴ ነው። እርሱ ግን የሚያውቀው አንዱ ነው፡ ለዚህም ነው እርሱ ቃል የሆነው።

268 እኔ ቃል አይደለሁም። እኔ ሰው ነኝ። ግን፡ አያችሁ፡ ይህን አካል ይጠቀማል። ምክንያቱም፡ ይህን ሥጋ ሊቀድሰው፡ ሊጠቀምበት፡ እና ሰጦታ ሊሰጥ ሞቶአልና። ልክ ከማርሽ እንደማውጣት፡ መንፈስ ቅዱስም ይቆጣጠረዋል።

269 ከዚያም፡ ያደረጋችሁትን፡ እዚህ ለምን እንዳላችሁ ከገለጸ ወይም ቢነግራችሁ፡ ወይም ስለ እናንተ ሲነገር፡ ታምናላችሁ። ጉባኤውስ እንዲሁ ያምናልን? [ጉባኤው “አሜን፡” አለ።—አርታዒ።] ጌታ እግዚአብሔር ያድርግላችሁ።

270 ለእግዚአብሔር ክብር፡ መንፈስን ሁሉ፡ በዚህ ውስጥ፡ በእኔ ቁጥጥር ስር አደርጋለሁ። አሁን ዝም ብላችሁ ተቀመጡ። በዙሪያ አትንቀሳቀሱ።

271 ተመልከቺ፡ ለአፍታ ብቻ። "እይኝ፡" እንደ ጴጥሮስና ዮሐንስ፡ በበሩ ሲያልፉ እንዳሉት። በሌላ አባባል፡ እኔ ለምናገረው ብቻ ትኩረትን ስጪ። እየሽ?

ኢየሱስ ሴትየዋን ጥቂት ጥያቄዎችን ጠየቃት። "መጠጥ አምጭልኝ።"

272 አያችሁ፡ ተመሳሳይ ነገር፡ እየሰበኩ ነበርኩ። አብ ወደዚህ ላከኝ ወደ—ወደ ባቶን ሩዥ። እኔም መጣሁ።

273 አብ በሰማርያ መሄድ እንደሚያስፈልገው ተናገረ። እሱም ተቀመጠ። መጀመሪያ ወደ እርሱ የመጣችው ሴት ነበረች። ያን ምልክትም በዚያች ሴት ላይ አደረገ፡ ከተማውም ሁሉ ንሰሐ ገባ። እንዴት ያለ ልዩነት ነው...

274 ይመስላችኋል፡ እሱ ተመሳሳይ ነገር ቢያደርግ፡ ዛሬ ማታ፡ ሁሉም ባቶን ሩዥ ንሰሃ የሚገቡ ይመስላችኋል? ያንን እጠራጠራለሁ፡ እናንተስ? በእርግጠኝነት እጠራጠራለው። እኛ ግን በመጨረሻዎቹ ቀናት ውስጥ ነን፡ ክፋት ከመቼውም ጊዜ በላይ ክፉ በሆነበት።

275 አሁን የአንቺ ሁኔታሽ። አንቺ እንዲጸለይልሽ እዚህ ነሽ። በእርግጠኝነት። እና በጉሮሮ ህመም እየተሰቃዬሽ ነው። ትክክል ከሆነ፡ እጅሽን አንሺ። እሱ ብቻ ሳይሆን፡ እየጸለይሽለት ያለሽው ሰው አለ። ልጅ ነው፡ እና ያ ልጅ የጉሮሮ ህመም አለው። እና የልጁ ጉሮሮ ሁኔታ ነው፡ በጉሮሮ ውስጥ እድገቶች አሉ። ጌታ እርሱንም እንደሚፈውሰው፡ ታምኚያለሽ? ያ በእጅሽ ያለው መሀረብ፡ ለእግዚአብሔር ያነሳሽው፡ ለምስክርነት... አሁን አትጠራጠሪ። ሄደሽ መሀረቡን በልጁ ላይ አድርጊው። በፍጹም ልብሽ፡ አትጠራጠሪ። እግዚአብሔር ሁለታችሁንም ይፈውሳችኋል እና ደህና ትሆናላችሁ። [ያቺ እህትም "ክብር ይሁንለት! ሃሌ ሉያ!" አለች፡—እርታዒ።] ያን ማድረግ ትችያለሽ? ["ኢየሱስ! አመሰግናለሁ፡ ኢየሱስ!"] ከዚያም ሂጂ፡ ጌታም ከአንቺ ጋር ይሁን። ["ክብር ለእግዚአብሔር! ሃሌ ሉያ!"]

እንዴት ነሽ? ከአንቺ ጋርም፡ አንተዋወቅም።

276 ታምናላችሁ? [ጉባኤው "አሜን፡" አለ።—እርታዒ።] ምልክቱ ይህ ነው። አሁን ድምፁ፡ የሚለው፡ "ወደ ቃሉ ተመለሱ!"

277 አንቺ አታውቂቅም፡ እሱ ያውቅሻል። ስለ አንቺ አንድ ነገር ቢነግረኝ፡ ያ የተናገርኩት ቃል ይረጋገጣል ብለሽ ታምኛለሽ? ያ ማረጋገጫ—ያ ነው። አያችሁ? እኔ አደረገ ስል፡ ያ ትንቢት መናገር ነው። ትንቢቱ ከተፈጸመ፡ ከዚያም እንዲህ አለ፡ "ስሙት።"

278 እየተሰቃየሽበት ያለሽበትም በጣም ከፍተኛ የሆነ የነርቭ ህመም አጋጥሞሻል፡ ነርቭ። እና እብጠት አለብሽ፡ እና እብጠቱ በእግርሽ ላይ ነው። ትክክል ነው፡ አይደል? [ያቺ እህት "አዎ፡" አለች።—እርታዒ።] አሁን ታምኚለሽ? ["አዎን፡ ጌታዬ።"] በይ አምነሽ፡ መንገድሽ ሂጂ። እናም፡ እንዳመንሽ፡ እንዲሁ ይሆናል።

279 እንዴት ነህ? አላውቅህም፡ እግዚአብሔር ግን ያውቅሃል። እግዚአብሔር ችግርህን ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? እኔን ተመልከት። ችግሮች አሉብህ። ግን እዚህ የቆምከው ለሌላ ሰው ነው፡ እና ያ ከአንተ ጋር

ያደገው ነው። እህትህ ናት። ትክክል ነው። አሁን ያቺ እህት ምን ችግር እንዳለባት እግዚአብሔር ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ? ትቀበለዋለህ? የልብ ችግር ገጥሟታል። ያ ትክክል ነው። አሁን ትፈወሳለች ብለህ ታምናለህ? እንግዲያውስ፡ እንደ እምነትህ፡ ለአንተ ይሁን።

280 ነይ፡ እመቤት። እንዴት ነሽ? እግዚአብሔር ችግርሽኝ ምን እንደሆነ፡ ወይም ምን እንዳደረግሽ፡ ወይም የሆነ ነገር ቢነግረኝ፡ እንድታምኚ ያደርግሻል? እኔ... እኔ—እኔ—እኔ እንደ ማላውቅሽ ታውቂያለሽ። እሱ በገባው ቃል መሰረት፡ በኔ ውስጥ ራሱን የሚለይበት ባህሪው ነው። [ያቺ እህት "እምናለው፡" አለች።—አርታዒ።] ያንን ታምኚያለሽ? ["አዎን። አሜን።"]

281 አንቺ ሌላ ነሽ፡ እንደ እድሜሽ ያሉ ሴቶች ሊኖራቸው የምችል ችግር አለብሽ፡ ነገር ግን ዋናው ሃሳብሽ ስለ ሌላ ሰው ነው። ወደ እግዚአብሔር ያለሽ ፍላጎት፡ እግዚአብሔርን የምትፈልጊው ለራስሽ አይደለም፡ ነገር ግን ለሌላ ሰው ነው፡ ይህ ሰው ወንድ ነው። ባልሽ ነው። እና የልብ ችግር አለበት። እሱ እንደሚያደርግ ታምኚያለሽ... እግዚአብሔር ይፈውሰውዋል? ሂጂ፡ እመኚ። እናም፡ እንዳመንሽ፡ እንዲሁ ይሁንልሽ።

282 አሁን፡ ስለ ወቅቱ፡ ስሰብክ የነበርኩትን፡ ሰብከቶችን ሁሉ፡ ተመልከቱ። ያው፡ ምንም ቢሆን፡ ሶስት ወይም አራት ሰዎች አልፈዋል፡ አሁን እዚህ መቆም ይከብደኛል። አያችሁ? አያችሁ፡ ሁሉም ህዝብ ልክ እዚህ ውስጥ፡ ወተት-የሚመስል ይመስላል። አያችሁ? ኢየሱስም እንድህ አለ፡ "ሃይል ከእኔ ወጥቷል።" አንዲት ሴትም፡ ልብሱን ዳሳ፡ ከእርሱ ኃይልን ከወጣ፡ እርሱ የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ፡ በጸጋው የዳነ ኃጢአተኛ፡ እኔስ?

283 እንዲህ አለ፡ "እኔ የማደርገውን እናንተ ደግሞ ታደርጋላችሁ። ከዚህ **በላይ** ታደርጋላችሁ።" ኪንግ ጄምስ "የሚበልጥ፡" እንደሚል አውቃለሁ። ግን ዋናውን ትርጉም ከወሰዳችሁ፡ እንድህ ይላል፡ "ከዚህ **በላይ** ታደርጋላችሁ።" ማንም ከሱ የሚበልጥ ማድረግ አይችልም። ሙታንን አስነስቷል፡ እና ተፈጥሮን አቆሟል፡ ሁሉንም ነገር አደረገ። እርሱ ግን እንድህ አለ፡ "እኔ ወደ አብ እሄዳለሁና፡ ከዚህ **በላይ** ታደርጋላችሁ።"

284 "ዓለም አያየኝም፣ እናንተ ግን ታዩኛላችሁ፡ እኔ... " ተመልከቱ፡ "እኔ፡" እኔ—እኔ የግል ተውላጠ ሰም ነው። "እኔ ከእናንተ ጋር እሆናለሁ፡ በእናንተ ውስጥ" ከዚያም፡ ሰው አይደለም። ክርስቶስ ነው።

285 እኔ እንደዛ የሚለው፡ ትንሽ እራሴን ለማነቃቃት፡ ራሴን መልሼ ለማግኘት ነው። ከተወሰነ ጊዜ በኋላ ወደ አንድ ቦታ ትሄዳላችሁ... **እዛ** ወደ ላይ እያላችሁ አይደለም፡ ወይም **እዚህ** ታች፣ መካከል ነው። ሰንቶቻችሁ ተረድታችኋል? አውቃለው—የተረዳችሁ ይመስላችኋል። እኔም እንደዛው፡ አደርጋለው።

286 ገጣሚዎች እና ነቢያት ሁል ጊዜ ወፈፌዎች እንደሆኑ ታውቃላችሁ? ሰንቶቻችሁ ታውቃላችሁ?

287 ስለ ታላቁ እንግሊዛዊ ገጣሚ ዊልያም ኮፐር፡ ሰንቶቻችሁ ሰምታችኋል? ታውቃላችሁ፡ እንዲህ ብሎ ጻፈ፡ "ከአማኑኤል ደም ስር፡ የተወሰደ በደም የተሞላ ምንጭ አለ።" ያንን መዝሙር ከጻፈ በኋላ፡ ምን እንደደረሰበት ሰምታችኋል? ብዙም ሳይቆይ በመቃብሩ አጠገብ ቆሜያለሁ። ራሱን ለማጥፋት ሞክሮ፡ በወንዙ ውስጥ ሰጠመ።

288 ሰንቶቹ ስለ እስጢፋኖስ ፎስተር ሰምታችኋል፡ ለአሜሪካ ምርጡን የህዝብ መዝሙር የሰጠውን? እሱ በጭንቅላቱ ውስጥ ነበረው ግን በልብ አልነበረም። መነቃቃት በመጣ ቁጥር፡ መዝሙር ይጽፍ ነበር። ከዚያም መነቃቃቱ ሲተወው፡ ከራሱ ጋር ምን ማድረግ እንዳለበት አያውቅም፡ እናም ጠፋ፡ እሱ—እሱ—እሱ ይጠጣ ነበር። እና በመጨረሻም ከዚያ መነቃቃት መውጣት ሲጀምር፡ አንድ አገልጋይ ጠርቶ፡ ምላጭ ወሰዶ ራሱን አጠፋ። ያ ትክክል ነው።

289 ነብዩን ኤልያስን፡ ተመልከቱ። ወደዚያ ወጥቶ ከሰማይ እሳትን ጠራ፡ በመጀመሪያው ቀን ከሰማይ ዝናብ ጠራ፡ ሰማያትንም ዘጋው ያን ሁሉ አደረገ። ከዚያም መነቃቃቱ ሲተወው፡ ወደ ምድረ በዳ ወጣ እና ሊሞት ፈለገ። እግዚአብሔርም፡ ከአርባ ቀን በኋላ፡ ወደ ዋሻው ተመልሶ አገኘው። ልክ ነው?

290 ነቢዩ ዮናስን፡ ተመልከቱ። መልእክቱን ከተናገረ በኋላ፡ ወደ ላይ ወጥቶ በኮረብታው ላይ ተቀመጠ፡ እና እንዲሞት እግዚአብሔርን ለመነ። ኡህ-ሁህ። "ባሪያህ በሰላም እንድሄድ አድርግ።"

291 ሰዎች አይረዱትም። አይ፡ አይ፡ አትረዱትም። እኔም ልገልጸው አልችልም፡ ሌላ ሰውም አይችልም። እግዚአብሔርን ማብራራት አትችሉም። አምላክ በሳይንሳዊ ምርምር አይታወቅም። እግዚአብሔር የሚታወቀው በእምነት ነው። እርሱን እናምነዋለን። እንዴት ማብራራት ትችላላችሁ? ከአሁን በኋላ እምነት፡ እንዴት ይሆናል? እግዚአብሔርን የምናውቀው በእምነት ነው።

292 ቤተክርስቲያን ጉልበቱን፡ እና ድካሙን መቼም አታውቅም፡ እና እሱን ለመሰበር የተሞከረው ድካም፡ እና ፈተና፡ መልእክቱን አታውቅም። እርሱ ያውቃል። ሽልማቴ ከሰዎች አይመጣም።

293 እዚ ተመልከቺ፡ እመቤት። አዎ፡ በፍጥነት። ያቺ ሴት በሞት ጥላ ላይ ነች። እግዚአብሔር ወደ ሴቲቱ ወዲያው አይመጣም፡ እኔ ማየት እችላለው... በዙሪያዋ የሚዞረውን ጥቁርነት አይታያችሁም? እንደ አለም፡ በእርግጥ ትሞታለች። እዚህ በቅርብ ጊዜ፡ እንደዚህ አይነት ነገር ፎቶ አንስተው፡ እቤት ወሰዱት። በአጠገቧ ጥቁር ጥላ ተንጠልጥሏል። በሞት አፋፍ ላይ ነች።

294 ምስክን ሴት ቀዶ ጥገና አድርጋለች። እናም በዚህ ቀዶ ጥገና፡ ለካንሰር ቀዶ ጥገና አድርገዋል። እና አሁን እሷ ችግሮች አሉባት፡ ሁሉም አይነት—የ፡ መልካም፡ ብቻ ውስብስብ ነው። አንድ ነገር፡ በጣም ደክሞሻል መቆም አትችይም። ሌላ ነገር፡ ከፊኛሽ ውስጥ ፈሳሽ ያልፋል። አሁን፡ አንድ ነገር እየተናገርኩ እንዳልሆን እንድታዩት ነው። አያችሁ? ያ ልክ ነው። ግን፡ እመቤት፡ ሐኪሙ ሞከረ። ለዚህም ክብር እሰጠዋለሁ። እርሱ ግን፡ መከላከያ ነበር፡ እግዚአብሔር ግን መድኃኒት ነው። እንደዛ ልትሞቺ ነው። የሚችለውን ሁሉ አድርጓል። ታምኚያለሽ? [ያቺ እህትም "አዎን፡" አለች።—እርታዒ።] ወደዚህ ነይ፡ አንድ ደቂቃ ብቻ።

295 ሁሉን ቻይ አምላክ በሰጠኝ ተልእኮ፡ አሁን በእሳት ዓምድ አምሳል ባለው፡ መልአክ በተረጋገጠው፡ የዚችን ሴት ህይወት እየወሰደ ያለውን ይህን ሰይጣን እወግዛለሁ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም። አሜን።

ሂጂ አሁን፡ እመኚ። በውስጥሽ ባለው ሁሉ፡ እመኚ።

296 ከምንም በላይ ብዙ ሰዎችን የሚገድል ችግር አለብህ፡ የልብ ችግር። ይህ ቁጥር-አንድ ገዳይ በሽታ ነው ይላሉ፡ ግን አይደለም፡ ዋዳጄ። ቁጥር-አንድ በሽታ... ኃጢአት እንደሆነ ይታመናል። ያንን ልብ እንደሚፈውስ እና አንተን ደህና እንደሚያደርግ ታምናለህ? [ያ ወንድም “እርሱ እንደሚችል አውቃለሁ፡” አለ።—እርታዒ።] በል እመንና፡ ሂድ። እግዚአብሀር ይባርክህ።

297 እግዚአብሔር ጀርባሽን የሚፈውስ እና የሚያድንሽ ይመስልሻል? በሙሉ ልብሽ ታምንያለሽ? ሂጂ፡ አመኚ፡ እህቴ። ምን እንደምሆን ተመልከቺ፡ ይሻላሻል።

298 አርትራይተስ እና የልብ ችግር። ነገር ግን እግዚአብሔር ደህና ሊያአርግሽ እንደሚችል ታምኚያለሽ? [ያቺ እህት “እምናለው፡” አለች።—እርታዒ።] በሙሉ ልብሽ? [“አዎን፡ ዋዳጄ።”] ትቀበያለሽ? [“አዎን፡ ዋዳጄ።”] እንቺ እንዳመንሽ፡ ለአንቺ እንደዚሁ ይሆናል። በይ ሂጂ፡ በፍጹም ልብሽ እመኚ፡ እግዚአብሔርም ደህና ያደርግሻል።

299 አንቺም የጀርባ ችግር አለብሽ። ኢየሱስ ክርስቶስ ሊያድንሽ እንደሚችል ታምኚያለሽ? [ያቺ እህት “አዎን፡ ጌታዬ፡” አለች።—እርታዒ።] በይ ሂጂ፡ በፍጹም ልብሽ እመኚ። እኔ ልፈውስሽ አልችልም፡ አየሽ።

300 ፕሮስቴት፡ ነርቭ፡ እና እንዲሁም አርትራይተስ አለብህ። እግዚአብሔር ሊያድንህ፡ ልፈውስህ እንደሚችል ታምናለህ? ትቀበላለህ? ሂድ፡ እመነው፡ እንግዲህ።

301 ብዙ ጊዜ ከእንቅልፍህ፡ ሳል ይቀሰቅሰሃል። እግዚአብሔር ግን አሰምን ይፈውሳል። ይህን ታምናለህ? [ያ ወንድም “አዎን፡ ጌታዬ” አለ።—እርታዒ።] አሁን ደህና እንደሚያደርግህ ታምናለህ? [“አዎን፡ ዋዳጄ።”] እግዚአብሔር ይባርክህ። ሰለ እምነትህ፡ አመሰግናለሁ።

302 አንድም ቃል እንኳን ባልነገርህ፡ እጄን ብቻ ብጭንብህ፡ ታምናለህ? [ያ ወንድም “አዎን፡” አለ።—እርታዒ።] ወደዚህ ና። እጆቼን በአንተ ላይ እጭናለው፡ በኢየሱስ ክርስቶስ ሰም፡ አርትራይተስ ይተውህ። ትቶ ይሄዳል።

303 ነይ። ነይ፡ እህቴ። ታምኚያለሽ? [ያቺ እህት “አዎን፡ ጌታዬ። ከዚህ በፊት በጌታ ተፈውሽያለው፡” አለች።—እርታዒ።] መልካም፡ ያ ድንቅ ነው። [“ሃሌ ሉያ!”] ከዚያ ሄደህ እራትሽን ብይ፡ ሆድሽ ደህና ይሆናል። [“ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ! ሃሌ ሉያ!”]

304 ብዙ የጀርባ ህመም፡ ለረጅም ጊዜ ሲያስቸግርህ ኖረ። ሂድ፡ በማመን ሂድ... ሂድ፡ ደህና እንደምትሆን በማመን ሂድ፡ እና እግዚአብሔር ያደርግልሃል። [ያ ወንድም “እግዚአብሔር አደረገ። አሜን፡” አለ።—እርታዒ።] አሜን። ያ ጥሩ ነው። [“ጌታ ይመስገን።”] ጌታ ይባርክህ፡ ወንድሜ። አሜን።

305 የሰኳር በሽታ፡ በእግዚአብሔር ምንም አይደለም። እሱ ሊፈውስሽ ይችላል። ይህንን ታምኚያለሽ? [ያቺ እህት፡ “አምናለው፡” አለች።—እርታዒ።] መልካም። ተቀበይ፡ እና ሂጂ በፍጹም ልብሽ አሁኑኑ እመኚ።

306 በደምሽ ውስጥም አለ። እግዚአብሔር እንደሚያድንሽ ታምኚለሽ? ሂጂ፡ በፍጹም ልብሽ እመኚ፡ እና ደህና ሁኚ።

307 ያኔ ደስታ ሲሰማሽ እንደፈወሰሽ ታምኚያለሽ? ፈውሶሻል።

308 የሴት ችግር። የልብ ችግር። ታምኚያለሽ? [ያቺ እህት “እምናለው።” አለች።—አርታዒ።] ሂጂ፡ በ—በኢየሱስ ስም ተፈወሺ።

309 እግዚአብሔር ጀርባሽን እንደሚያስተካክል ታምኚያለሽ፡ ኩላሊትሽም... ይባርክሽ! ቀጥይ ሂጂ።

እኔ አልፈውስም። እኔ መፈወስ አልችልም። እኔ ፈዋሽ አይደለሁም።

310 ስለ ጀርባው ሲናገር ምን አሰብክ፡ የአንተም ደህና፡ እንደምሆን ታምናለህ? መልካም፡ እያመንክ፡ ሂድ፡ ከዚያ... ሂድ በፍጹም ልብህ፡ እመን።

311 ያንተም ደግሞ፡ እግዚአብሔር እንደምፈውሰህ ታምናለህ? ሂድ፡ በፍጹም ልብህ፡ እመን። እግዚአብሔር ይሰጣችኋል... ቢሆንም፡ ማመን አለባችሁ።

312 አንቺንም፡ እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኚአለሽ? [ያቺ እህት “ጌታ ይመስገን! እርግጠኛ ነኝ፡” አለች።—አርታዒ።] መልካም። እግዚአብሀር ይባርክሽ። ልክ እንደዚሁ ቀጥይ እና በሙሉ ልብሽ እመኚ።

313 ና፡ ዎዳጄ። አንድ ያረጀ ነጭ ነጠብጣብ ወደ ታች ይወርዳል። የዚያ ምርመራ የስኳር በሽታን ያሳያል። [ያ ወንድም “የስኳር በሽታ፡” አለ።—አርታዒ።] ይፈውሰኛል ብለህ ታምናለህ? አሁን በእምነት፡ ወደ ፈሰሰው ደም ወደ ቀራንዮ እንሂድ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ይፈወስ። አሜን። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። በሙሉ ልብህ እመን። ታምናለህ? [“በትክክል እውነት።”]

314 አሁን በጉባኤ ያላችሁ አንዳንዶቻችሁስ? በፍጹም ልባችሁ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ትናንት፡ ዛሬ፡ እና ለዘላለም ያው እንደሆነ ታምናላችሁ? ይህን ታምናላችሁ? [ጉባኤው እንዲህ ይላል፡ “አሜን።”—አርታዒ።]

315 **በዚህ** መደዳ ውስጥ ያላችሁስ? የተቀመጠች ምስኪን ሴት፡ እዚያ እኔን እያየች፡ በሴት ችግር እየተሰቃየች ነው፡ እግዚአብሔር እንደሚፈውስሽ ታምኛለሽ? ትንሽ ሰማያዊ ቀሚስ ያረግሽው። መልካም። አሁን እመኚ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ ደህና ያደርግሻል። ያን ያህል ቀላል ነው።

316 ሴትየዋ ከኋላሽ የተቀመችው፡ ጥቁር ፀጉር። እንዲህ አለች፡ “ጌታ ሆይ፡ አመሰግንሃለሁ።” የሆነ ነገር ነክቶታል። ምን እንደሆነ አላወቀችም። የፊኛ ችግር ትቶሻል፡ እዚያው ተቀምጠሽ፡ ከሴትየዋ ጀርባ ልክ በዚያን ጊዜ ተፈወሰች። በሙሉ ልብሽ ካመንሽ፡ እመቤት። ታምኚያለሽ? መልካም፡ መቀበል ከፈለግሽ እጅሽኝ አንሺ። እግዚአብሔር ጤነኛ ያድርግሻል።

**እዚህ** ወደታች፡ የሆነ ሰው አለ?

317 እዚያ ከኋላ በጉባኤ ውስጥ፡ አሁን በእውነት ዝቅ በሉ። አትንቀሳቀሱ። አያችሁ፡ እነዚህ በሽታዎች ከአንዱ ወደ ሌላው ይሰፍራሉና።

318 አንተስ፡ ዎዳጄ? እኚህ አዛውንት እዚህ ወንበር ላይ የተቀመጠው? ታምናለህ? እግዚአብሔር ሊፈውስህ እንደሚችል ታምናለህ? አርትራይተስ፡ እና ብሮንካይተስ አለብህ። እግዚአብሔር ይህን እንደሚያስተካክል ታምናለህ? ታምናለህ? መልካም፡ የጠየቅከውን ማግኘት ትችላለህ። “ማመን ከቻልክ!”

319 ምን ይመስልሻል፡ እመቤት፡ ከአጠገቡ የተቀመጥሽ? አንቺስ፡ ታምኚአለሽ? ታምኚአለሽ? ችግርሽ ምን እንደሆነ እግዚአብሔር ሊነግረኝ እንደሚችል ታምኚአለሽ? ከእኔ ርቀሽ ነው ያለሽው። እሱን አሁን እመኚ።

እውነት እንደነገርኩሽ ታምኚአለሽ? ከዚያም የደም ግፊትሽ ይቀንሳል። ታምኚአለሽ?

320 አንተም፡ እጅህን አንስተሃል። ልታበረታታት እየሞከርክ ነበር። እግዚአብሔር ምን እንደሆነ ሊነግረኝ እንደሚችል ታምናለህ... እሷን ለመርዳት በጣም ጥሩ ነበርክ፡ አሁን እግዚአብሔር ሊረዳህ ጥሩ ይሆናል። የሚያስጨንቅህ መንፈሳዊ ችግር አለብህ። ትክክል ከሆነ፡ እጅህን **እንደዚህ** አወዛውዝ። አሁን ሊፈታ ነው። እርሱ ያስተካክለዋል።

321 ስንቶች ታምናላችሁ? ስንቶቻችሁ ትቀበላላችሁ-... ክርስቲያን፡ ያልሆናችሁ የተሰማው—ኢየሱስ ክርስቶስ እዚህ አለ የሚል ስሜት የተሰማው፡ አሁን መቆም የሚፈልግ፡ እንዲህ ይበል፡ "ኢየሱስ ሆይ፡ ራሴን እንደ ኃጢአተኛ መለየት እፈልጋለሁ፡ ኃጢአቴን ይቅር ትለኛለህ? " በእግሮቻቹ ላይ ቁሙ። ጌታ ይባርክህ፡ ዎዳጄ። እግዚአብሔር ይባርሽ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። ያ ነው... እግዚአብሔር ይባርክህ፡ አንተ፡ አንተ፡ አንተ። ይህ፡ ያያችኋል። ያንን ስታደርጉ ስምህን ያስቀምጣል።

322 እዚህ ወደ በረንዳው፡ ተነሱ፡ እንዲህ በሉት፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ እፈልጋለሁ፡ መታወቅ እፈልጋለሁ። ለነፍሴ ምህረትን እፈልጋለሁ።" ጌታ ይባርክህ፡ ዎዳጄ። "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ምሕረትን እፈልጋለሁ።"

323 ማየት አትችልም፡ ወዳጄ፡ እሱ እዚህ ነው? እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወጣት። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ወጣት ሴት። ያደረጋችሁት ታላቅ ነገር ነው። አሁን ሌላ ያላደረገ ካለ፡ ተነስ፡ እንድህ በል፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ መለየት እፈልጋለሁ፡ ዛሬ ማታ፡ እራሴን ለይቻለሁ።"

324 "ኃጢአቱን የሚናዘዝ፡ ምሕረትን ያገኛል። ኃጢአቱን የሚሰውር፡ አይለማም።"

325 በእርሱ ፊት፡ ትሆናላችሁ? እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። እፈልጋለሁ... እግዚአብሔር ይባርካችሁ። አዎ። እና እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ጌታ ይባርክህ፡ ዎዳጄ። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። ጌታ ይባርክህ።

326 እንዲህ ትላላችሁ፡ "ይህ ማለት ምንም ማለት ነው? " በሞት እና በህይወት መካከል፡ ይህ ልዩነት ነው።

327 እዚህ የእርሱን መገኘት ታውቃላችሁ? ያንን ታውቃላችሁ? ያ ይሰማችኋል? እያችሁ፡ እያችሁ፡ ሲሰራ ታያላችሁ። ያ እርሱ ነው። እሱ እንደሚያደርገው የተናገረውም ይህንኑ ነው። ታምናላችሁ? [ጉባኤው እንዲህ ይላል፡ "አሜን።"—እርታዒ።]

328 እንዲህ የሚል ሌላ ሰው፡ "ጌታ ሆይ፡ ራሴን እንደ ኃጢአተኛ መለየት እፈልጋለሁ፡ አሁን ኃጢአቴን ይቅር በለኝ።" አስቀድማችሁ ቆማችሁ ከሆነ፡ እጃችሁን ብቻ አንሱ። አንዳንዶቻችሁ በግድግዳው አካባቢ፡ ከፍ አድርጉ... እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። ሌላ ሰው፡ በረንዳው ላይ ወደ ኋላ፡ እንዲህ በሉ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ራሴን መለየት እፈልጋለሁ። በዚህ ምሽት፡ በመለኮታዊ መገኘት ሆኜ፡ ምህረትን እጠይቃለሁ፡ የሚፈርደኝ

እምላክ፡ አሁን መገኘቱ እዚህ እንዳለ፡ እምኜ ነው። ለልቤ እየተናገረ እንደሆነ እና እንደተሳሳትኩ እየነገረኝ እንደሆነ ያውቃል። ተነስቼ ተሳስቻለሁ ማለት እፈልጋለሁ። ስህተቴን እናዘዛለሁ። በልቤ፡ እየኮነነከኝ ነው።" የጸሎቱን መስመር ያቆምኩት ለዚህ ነው። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

329 ያንን ያቆምኩት ለምን መሰላችሁ? ያ መከሰት እንዳለበት ስለማውቅ ነው ያቆምኩት።

330 አሁን፡ እዚህ ሌሎች አሉ፡ አትቆሙም? ተነሱና አንድ ነገር ለልብህ እየተናገረ ነው በል፡ "ተሳስተሃል።" ጌታ ይባርክህ፡ ዎዳጄ። እግዚአብሔር ይባርክህ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። እግዚአብሔር ይባርካችሁ። "ተሳስቻለሁ። ይቅር በለኝ፡ ጌታ ሆይ። ራሴን እየገለጽኩ ነው። ተነሥቻለሁ፡ ጌታ ሆይ፡ በመገኘትህ ፊት። እዚህ እንዳለህ አውቃለሁ። እኔ... እዚህ መሆን አለብህ። ይህ ይሆናል ብለሃል—ማድረግ ያለብህን ነገር። አሁን እኔ እሆናለሁ... ምልክቱን እይቻለሁ፡ እናም ይህ ቀን የዚህ ቀን ምልክት መሆን እንዳለበት እንደተገለፀልኝ አውቃለሁ። ወደ ንስሐ የሚጠራውን ድምፅ እሰማለሁ። እነሆ፡ ጌታ ሆይ። ምልክቱን አምናለሁ። ድምፁን እሰማለሁ።"

331 አሁን የሚናገራችሁ ድምጽ! ተመለሱ፡ ኦ የተበታተናችሁ! ተመለሱ፡ ኦ ተቅበዝባዥ ኮከብ! ተመልሰ፡ ኦ የተባረርከው ሆይ! ተመለስ፡ ዛሬ ማታ!

332 አትመለሱም? ብቻ ቆማችሁ እንድህ በሉ፡ "ምህረትን በመጠየቅ፡ ራሴን እንደ ኃጢአተኛ ለይቻለሁ።" ያንን ታደርጋላችሁ፡ የሆነ ሰው? እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ እዛ ላይ፡ ልጄ። እኔ ባልፍህ፡ እሱ አያደርገውም። እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። ያ በጣም ጥሩ ነው። ያ በጣም ጥሩ ነው። ሌላ ሰው? ብቻ ቀጥሉ... አንድ ደቂቃ ብቻ መያዝ እፈልጋለሁ፡ ምክንያቱም አሁንም እዚህ ትንሽ ሸክም ስለሚሰማኝ፡ አያችሁ። ሌላ ሰው? እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ እመቤት። ያንን የምናደርግበት መንገድ ነው። ያ ነው በቃ። ሌላ ሰው፡ "እኔ ራሴን መለየት እፈልጋለሁ፡ እራሴን እንሳ እና ተሳስቻለሁ። ምህረትን እጠይቃለሁ"? ታደርጋላችሁ? ወደ ፊት ከማለፋችን በፊት በፍጥነት ተነሱና፡ እንዲህ በሉ፡ "ጌታ ኢየሱስ ሆይ ራሴን፡ መለየት እፈልጋለሁ።" እግዚአብሔር ይባርክሽ፡ ወጣት ሴት።

333 ታውቃላችሁ፡ ምናልባት ወደ ቤታችሁ ከመሄዳችሁ በፊት፡ ግን አንዳንድ ጊዜ ወይም ሌላ ጊዜ ቀዝቃዛ ጭጋግ በፊታችሁ ላይ ይመጣል። ምናልባት አንድ ጠዋት ሐኪሙ ይመጣል እና የልብ ምታችሁ ወደ እጅጌያችሁ ሲወጣ ይሰማዋል፡ ሌላ ምንም ነገር ማድረግ አይቻልም። ከዚያም ቀዝቃዛው የሞት ሞገዶች በፊታችሁ ላይ ሲንሳፈፍ ይሰማችኋል። ያደረጋችሁትን ታስታውሳላችሁ።

334 አስታውሱ፡ እነሱ በጥልቀት ሊቀብሯችሁ አይችሉም፡ ምንም ሊያደርግላችሁ አይችሉም። እግዚአብሔር ቃል ገብቷል፡ "በመጨረሻው ቀን፡ እንደገና አስነሳሃለሁ።" ተመልከቱ። "ቃሌን የሚሰማ የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም ሕይወት አለው እና ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድም አይመጣም።" ከቻለ አንድ ሰው ያንን ይፋቅ። ኢየሱስ ክርስቶስ እንደዚያ ብሏል። "ቃሌን የሚያምን (ያ 'መረዳት ነው') የላከኝንም የሚያምን፡ የዘላለም

ሕይወት አለው፡ ከሞት ወደ ሕይወት ተሻገረ እንጂ፡ ወደ ፍርድና፡ ኩነኔ ከቶ አይመጣም።” ምክንያቱም፡ ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት፡ እግዚአብሔር ያስነሣውን፡ በእግዚአብሔር በአንድያ ልጅ አምኗልና፡ እና በዚህ ምሽት፡ ህያው ሆኖ፡ የትንሳኤውን ባህሪ እያሳየ ነው።

335 ሌላ ተነሥቶ፡ ከዚያ በኋላ፡ እንዲህ የሚል ሌላው፡ “መቀበል እፈልጋለሁ። እሱን መቀበል እፈልጋለሁ”? እግዚያብሔር ይባርክ። እግዚአብሔር ይባርክሽ። ያ በጣም ጥሩ ነው፡ ምስክን ሴት። ያ ገራሚ ነገር ነው። እንድታስተውሉ እፈልጋለሁ።

336 እዚህ ከተወሰነ ጊዜ በፊት፡ አንድ ጊዜ መሠዊያ ሲጠራ፡ ሰዎች እየመጡ፡ ማስቲካ እያኘኩ ተመለከትኩ፡ በጎን በኩል እርስ በርስ በቡጢ ሰመታቱ።

337 ነገር ግን በሰዎች ፊት ላይ ያለውን ቅንነት አስተውላችኋል? እነርሱ ወጣት ሴቶች፡ ስለ አጭር ፀጉራቸው፡ ሜክ-አፕ ስለለበሱ ከተኮነኑ በኋላ እንኳ፡ ከዚያ ሜክ-አፕ እንደተቀቡ፡ ከአጭር ፀጉር ጋር፡ እንደዚሁ ይቆሙና፡ “እኔ ኃጢአተኛ ነኝ። ማረኝ፡ አምላኬ።” ያ ዘሮች እዚያ የሚቀመጡት ናቸው። ብርሃኑ በላዩ ወጣ፡ እነሱም ያውቁታል። እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

አሁን አንገታችንን ዝቅ እናድርግ።

338 እዚህ እያንዳንዱን አማኝ፡ ያ ከቆመው ሰው አጠገብ የቆመ፡ በቆመው ሰው ላይ እጅ ይጫን፡ (ትጭናላችሁ? )፡ ከቆሙት መካከል። ከጎናችሁ የቆሙ ካሉ። ክርስቲያን ከሆናችሁ፡ እጃችሁን በእነሱ ላይ አድርጉ፡ “እህት፡ ወንድም፡ አሁን እጄን በእናንተ ላይ አድርግያለው። ልጸልይ ነው።”

339 የሰማዩ አባታችን ሆይ፡ በዚህ ምሽት እዚህ ያሉ አሉ—የሚያምኑህ። “አንዳንድ ዘሮች በመንገድ ዳር ወደቁ፡” እንዲህ ብለሃል፡ “ወፎቹ መጡ እና ለቅመው ወሰዱት። ሌሎች ደግሞ በድንጋያማ መሬት፡ በእሾህና አሜከላ ላይ ይወድቃሉ። ነገር ግን አንዳንዶቹ ወደ ጥሩ፡ ለም መሬት ይሄዳሉ።” እና የአንተ መኖር፡ ዛሬ ማታ፡ አንተ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሆንክ ለዘላለም በሕይወት እንዳለህ፡ ብዙዎችን እዚህ አሳምኗል። እና ቃል ገብተሃል፡ ምክንያቱም ስለምትኖር፡ እኛም መኖር እንችላለን።

340 ጌታ ኢየሱስ ሆይ፡ ተነሥተው እንዳመኑህ ምስክር ሆነው ቆመዋል። አሁን፡ ጌታ ሆይ፡ በዚያ ቀን እንደምትቆምላቸው አውቃለሁ። አድርገው፡ ጌታ ሆይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ ለአንተ ሰጥቻቸዋለሁ። ወደ ጥሩ ቤተ ክርስቲያን ሄደው በክርስትና ጥምቀት ይጠመቁ። ከጥሩ አማኞች ሰብሰብ ጋር ይተባበሩ። በመንፈስ ቅዱስም ይሞሉ። በዚያ ቀን በዘውድህ ውስጥ የከበሩ የወንጌል፡ ዋንጫዎች ይሁኑ። እናም በዚያን ታላቅ ቀን ዳግመኛ ካላየኋቸው፡ በዚያ ቀን በራዕይ ላይ ልያቸው፡ እንዲህ ሲሉ፡ “አታስታውሰኝም? ያን ምሽት፡ የተነሳሁት፡ በባቶን ሩዥ ነበር።” አድርገው፡ አባት ሆይ። በክርስቶስ ስም፡ ያንተ ናቸው።

341 እነሆ፡ በፊቴ የመሀረቦች ሳጥን፡ ትንንሽ ጫማ፡ ቦት ጫማ፡ መሀረብ፡ እና ጨርቆች፡ እና ሸርጦች፡ ተቀምጧል። በመጽሐፍ ቅዱስ፡ እንደተማርነው፡ እነርሱም ከቅዱስ ጳውሎስ አካል፡ መሀረብና ልብስ ሲወሰዱ፡ ርኩሳን መናፍስትም ከሕዝቡ ወጣ። አሁንም፡ አባት ሆይ፡ እኛ ቅዱስ ጳውሎስ እንዳልሆንን እናውቃለን፡ ነገር ግን አንተ አሁንም ያው አምላክ ነህ፡ ስለዚህ ይህ ትውልድ በቅንነት አምኖ ያንኑ ውጤት፡ እንድትሰጣቸው እጸልያለሁ።

ጳውሎስን ጳውሎስ ስለነበር በፍጹም አላመኑትም፡ አንተ ከጳውሎስ ጋር ራስህን ስለለየህ ጳውሎስን አምነዋል። ዛሬ ማታ ተመሳሳይ ነገር አምነዋል፡ ጌታ ሆይ፡ አሁን ዛሬ ማታ፡ አንተ በእኛ መካከል ገልጠሃል፡ እና አንድ ቀን፡ እንላለን...

342 አንድ ጸሃፊ፡ እንዲህ ይለናል፡ “እስራኤል ወደ ተስፋይቱ ምድር በመንገድ ላይ ነበረች፡ ከተስፋይቱ ምድር ሊያጠፋቸው፡ የቀይ ባህር በመንገድ ገባ።” ጸሐፊው፡ እንዲህ አለ፡ “በእስራኤል ላይ በተንቀሳቀሰ ጊዜ፡ እግዚአብሔር በዚያ የእሳት ዓምድ፡ በተቆጡ ዓይኖች ተመለከተ። ለማያምኑት ጨለማ፡ ዕውርነትን፡ ለእስራኤልም ብርሃን አደረገ። ያ ቀይ ባህር መንገድ ላይ ሲገባ፡ ፈራ፡ ወደ ኋላም ተንከባሎ፡ እስራኤልም በደረቅ ምድር ወደ ተስፋይቱ ምድር ተሻገረ።”

343 ጌታ እግዚአብሔር ሆይ፡ ዛሬ ማታ፡ በልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ደም፡ ተመልከት። በእነዚህ መሃረብ ላይ እጆቼን ስጭንባቸው፡ በሽተኞች ላይ ሲቀመጡ፡ ጌታ ሆይ፡ መንፈስ ቅዱስ፡ ያንን ሰው ተመልከት፡ እና በሽታውም ከእርሱ ይራቅ፡ እና ወደዚያች ጥሩ ጤንነት እና ጥንካሬ ወደዚያ አገር ይሻገሩ። መጽሐፍ ቅዱስ፡ እንዲህ ብሏል፡ “ከሁሉም በላይ፡” እኛ እንድንፈልግ ይፈልጉ ነበር “በጤና ላይ ብልጽግና።” አድርገው፡ ጌታ ሆይ። በኢየሱስ ክርስቶስ ስም፡ እልካቸዋለሁ። አሜን።

> ... እኔ እከተላለሁ፡
> የሚመራበት ቦታ...

ዝም ብለን እንዘምር።

> ... እከተላለው፡
> ከእርሱ ጋር እሄዳለሁ፡

አሁን የሱ መገኘት እዚህ አለ፡ እሱን በጣፋጭ፡ መዝሙር እናመልከው።

> ... እስከ መጨረሻ።

344 በእውነቱ፡ እንደዚህ መዘመር፡ ትችላላችሁ፡

> የሚመራኝን ቦታ እከተላለሁ፡
> የሚመራኝን ቦታ እከተላለሁ፡
> የሚመራኝን ቦታ እከተላለሁ፡
> እሄዳለሁ...

አሁን ከፈለጋችሁ፡ እጆቻችሁን አንሱ።

> ... ከእርሱ ጋር በመንገድ ሁሉ።

አሁን እንነሳ፡ እጆቻችሁን እንደገና አንሱ።

> ... እሱ በአትክልቱ ውስጥ፡

345 አሁን ሁሉም በመንፈስ ይዘምራል። እውነተኛ የምቆርጥ መልእክት። በመገኘቱ እናመልከው። መመለክን ይወዳልና።

> ... በአትክልቱ ቦታ ውስጥ፡
> በአትክልቱ ሰፍራ ከእርሱ ጋር እሄዳለሁ፡
> ከእርሱ ጋር፡ ሁሉንም ቦታ ከእርሱ ጋር...

አሁን እናንጎራጉረው።

እችላለሁ...

346 አሁን ያንን ስታደርጉ፡ ከአንድ ሰው ጋር እንድትጨባበጡ እፈልጋለሁ፡ እንድህ በላቸው፡ “እግዚአብሔር ይባርክህ፡ የሰማይ ተጓዥ። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ የሰማይ ተጓዥ፡” ልክ እንደዛ። እርስ በርሳችን አንድ ነን። ሜቶዲስት፡ እና ባፕቲስት፡ ፕሪስባይቴሪያን፡ ጴንጤቆስጤዎች፡ ሁላችሁም እርስ በርሳችሁ ተጨባበጡ፡ “እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ የሰማይ ተጓዦች።” ያ ነው እኛ፡ የሰማይ ተጓዦች ነን።

... በአትክልት ቦታ፡

347 እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ተጓዦች። እግዚአብሔር ይባርካችሁ፡ ከሁሉም ሰው ጋር እንግዳ ነን። እግዚአብሔር ይባርክህ፡ ወንድሜ። እግዚአብሔር ይባርክህ። [በቴፕ ላይ ባዶ ቦታ—አርታዒ።]

... በአትክልት ስፍራ፡

አሁን እጆቻችሁን አንሱ።

ከእርሱ ጋር እሄዳለሁ፡ ኦህ፡ ከእሱ ጋር እስከመጨረሻው እሄዳለሁ።

348 በትህትና፡ በጸሎት፡ አንገታችንን ዝቅ እናድርግ። እትርሱ፡ በጠዋት፡ ሰንበት ትምህርት ቤት አለ።

349 **በሆነ መንገድ**፡ የእግዚአብሄርን መኖር በልቤ ውስጥ እውን ሆኖ ነው የተረዳሁት። ዛሬ ማታ፡ ማቆም ለእኔ፡ በጣም ከባድ ነው። በዚህ ምሽት፡ መንፈስ ቅዱስ እንደተደሰተ ይሰማኛል። ነገ ታላቅ ሰብሰባ እናደርጋለን፡ ሰዎች ወደ ክርስቶስ ሲመጡ እናያለን፡ አያችሁ። አንድ ሰው ለምን የመሰዊያውን ጥሪ እንዳልጠራሁ የሚጠይቅ አለ። እስክምመራኝ ድረስ እጠብቃለሁ። አያችሁ?

350 እንድህ እጁን ያነሳ፡ ወይም የተነሣ ሁሉ፡ እኔ አምናለው ነገ በመልካም ቤተክርስቲያን እንደምትገኙ አምናለሁ፡ በአማኞች መካከል ተቀመጡ።

351 አንገታችንን ዝቅ እንዳደረግን፡ እዚህ ፓስተር ከፈቀደ፡ እዝህ መጥቶ፡ እንድጨርስልን እንጠይቃለን። አሁን ራሶቻችን እና ልባችን በእግዚአብሔር ፊት ዝቅ ብሎ እያለ፡ እግዚአብሔር ይባርካችሁ።

64-0321E የምልክቱ ድምጽ
ዴንሃም ስፕሪንግስ ሀይ ስኩል
ዴንሃም ስፕሪንግስ, ሉዊዚያና ዩ.ኤስ.ኤ

AMHARIC

©2024 VGR, ALL RIGHTS RESERVED

Voice Of God Recordings
P.O. Box 950, Jeffersonville, Indiana 47131 U.S.A.
www.branham.org

## የቅጂ መብት ማሳሰቢያ

ይህ መጽሐፍ የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ይሰፋ ዘንድ፣ በቤት ለግል ጠቀሜታም ሆነ ለሌሎች ሰዎች ያለ ክፍያ ለማበርከት፣ በቤት ማተሚያን መጠቀም ይቻላል። ይህ መጽሐፍ ያለ ቮይስ ኦፍ ጋድ ሪከርዲንግስ በጽሑፍ የተደገፈ ህጋዊ ፈቃድ መሸጥም ሆነ፣ አብዝቶ ማተም፣ በዌብ ሳይት ላይ ማስቀመጥ፣ በማከማቻ ዘዴዎች ላይ ማስቀመጥ፣ ወደ ሌሎች ቋንቋዎች መተርጎምም ሆነ የድጋፍ ማሰባሰቢያ አድርጎ መጠቀም የተከለከለ ነው። ህጋዊ መብቱም ሁሉ የተጠበቀ ነው ።

ለተጨማሪ መረጃ ወይም ተጨማሪ ግብዓቶች ቢፈልጉ፣ እባኮትን ይህ አድራሻ ይጠቀሙ፡

VOICE OF GOD RECORDINGS

P.O. BOX 950, JEFFERSONVILLE, INDIANA 47131 U.S.A.

www.branham.org